ከአቡነ ሺኖዳ መንፈሳዊ ገፅ የተቀናበሩ ልዩ ልዩ ፅሑፎች

በዲ/ን ሚኪኤለ ገ/ሰላሴ

ሰኔ 08,2012 ዓ/ም

ክፍል 2

በረከታችው ይደርበን!!

ራስን ድል መንሳት

የስጋ ምኞትንና ፍላጎትን አስመልክቶ ጸምና ድንግልናን ራስን ድል የመንሳት መንገዶች ናቸው። ነፍስን አስመልክቶ የሚጠቀስም ሌላ መንገድ አለ።ራሱን የሚገዛና እርሱነቱን ወደ ዓለማዊ ደስታ ከማዘንበል የሚያግድ ሰው ብጹዕ ነው።

ማንነት ልታይ ልታይ ሲል፣ ጉራውን ሊገልጥ ሊተብት ይችላል።በዚህ ሁሉ ግን ልንቃወመው ይገባናል። ለእኛ #ከእግዚአብሔር ጋር መደሰትና መልካም የሆነው ነገር ለመጪው ህይወት ብናቆይ የሚሻለን መሆኑን ራሳችንን ልናሳምነው ይገባናል። በዚህ ዓለም ድስታን ለማግኘት በሚፈልጉ ሰዎች ላይ #የመድኃኒ_ዓለም ቃል ይመሰክርባቸዋል፡- " . . . እውነት እላችኋለው፡- ዋጋቸውን ተቀብለዋል።"ማቴ6፡5።

ስለዚህ በምድር ላይ ያሉ መብቶችህን ሁሉ ለማግኘት አትሞክር እግዚአብሔር እያንዳንዱ ዕንባህን ከዓይኖችህ ላይ የሚጠርግበት በወድያኛው ዓለም ቢሆንልህ ይሻልሃልና።

ማንነትህ ወይም ስጋህ አሁን ላለህበት ዓለም ደስታ የሚያዘም ከሆነ በርትተህ ተከላከላቸው። በራስህ ወይም በስጋህ ላይ የምይወስደው ይህ እርምጃ ጭካኔ አደለም፡ለእነርሱ ዘላለማዊ ሕይወትን ማረጋገጫ እንጂ!

ራሱን በዚህ ዓለም ሳለ የሚንከባከባት ያጠፋታል። ራሱን በጥብቅ ከመቆጣጠር ችላ የሚል ሰው በእርሱ ላይ ኃይል እንዲኖረው ያደርጋል።ሰለሆነም ራሱን ለጽድቅ ከሚያለማምደውና #የእግዚአብሔር መንገድ ከሚተገብረው ሰው በተለየ ሁኔታ በመንፈሳዊ ጠባዩ ላይ እንዲያምጽ ያደርገዋል።

ራስን ድል መንሳት የሚሰጠው መንፈሳዊ ደስታ ከስጋ ደስታ ጋር እንደማይነጻጸር እርግጠኛ ሁን። ከሁሉ በጣም የሚያስደንቀው የራስ ጉራ ሙሉ ለሙሉ መጥፋት በሚገባው በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ከፍ ከፍ ማለቱ ነው።

#ቅድስነታችው_አቡነ_ሺኖዳ_ሣልሳዊ

(መንፈሳዊ ውግያዎች ከሚል መጽሓፋቸው የተወሰደ ተጽሓፈ በእግዚአብሔር ፍቅር ነው።)

ከእግዚአብሔር መማር

ዕውቀት ፈጽሞ መቀበል የማይችሉ አንዳንድ አላዋቂ ሰዎች አሉ። ሌሎች ደግሞ ከሰዎች የሚማሩ አሉ። እነዚህኛዋቹ የበለጠ አላዋቂዎች ናቸው። በትክክል ተምረዋል ወይም አዋቂዎች ናቸው የሚባሉ ግን በቀጥታ #ከእግዚአብሔር የሚማሩ ናቸው።

ሰው ግን እግዚአብሔርን ትቶ ከሌላ መማር በጀመረ ጊዜ አላዋቂ መሆንን ጀመረ ። መጀመሪያ ከእባቢቱ ተማረና መልካሙንና ክፉውን ከምታሳውቀው ዛፍ በላ። በዚህም ጊዜ አላዋቂ ሆነ። ከዚህ በኋላም ሰው ከእግዚአብሔር ሌላ ዕውቀትን በመፈለጉ በአላዋቂነት ላይ አላዋቂነትን እየጨመረ መጣ።

ምንም እንኳ የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ቢሆንም ዛሬ በዓለማችን ብዙ የተማሩና አዋቂ ሰዎች ይገኝሉ። ቅዱስ አውግስጢን በዚህኛው መንገድ ለረጅም ጊዜ ገተጓዘና እግዚአብሔርን በውጪ ሲፈልገው ቆይቶ ካጣው በኋላ በመጨረሻ እርሱ በወደደ ሊገለጥለት ይህን ዘልኣለማዊ ቅኔ ተቀኝቶለታል ።

"የወደድኩህ በጣም ዘግይቼ ነው። ቀዳማዊ ብትሆንም ምንጊዜም አዲስ ነህ። የወደድኩህ በጣም ዘግይቼ ነው አንተ በእኔ ውስጥ እያለህ እኔ በውጪ ሆኜ እፈልግህ ነበረ። አንተ በፈጠርከውና ባሳመንከው ውስጥ ሁሉ ያለማስተዋል እባዝን ነበር። በዚህ ሁሉ ጊዜ ግን አንተ ከእኔ ጋር ነበርህ እኔ ግን ከአንተ ጋር አልነበርኩም ። "

ከዚህ በኋላ ቅዱስ አውግስጢን እግዚአብሔር በውስጡ ሲያገኝው ከጻድቃን ወገን ሆነ።

"እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በርካሽ ዋጋ ያውም በሠላሳ ብር ብቻ ተሸጠ። ነገር ግን ዓለምን በውድ ዋጋ በከበረ ደሙ ገዛ፡"

- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ

" ጨዋ ሰው በሌሎች ሰዎች መሳሳቆል ላይ የራሱን ምኞት አይገነባም እርሱ የሌሎችን ሰዎች ምኞት ለማደላደል የራሱን ምኞት ይረሳልና "

- አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

ሰላም ለሁላችሁ እግዚአብሔር እንደ ሰው አይደለም። አብርሃም ሳይፈቀድለት ከገረዱ ልጅ ወልዶ ነበር፣ ያዕቆብ አታላይ ነበር፣ ሶምሶን በሴት ጸጋውን ጥሎ ነበር፣ ጌድዎን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የለም ብሎ ነበር። ዳዊት የሰው ሚስት ቀምቶ ባሏን አስገድሎ ነበር፣ ኢሳይያስ ለምጻም ነበር፣ ዮናስ እግዜርን እምቢ ብሎ ነበር። ካህኑ ዘካርያስ ሽማግሌ አይወልድም ብሎ ነበር። ጴጥሮስ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ክዶ ነበር። ጳውሎስ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነበር።ሰው ሁሉ ከድካሙ ጋ ነበር።ዛሬም ከድካሙ ጋ ያመልከዋል። የሰማይ አምላክ ግን ለዘለዓለም ከምህረቱና ከፀጋው ጋር አለ። ስሙ ምስጉን ይሁን።

□□ቀሲስ አሸናፊ ገ/ማርያም□□

እግዚአብሔርን የሚወድ እና በእግዚአብሔር የሚወደድ #መንፈሳዊ_ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው ። በምንም ሁኔታ ይሁን በምንም እግዚአብሔር በእርግጠኝነት እንደሚሰራለት ይሰማዋል በእርሱም ስራ ይደሰታል ። በእርግጥም እግዚአብሔር ሥራውን ባናየውም እንኳ ይሠራል ። ሥራውን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ልናየው እንችላለን በዚህም እንደሰታለን ። ይህን ደስታችንም

ማንም አይወስድብንም ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚደሰቱት በስጦታዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሱ በጌታም ነው ።

- አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

†ወደ ላቀ ክብር መሸጋገርህን የሚያረጋግጥልህ ብርሃናዊ አክሊል ያለው በድካምህ ሥር ነው። ስለሆነም በመንፈሳዊ ቡራኬ የታጀበውን ክርስቲያናዊ ቀንበር በማጉረምረምና በተቃውሞ አትሸከመው።

#አቡነ_ሺኖዳ_፫

" ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና"

፪ቆሮ ፲፪

የቅርብ ወዳጅ ስለነበሩ ሐዘኑ የጋራችን ነው" ሲል ፍቅራቸውን በእንባ ገልጧል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ብእራቸውን ያልሰቀሉ የሃይማኖት ደራሲ (ጸሐፊ)፤ ገዳማትን ያስፋፉ ለመናንያን አርአያ የሆኑ ባህታዊ (መነኮስ)፤ ቤተሰባዊ ችግሮችን በመፍታት የታወቁ መካሪ፤ መንጋውን ተግተው የመገቡ መሪ (እረኛ)፤ በደሙ በዋጃት ቤተክርስቲያን ላይ አለቃ አድርጎ የሾማቸውን ያልዘነጉ ጳጳስ፤ የእስክንድርያን ቤተክርስቲያንን እንደዋርካ ያሰፉና ቅዱስ ሲኖዶሷን በምሁራን ያደራጁ ፓትርያርክ ናቸው። የብእራቸው አሻራ ድንበር ተሻግሯል። በመላው ዓለም ብዙ ወዳጆች እና አድናቂዎች አሉአቸው። በሥጋ ሲለዩን ሚልዮኖችን አስነብተዋል። ግብጻውያን ብቻ አይደሉም የሚያውቋቸው ሁሉ አዝነዋል።

- እኛስ ምን ሠርተን እናንቀላፋ ይሆን? ወደ መቃብር ሳንወርድ ለወገን ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር መልካም ሥራ እንሥራ። የብፁዕነታቸው በረከት አይለየን! አሜን!!!

✨ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ 117ኛው የግብጽ ፓትርያርክ።✨

፡ዓርብ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ድል በነሳበት በመስቀሉ ፍቅር በገዛን ዕለት በእኛ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በዕለተ ዓርብ ሐምሌ 27 ቀን 1915 ዓ.ም. እንደ ኮፕቲኮች አቆጣጠር ደግሞ በዕለተ ዓርብ (አቢብ 27 ቀን 1639 ዓመተ ሰማዕታት) እ.ኤ.አ. ኦገስት 3 1923 ዓ.ም. በላዕላይ ግብጽ አስዩት አብኑብ በተባለ ቦታ የኮፕቲክ ብርሃን የሊቀ ዲያቆናት ሐቢብ ጊዮርጊስ ፍሬ ለቤተሰቦቻቸው 8ኛው እና የመጨረሻው ልጅ ሆነው ተወለዱ።

ወላጆቻቸው የሰጧቸው ስም ናዚር ጋዪድ የሚል ነበር። ገና በተወለዱ በጥቂት ቀናት ውስጥ እናታቸውን ያጡት አቡነ ሺኖዳ ከአምስት እኅቶቻቸው እና ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር

ቀሩ። ከልጅነታቸው ጀምረው በጣም የተረጋጉ እና አስተዋይ ነበሩ። የመጀመርያውን ትምህርት በዳማንሁር ባንሐ ካይሮ የተከታተሉ ሲሆኑ፤ ከካይሮ ዩኒቨርሲቲ የመጀመርያ ዲግሪያቸውን በታሪክ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወሰዱ። ከዚያም ከኮፕቲክ ሴሚናሪ በነገረ መለኮት የመጀመረያ ዲግሪ አግኝተው በዚያው ሴሚናሪ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መምህር ሆኑ።

- የግብጽ ቤተ ክርስቲያንን ከድካም ያበረታት ሐቢብ ጊዮርጊስ የሰንበት ት ቤቶችን እንቅስቃሴ ሲጀምር ዋናው የተልዕኮው አንቀሳቃሽ አቡነ ሺኖዳ ነበሩ። እርሳቸው በዚያ ወቅት የኮፕቲክ ወጣቶች ጎብረትን መሠረቱ። ለሰንበት ት/ቤቶች መጽሔቶች የተለያዩ ጽሑፎችን በማበርከት ወጣቱን ያበረቱት ነበር። በኋላ ዘመን የመንፈስ አርነት ተብሎ የታተመው መጽሐፋቸው የእነዚህ መጣጥፎች ስብስብ ነው። በሐምሌ 18 ቀን 1954 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በዋዲ ኤል ናትሩን ወደሚገኘው የሶርያውያን ገዳም

ገብተው በአቡነ ቴዎፍሎስ እጅ ምንኩስና በመቀበል አባ እንጦንስ አል ሱሪኒ ተባሉ። (ክርስቲያኖች ያሳደጉት ልጃቸው የአባቶቹን መንገድ ስለተከተለ ስሙም ስለተለወጠ አባ ብለው በአክብሮት መጥራት በመስቀላቸው መባረክ ጀመሩ።) ገዳማውያኑም የቤተ መጽሐፍት ኃላፊ አድርገው ሾሟቸው። በዚያ ገዳም ሺኖዳ አያሌ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ማንበባቸው ይነገራል። በመነኮሱ በዓመታቸው ክህነት ተቀብለው ቄስ ሆኑ። ከምንም በላይ ለምንኩስና እና ለምናኔ ሕይወት ልዩ ትኩረት ስለነበራቸው ለብዙ ዓመታት የኖሩትም በተባሕትዎ ነበር። መጀመርያ ከገዳሙ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ አንድ ዋሻ ውስጥ ተቀመጡ፤ በመቀጠልም ከገዳሙ ዐሥር ኪሎ ሜትር ወደሚርቅ እና በባሕር አል ፋሪግ፡ወደሚገኝ ዋሻ ገብተው ተጋድሎአቸውን ቀጠሉ። ባሕታዊው የተሰኘውንና በኋላ እ.ኤ.አ. በ1954 የታተመውን ቅኔያቸውን የጻፉት በዚህ ጊዜ ነበር።

- በ1959 እ.ኤ.አ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ ልዩ ጸሐፊያቸው፡አድርገው ሾሟቸው። አቡነ ሺኖዳ ግን ደስተኛ አልነበሩም። ከገዳማቸው መውጣት እና ባዕታቸውን መልቀቅ አያስደስታቸውም ነበርና። ብዙ ጊዜያቸውንም የሚያሳልፉት በዋሻቸው ውስጥ በጸሎት እና ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ነበር። ለብዙ ጊዜያትም ወደ ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይጠሩ ሲከላከሉ ኖረዋል።

- በ1962 እ.ኤ.አ. አቡነ ሺኖዳ በነበሩበት ገዳም ውስጥ አንድ አስተዳደራዊ ችግር ተፈጠረ። ጉዳዩም ወደ ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ ዘንድ ቀረበ። በዚያ ጊዜ ሺኖዳ በገዳሙ አስተዳደር ውስጥ ነበሩበት። ገዳማውያኑ እንደ ጥንቱ አበው ሆነው እንዲኖሩ፣ ገዳማት የችግር ቦታዎች ሳይሆኑ የጸሎት ቦታዎች እንዲሆኑ፤ የግብጽ ገዳማት አዲሱን ትውልድ ለመቀበል በሚችሉበት መንገድ እንዲደራጁ፤ ገዳማውያኑ ሥራ፣ ጸሎት እና ትምህርትን አጣምረው እንዲይዙ ይታገሉ ነበር። ይህ የአቡነ ሺኖዳ ሐሳብ ያልተስማማቸው አንዳንድ ገዳማውያንም አቡነ ሺኖዳን ከሰው ('ሰ' ጠብቆ ይነበብ) ወደ አቡነ ቄርሎስ ዘንድ አቀረቧቸው። አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ አቡ ሺኖዳን አስጠሯቸው። አቡነ ሺኖዳ በቄርሎስ እግር ሥር ተደፍተው "አጥፍቻለሁ፣ ድሮም ኃላፊነቱን የተቀበልኩት ያለ አቅሜ ነው። እባክዎ ከኃላፊነት ያንሱኝና በዋሻዬ ብቻ ተወስኜ ልኑር። እኔ ደካማ ሰው ነኝና" ብለው ለመኗቸው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ

ቄርሎስም "ዛሬ እንደርና ነገ ውሳኔዬን አሳውቃለሁ" አሉ። በማግሥቱ መስከረም 30 ቀን 1962 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ፓትርያርክ ቄርሎስ እና ሌሎች ጳጳሳት የአቡነ ሺኖዳን ጉዳይ ለማየት በመንበረ ፓትርያርኩ ተሰባሰቡ። አቡነ ሺኖዳ ውሳኔውን በጉጉት ነበር የጠበቁት። ኃላፊነት ከሚባለው ነገር ተገላግለው የምናኔ ሕይወታቸውን ብቻ ለመያዝ ፈልገዋል። አባታችን ተጠሩ፤ ጳጳሳቱ ቆሙ። ሁሉም ቄርሎስን ያይ ነበር። አቡነ ሺኖዳ እንዲንበረከኩ

ተነገራቸው። ተንበረከኩ። ፓትርያርኩ ቄርሎስም እጃቸውን በአቡነ ሺኖዳ ላይ ጫኑ። ሌሎች ጳጳሳትም ወደ እርሳቸው መጡ። ሳይታሰብ አቡነ ሺኖዳ ተብለው የግብጽ የመንፈሳውያን ኮሌጆች እና የትምህርት ተቋማት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ። አቡነ ሺኖዳ ደነገጡ። አለቀሱም። በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥናት በማድረግ የታወቀው የካይሮ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሩ ጀርመናዊው ኦቶአ ሜናድረስ የአቡነ ሺኖዳን መሾም ሲሰማ 'እንኳን ደስ አልዎት!' የሚል ደብዳቤ ላከላቸው። እሳቸው ግን የመለሱለት መልስ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እና ሰላም ካንተ ጋር ይሁን። 'እንኳን ደስ አልዎት!' ብለህ በቅንነት ስለላክህልኝ መልእክት አመሰግንሃለሁ! ያንተን ወዳጅነት እና ፍቅር መቼም አልዘነጋውም። እውነቱን ለመናገር ግን ለእኔ መላክ ያለበት የሀዘን ደብዳቤ እንጂ የደስታ ደብዳቤ አይደለም። አንድ መነኩሴ ፀጥታ የተሞላበትን የጸሎት በረሃ ለቅቆ ጫጫታ እና ሁካታ በተሞላበት ከተማ እንዲኖር ሲደረግ እንዴት 'እንኳን ደስ ያለህ' ይባላል? ማርያምን ከክርስቶስ እግር ሥር ተነሥታ ማርታን ልታግዝ ወደ ጓዳ ስትገባ ማነው እንኳን ደስ ያለሽ የሚላት? ለእኔ ይህ ደስታ ሳይሆን ሀፍረት ነው። እኔ ኤጲስ ቆጶስ ሆኜ የተሾምኩበትን ቀን በደስታ ሳይሆን በሀዘን እና በለቅሶ ነው የማስታውሰው። ብሕትውና እና የተጋድሎ ጸሎት ከምንም በላይ የሚበልጥ ነገር ነው። ብሕትውና እና ምናኔ ከኤጲስ ቆጶስነት ቀርቶ ከፓትርያርክነት ጋር እንኳን የሚወዳደር አይደለም። "ወዳጄ ሆይ! እውነተኛው ቅድስና ሲመት ሳይሆን ልብን ቤተ መቅደስ አድርጎ ለክርስቶስ መቀደስ ነው። ክርስቶስ በመጨረሻው ቀን የልባችንን ንጽሕና እንጂ የክህነታችንን መዓርግ አይጠይቀንም። ይህንን ደብዳቤ የምጽፍልህ በምወድዳት ዋሻዬ፣ በባሕር አል ፋሬግ፣ በዋዲ ኤል ናትሩን ውስጥ ሆኜ ነው። እዚህም እስከ ጥምቀት ድረስ ለመቆየት አስባለሁ። ከዚያም ወደ ካይሮ እመለሳለሁ።"

- አቡነ ሺኖዳ እያለቀሱ ያቺን የዋዲ ኤል ናትሩን ዋሻ ትተው ካይሮ ቢመጡም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወደ ዋሻቸው መሄድ ያዘወትሩ እንደ ነበር ታሪካቸውን የጻፈላቸው የቅርብ ወዳጃቸው እና በእምነቱ ፕሮቴስታንት የነበረው ኦቶአ ሜናድረስ ሳይቀር ይመሰክራል። እስከ 1969 እ.ኤ.አ. ድረስ የቤተ ክርስቲያኒቱን የትምህርት ተቋማት በዘመናዊ መልኩ አደራጅቻው። በዚህ የተነሣም በሙሉ ጊዜያቸው የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከአንድ መቶ ወደ 207 አደገ። አቡነ ሺኖዳም በየሳምንቱ ዓርብ ዓርብ ሕዝቡን የሚያስተምሩበት እና የሕዝቡን ጥያቄዎች የሚመልሱበት የትምህርት መርሐ ግብር ከፈቱ። እስከ አሥር ሺ የሚጠጋ ሕዝብም መርሐ ግብሩን ይከታተለው ነበር። ለሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሆኑ መጻሕፍትን፣ መዝሙሮችን እና ትምህርቶችን ያዘጋጁ

ነበር። የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራንንም ያሠለጥኑ ነበር። በዚህ የሥራ ብዛት ውስጥ እያሉ እንኳን የሳምንቱን ግማሽ በካይሮ ቀሪውን ደግሞ በገዳማቸው ዋሻ ውስጥ ያሳልፉ ነበር።

በዚሁ ዓመት አቡነ ሺኖዳ የመካከለኛው ምሥራቅ የነገረ መለኮት ተቋማት ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ። ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሌሎቹ ጋር የማቀራረቡን ሥራ የጀመሩት ገና በጳጳስነታቸው ዘመን ነው። በእርሳቸው መሪነት ቤተ ክርስቲያኒቱ በኢያሌ የነገረ መለኮት ውይይቶች ላይ ተሳትፋለች።

- ፓርትያርክ ቄርሎስ በመጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም. ዐረፉ። በመጋቢት 22የተሰበሰበው የግብጽ ሲኖዶስም ተተኪውን ለመምረጥ ዝግጅት ጀመረ። አምስት እጩዎችንም መረጠ። ነገር ግን በመካከሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ኢያሌ ፈተናዎች ገጠሟት። በዚህም ምክንያት ፓትርያርክ ሳይመረጠ ረዥም ጊዜ ቆየ። በጥቅምት 29 ቀን የተሰበሰበው ቅዱስ ሲኖዶስ የእጩዎችን ቁጥር ወደ ሦስት ዝቅ አደረገው። የሦስቱም እጩዎች ስም በመንበረ ማርቆስ ካቴድራል መንበር ላይ ተቀመጠ። ሕዝቡ እና ገዳማውያኑም ለሦስት ቀን ሱባኤ ያዙ።

- ጥቅምት 31 ቀን 1971 እ.ኤ.አ. በዕለተ ሰንበት ሕዝቡ፣ ካህናቱ፣ ገዳማውያኑ እና ጳጳሳቱ በተገኙበት ጸሎት ከደረሰ በኋላ አንድ ዓይኑን በሻሽ ለተሸፈነ ዐይማን ሙኒር ካሊል የተባለ ሕፃን በመንበሩ ላይ የተጸለየባቸው ስሞች ቀረቡለት። እጁን ዘርግቶ አንዱን ዕጣ አወጣው። በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኒቱን በጊዜያዊነት ይመራ የነበረው ኮሚቴ ሊቀ መንበር ለሆኑት ለሜትሮፖሊጣን አንቶኒዮስም ሰጣቸው። ወረቀቱን ዘረጉት። "እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን አባት ይሆኑ ዘንድ አቡነ ሺኖዳን መርጧል" ሲሉ አካባቢው በጭብጨባ እና በእልልታ ተናጋ።

- ከሁለት ሳምንት በኋላ ኅዳር 14 ቀን 1971 እ.ኤ.አ. በቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል፣ ሺኖዳ 3ኛ 117ኛው የግብጽ ፓትርያርክ ተብለው ተሾሙ። በእሳቸው ዘመን ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደገና ኃይል አገኘች። ያኔም በነገረ መለኮት ኮሌጅ

ያስተምራሉ። የኮሌጁ ዲንም ነበሩ። የኤልኬራዛ መጽሔትም አዘጋጅ ናቸው። ዓርብ ዓርብ ያስተምራሉ። ገዳማትን እና ትምህርት ቤቶችን አስፋፉ። ወጣቱን ወደ አገልግሎት ጠሩ።

እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስም በፓትርያርክነታቸው ዘመን በአባ ቢሾይ ገዳም የሳምንቱን ግማሽ በገዳማዊ ሕይወት ማሳለፋቸውን አልተውም። መጻሕፍትን ይጽፋሉ። በውጭ እና በሀገር ውስጥ ያለውን ሕዝብ ይጎበኛሉ። እርሳቸው ሲሾሙ በውጭ ያሉት አጥቢያዎች ሰባት ብቻ ነበሩ። ከተሾሙ በኋላ ግን በአሜሪካ እና ካናዳ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት እንኳ ከሰማንያ በላይ አድርሰዋቸዋል። በአውስትራልያ ከ26፣ በአውሮፓ ከ30 በላይ አጥቢያዎች ይገኛሉ።

- አቡነ ሺኖዳ ለአቋማቸው እና ለእምነታቸው ሲሉ ስደትን የቀመሱ ፓትርያርክ ነበሩ። አንዋር ሳዳት የግብጽ መሪ በነበረ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኒቱ እና በምእመናኗ ላይ የሚደርሰውን መከራ በመቃወም አቡነ ሺኖዳ ደጋግመው ይናገሩ ነበር። በዚህ ያልተደሰተው ሳዳት መስከረም 3 ቀን 1981 እ.ኤ.አ. ባወጣው ዐዋጅ አቡነ ሺኖዳን ከመንበራቸው አሳደዳቸው። በግዞትም ወደ አባ ብሶይ ገዳም ተላኩ። ሕዝቡ ሌላ አባት አንመርጥም ብሎ ተከትሏቸው አባ ብሶይ ገዳም ገባ። እዚያም በሚወዱት ገዳም ተጋድሏቸውን እና ትምህርታቸውን ቀጠሉ።

በገዳሙ በግዞት ለአራት ዓመት ተኩል ከቆዩ በኋላ ሳዳት ሞቶ ሙባረክ ሲተካ በጥር 2 ቀን 1985 እ.ኤ.አ. ወደ መንበራቸው ተመለሱ።

- አቡነ ሺኖዳ ቀልድ አዋቂ ናቸው። በተለይ ሕፃናትን ማስተማር ይችሉበታል። ሕዝቡን ሲያስተምሩም አስተማሪ ቀልድ እና ታሪክ ጣል ያደርጋሉ። ሴቶች በቤተ ክርስቲያን የነበራቸውን የአገልግሎት ተሳትፎ በማሳደግም ከፍተኛ ለውጥ አምጥተዋል። ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር ልክ የለውም። "በልባችን ውስጥ ያለችው ግብፅ ከምናያት ግብፅ ትበልጣለች" የሚለው አባባላቸው በግብፃውያን ልብ ለዘለዓለም ታትሞ ቀርቷል።

- ክርስቲያን እና ሙስሊሙ ሕዝብ ተከባብሮ እና ተባብሮ እንዲኖር በብርቱ ጥረዋል። በአርባ ዓመት አገልግሎታቸው ከ120 በላይ መጻሕፍትን ጽፈዋል። ንግግር ዐዋቂ፣ ባለ ቅኔ፣ ሰባኪ እና ደራሲ ናቸው። አባታችን በሙስሊሞች፣ በፕሮቴስታንቶች እና በካቶሊኮች ዘንድ የሚወደዱ እና የሚከበሩ አባት ናቸው።

- የታላቁ የአልአዝሐር መስጊድ ኢማም የፖፕ ሺኖዳን ሞት ተከትሎ "ግብፅ እኒህን ጥበበኛ ሰው በምትፈልግበት ወሳኝ ጊዜ እርሳቸውን ማጣታችን የሚያንገበግብ ነው" ነበር ያሉት። ዜና ሞታቸው ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም የጎዳ ነው። ተወዶ የሚኖርና ተለቅሶለት የሚቀበር የሃይማኖት መሪ በዓለም ላይ እየጠፋ ባለበት በዚህ ጊዜ አቡነ ሺኖዳ በሕይወታቸውም በሞታቸውም ያስተማሩ አባት ሆነዋል።
- በህክምና ሲረዱ ቆይተው መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. ዐረፉ። በሚወዱት በአባ ብሾይ ገዳምም ተቀበሩ።

☞ መጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በመንበረ ማርቆስ 117ኛው የእስክንድርያ ፖፕ (ፓትርያርክ) ሆነው ከተሾሙበት በሞት እስከተለዩበት እስከ መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. (17/03/2012 እ.ኤ.አ) ድረስ ለ41 ዓመታት በፓትርያርክነት አገልግለዋል።

☞ ለ7 ዓመታት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል።

☞ የአገራቸው፣ የአሜሪካንና የጀርመን ዩኒቨርስቲዎች አምስት የክብር ዶክትሬት ሰጥተዋቸዋል።

☞ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስን በዘመናዊ መልክ አደራጅተዋል።

☞ በ1985 ዓ.ም. ዓላማ እና ፖሊሲዎችን ያቀፈ የሲኖዶስ ውስጠ ደንብ አጽድቀዋል። በአሁኑ ወቅት ቅዱስ ሲኖዶሱ 90 ሜትሮፖሊታኖች እና ጳጳሳት አባላት አሉት።

☞ ከግብጽ ውጪ 150 አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል።

☞ ከግብጽ ውጪ 8 ገዳማትን በአፍሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ መስርተዋል።

☞ የነገረ መለኮት ኮሌጆችን ቁጥር ወደ 11 ከፍ አድርገዋል። የድኅረ ምረቃ ተቋምም አቋቁመዋል።

☞ ከ120 በላይ የሚሆኑ የእምነትና የሥነ ምግባር መጻሕፍትን ጽፈዋል በዚህም ምክንያት "የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዮሐንስ አፈወርቅ" ተብለዋል። ከ50 በላይ የሚሆኑትም በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመዋል።

☞ የዓለም፣ የአፍሪካ እና የመካከለኛው ምስራቅ አብያተክርስቲያናት ምክር ቤቶችን አጠናክረዋል።

☞ 300 መነኮሳት 150 መነኮሳይያትን አመልኩሰዋል።

☞ 96 ጳጳሳትን ከ600 የሚበልጡ ካህናትን ሹመዋል።

☞ ቅዳሴአቸውን በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በጀርመንኛ፣ በኢጣልያንኛ፣ በስዋሊና በደቡብ አፍሪካ ቋንቋዎች እንዲተረጎም አድርገዋል።

☞ ምእመናን በቤተክርስቲያን አስተዳደርና ማኅበራዊ ጉዳይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አድርገዋል። ቁጥራቸውንም 12 ሚልዮን አድርሰዋል።

☞ ሀገራችን ኢትዮጵያንም ሁለት ጊዜ ጎብኝተዋል። (በንጉሥ ኃ/ሥላሴ ግብዣ

መስከረም 15 ቀን 1966 ዓ.ም እና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ጋባዥነት ሚያዝያ 3 እስከ 5 ቀን 2000 ዓ.ም)

☞ በሞት እስከተለዩበት እስከ መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም (17/03/ 2012 እ.ኤ.አ) ድረስ ለ41 ዓመታት በፓትርያርክነት አገልግለዋል። ቤተክርስቲያንን በብዙ ጸጋ ያገለገሉ ብፁዕ ወቅዱስ ፖፕ ሺኖዳ ሣልሳዊ በተወለዱ በ88 ዓመታቸው መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በዕለተ ቅዳሜ አርፈዋል።

☞ እረፍታቸውን ተከትሎ የዓለም የመረጃ መረቦች ስለበጎነታቸውና ሥራቸው ብዙ ዘግበዋል። ቢቢሲ ከካንሰር ጋር እንደኖሩ መረጃ ሰጥቷል። የቅርብ አማካሪያቸው እና አዚዝ ደግሞ "የሰነበተ ህመም አባታችንን ነጠቀን" በማለት ገልጧል። ከግብጻውያን አስተያየት ሰጪዎች አንዱ "የክርስቲያኑ የሙስሊሙም የቅርብ ወዳጅ ስለነበሩ ሐዘኑ የጋራችን ነው" ሲል ፍቅራቸውን በእንባ ገልጧል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ብእራቸውን ያልሰቀሉ የሃይማኖት ደራሲ (ጸሐፊ)፤ ገዳማትን ያስፋፉ ለመናንያን አርአያ የሆኑ ባህታዊ (መነኮስ)፤ ቤተሰባዊ ችግሮችን በመፍታት የታወቁ መካሪ፤ መንጋውን ተግተው የመገቡ መሪ (እረኛ)፤ በደሙ በዋጃት ቤተክርስቲያን ላይ አለቃ አድርጎ የሾማቸውን ያልዘነጉ ጳጳስ፤ የእስክንድርያን ቤተክርስቲያንን እንደዋርካ ያሰፉና ቅዱስ ሲኖዶሷን በምሁራን ያደራጁ ፓትርያርክ ናቸው። የብእራቸው አሻራ ድንበር ተሻግሯል። በመላው ዓለም ብዙ ወዳጆች እና አድናቂዎች አሉአቸው። በሥጋ ሲለዩን ሚልዮኖችን አስነብተዋል። ግብጻውያን ብቻ አይደሉም የሚያውቋቸው ሁሉ አዝነዋል።

- እኛስ ምን ሠርተን እናንቀላፋ ይሆን? ወደ መቃብር ሳንወርድ ለወገን ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር መልካም ሥራ እንሥራ። የብፁዕነታቸው በረከት አይለየን! አሜን!!!

<u>አቡነ ሺኖዳ ካስተማሩት</u>

- "አባት ሆይ ይቅር በላቸው" ብለህ ስለ ሌሎች ብትማልል ለዚህ በርህራሄ ለተሞላው ተማፅኖህ "ልጄ ሆይ አንተንም ይቅር እልሃለሁ" የሚል ምላሽ ታገኛለህ።ስለዚህ ለራስህ ይቅርታ ማግኘትን በጽኑ የምትሻ ከሆነ ለሌሎች የምታደርገው ይቅርታ ዋስትና ይሆንልሃል። ይቅርታ ባደረክ ቁጥር በልብህ የሚሰማህ ሞቃ ያለ ደስታ ለዚህ በቂ ማሳያ ነው።
- ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔርን ማክበር የማያቋርጥ ግባችን ልናደርግ ይገባል ።
- በዚህ ግባችን ላይ የምናተኩር ከሆነ ወደዚህ የሚያደርሱንን ምክንያቶች እንፈልጋለን ። ከዚህ በተጨማሪ እኛ እግዚአብሔርን ካከበርነው እርሱም እኛን እንደሚያከብረን እናውቃለን ። እግዚአብሔር ከራሱ የሆነውን ክብር ለፍጥረቱ በመስጠት ማክበሩ ምንኛ ድንቅ ነገር ነው! ይሕ እንደምን ያለ ትሕትና ነው?
- †□ እግዚአብሔር ድካምህን እንደሚያውቅና እስካሁን ድረስም እንደሚወድህ እርግጠኛ ሁን ! በኃጢአት ውስጥ ብትሆንም እግዚአብሔር ሊያድንህ ወደ እርሱ ሊያቀርብህና ወደ ቀደመ ደረጃህ ሊመልስህ እንደሚሰራ እመን ። አዳም የዳነው ንሥሐ ለመግባት ባደረገው ሙከራ ሳይሆን #አዳምን_በተመለከተው_የእግዚአብሔር_ቸርነት_ነው ።
- †□ ድንግል ማርያም በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ሴቶች ሁሉ መካከል በእግዚአብሔር ስለ ተመረጠች ክብሯ እጅግ ታላቅና ብሩኅ ነው ።
- በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዘመናት የተጠበቀች ብቸኛ የሰው ዘር ድንግል ማርያም ብቻ ናት ። ከተመረጠች በኋላም እጅግ ታላቅ ክብር ይገባት ስለ ነበር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዲህ በማለት አወድሷታል። "...መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ። ሉቃ 1*35
- እኛ እያንዳንዱ የተቆለፈ በር ሺህ መክፈቻ ቁልፎች አሉት ብለን እንናገራለን ። እግዚአብሔር ግን ሁሉንም የተዘጉ ደጃፎች ወይም መዝጊያዎች መክፈት ይችላል ። ሁሉም ጨለማ በብርሃን ይተካል እያንዳንዱ ጥያቄም መፍትሄ ወይም መፍትሔዎች ይኖሩታል ። እግዚአብሔር እያንዳንዱን መከራ መቆጣጠር ይቻለዋል ከመራራው ጣፋጭን ከበላተኛውም የሚበላ ማውጣት የሚቻለው እግዚአብሔር ለችግሮቻችን በሙሉ መፍትሔ አለው ።
- እግዚአብሔርን የሚወድ እና በእግዚአብሔር የሚወደድ #መንፈሳዊ_ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው ። በምንም ሁኔታ ይሁን በምንም እግዚአብሔር በእርግጠኝነት እንደሚሰራለት ይሰማዋል በእርሱም ስራ ይደሰታል ። በእርግጥም እግዚአብሔር ሥራውን ባናየውም እንኳ ይሠራል ። ሥራውን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ልናየው እንችላለን በዚህም እንደሰታለን ። ይህን ደስታችንም ማንም አይወስድብንም ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚደሰቱት በስጦታዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሱ በጌታም ነው ።

- እግዚአብሔርን የሚወድ እና በእግዚአብሔር የሚወደድ #መንፈሳዊ_ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው ። በምንም ሁኔታ ይሁን በምንም እግዚአብሔር በእርግጠኝነት እንደሚሰራለት ይሰማዋል በእርሱም ስራ ይደሰታል ። በእርግጥም እግዚአብሔር ሥራውን ባናየውም እንኳ ይሠራል ። ሥራውን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ልናየው እንችላለን በዚህም እንደሰታለን ። ይህን ደስታችንም ማንም አይወስድብንም ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚደሰቱት በስጦታዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሱ በጌታም ነው ።
- ክርስትና ለተቀጠቀጠው ሸንበቆና ለሚጨሰው ጧፍ ተስፋ ሰጥቷል።እግዚአብሔር የተቀጠቀጠ ሸንበቆን ሰብስቦ በአንድ ለማሰርና የሚጨስ ጧፍን ለማቀጣጠል አይሳነውም።ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለሰዎች ተስፋን ይሰጥ ዘንድ "የደከሙትን እጆች አበርቱ" (ኢሳ.35:3) በማለት ተናግሯል።ይህን በማለቱም ለደከሙት እጆችና ለላሉት ጉልበቶች ተስፋ ሰጥቷል።
- በክርስትና ተስፋ የተሰጠው ለሁሉም ነው።ለግለሰቦች : ለተቋሞች : ለአብያተ ክርስቲያናት : ለሀገሮችና ለመላው ዓለም ነው።እግዚአብሔር በማንኛውም ዘመን ሰውን ስለሚፈልገው በዚህ ሁላችንም ተስፋ አለን።ይህ በአማኞች ዘንድ ያለ ተስፋ ነገሮች ቢወሳሰቡና ከባድ ቢመስሉም እንኳ በጭራሽ አይላላም።

  □ነቢዩ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ተስፋ ነበረው። (ዮና. 2:5)

  □የማይድን በሽታን በማዳን ውስጥ ተስፋ አለ። (ዮሐ. 5:8)

  □ልጅ ባለመውለድ ውስጥ ተስፋ አለ።(ኢሳ. 54:1-3)

  □ነገሮች ከባድ የማይቻሉና አስቸጋሪ ቢመስሉም እንኳን ከእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች አሉን። (ማር. 10:27 ; 9:23 ፊልጵ.4:13)

  □በክርስትና ተስፋ ወሰን ስለሌለው አንድ ክርስቲያን በችግር በመከራና በጭንቅ ውስጥ ወድቆ ወይም ለፈተናዎቹ መፍትሔ ያጣላቸው ሲመስል የተስፋ ጸጋ እንዳለውና እንደሌለው ለማወቅ ራሱን ይፈትሻል።በዚህ ጊዜ በተስፋው ውስጥ እግዚአብሔር ለችግሮቹ ሁሉ ብዙ መፍትሔዎች እንዳሉትና ሰዎች ዘግይቷል ብለው በሚያስቡበት ሰዓት በእርግጥ እንደሚመጣ ይታወቀዋል።
- በሕይወት ካሉት ጋር ጎብረት እንዳለን ሁሉ በሞት ከተለዩት ጋርም ጎብረት አለን !!ሞት ከሌሎቹ የክርስቶስ ብልቶች ጋር አይለየንም እነርሱን በግልና በጉባኤ ጸሎታችን ውስጥ እናስባቸዋለንና ። እነርሱም በምድር ላይ የሚኖሩንን የቆይታ ቀናት በሰላም አጠናቀን ከእነርሱ ጋር እንድንገናኝ አጥብቀው ይጸልዩልናል ።ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የአማኞችን ጎብረት አስመልክቶ የተናገረው ቃል እንዲህ ይላል ፦ " ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን #ጎብረት_አለን ። የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል ። 1ኛ ዮሐ 1*7
- እምነት ባህርን ከፍሎ ያሻግራል፣በበረሃ መካከል ከሚገኝ ዓለትም ውኃ አፍልቆ ያጠጣል። በዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል የሚለው።
- "በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ እግዚአብሔርን ማንሣትና በችግር ውሥጥ ሥሙን መጥራት ተማር። በራሥህ ማስተዋል ተደግፈህ ችግሮችን ለመጋፈጥ አትሞክር። ከጓደኞችህ

ከወዳጆችህ አጠቃላይ ከሰው መፍትሄን አትጠብቅ። ምንም ምንም ቢሆን ያለ እግዚአብሔር መሥራት እንደማትችል የሚያረጋግጥ ሀሣብ በውሥጥህ ይኑር! ለችግሮችህ መፍትሄ ያለው ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ውሥጥ ብቻ ነው።እግዚአብሔር የማይፈታው ቋጠሮ የለም። ምንም እንኳን ለአንተ ችግሩ ቀጣይ ቢመሥልህ ወይም በመከራ ውሥጥ ብትሆን አሥፈላጊውን የልብ ጽናት እርሱ ይሠጥሀል።

- ከምን ዓይነት ነገር መላቀቅ እንዳለብህ ታዉቃለህ ??
- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ ምድራዊ ምኞት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነና እንዴት ከዚህ ነገር ነፃ መውጣት እንዳለብን እንዲህ በማለት ይመክሩናል፦
- ወዳጄ ከምድራዊ ምኞትህ ተላቀቅ ከምን አይነት ነገር መራቅ እንዳለብህ ታውቃለህ? ከምድራዊ ፍላጎት ከመሳሰሉት ራቅ ፍፁም የመንፈስ ነፃነት እንዲኖርህ ከፈለክ ከምድራዊ ምኞቶችህ ተላቀቅ።
- በእርጋታና በግልጽነት ላውጋህ እጅግ አብዝተህ የምትጨነቅባቸው ልብህን የተቆጣጠሩት ታላላቅ ምድራዊ ተስፋዎች አሉህ።
- እነኚህም ሃሳብህን ሁሉ ይቆጣጠሩታል ብቻህን በምቶንበት ጊዜ በምናብ ይመጡብሃል በምትተኛ ጊዜ ህልምህ ሁሉ ይህ ይሆናል ልትክዳቸው የማትችለው ነገር ግን የምታውቃቸው ምድራዊ አላማዎች አሉህ። ተፈላጊነት እንዲኖርህ ትመኛለህ፣ ስልጣን እንዲኖርህና፣ ኃያል እንድትሆን፣ ዕውቅና እንዲኖርህና ስምህ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እንዲናኝ ትፈልጋለህ።
- በሀብት፣ በምድራዊ ስልጣን፣ በዕውቀት በማዕረግና በመልክ ዝነኛ የመሆን ተስፋ አለህ ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በምግብ፣ በልብስና በሰውነት ደስታን በሚሰጡ ነገሮችም ተስፋ አለህ።
- ዓለም በአንተ እንጂ አንተ በዓለም እየኖርክ አይደለም። ስለዚህ አንተነትህ በዚህ ምድራዊ ተስፋ የታጠረ ነው። መንፈስህም ከስጋ ፍላጎቶች መራቅን ትመኛለች ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስ በሥጋ ላይ ይመኛልና። (ገላ.5፥17) እነዚህ ሥጋዊ ተስፋዎችና ፍላጎቶች ስኬታማ ስለማይሆኑ ግራ ትጋባለህ።
- ይህን በእርግጥ ቅሬታን ያመጣብሃል።
- እነዚህን ነገሮች ሁሉ ትናፍቃለህ ነገር ግን ናፍቆትህ አያስደስትህም። ስለዚህ ለምኞትህ ሁሉ ማስተካከያ ታበጅለት ይሆናል ምናልባትም ይጠቅሙኛል የምትላቸውን ሰዎች ማግኘት፣ በምኞትህ ዙሪያ የተጻፈ መዛግብት ማገላበጥ ትፈልግ ይሆናል በዚህም ላይ ታች ስትል ምኞትህን ለማሳካት ትታገላለህ እንዲሆን ሌላ ዘዴ ልትፈጥር ትችላለህ ይሁን እንጂ ሳይሳካልህ ቀርቶ በሃሳብና በጥረት ትታክታለህ ከዚያም ትበሳጫለህ። ከዚህ የከፋው ነገር በእነዚህ ምኞቶችና ተስፋዎች ስኬታማ አለመሆን ምክንያት ለከፋ ሕይወት መዳረግህ ነው።
- እንደምትሰለች አውቃለሁ አዘንኩልህ እስከመቼ ድርስ በምኞት ማዕበል ውስጥ ትኖራለህ? የምትመኘውን ባገኘህ ጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ ይህ ደስታ ስለማያረካህ ሌላ አዲስ ደስታን እንድትመኝ ያደርግሃል። ልክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል" (ዮሐ.4፥13) እንዳለው እርካታ አይኖርህም።

- ስለዚህ ውድ ወንድሜ ነገሩን በእርጋታ ከአንተ ጋር ለመነጋገር እፈልጋለሁ። "አለሙም ምኞቱም ያልፋል" (1ኛ ዮሐ.2፥17) ታዲያ ይህን ቃል ካወክ ለምን አለማዊ ፍላጎቶችን ለማግኘት ትታክታለህ? አንተ ልክ እንደ እኔ ለመሬት እንግዳ ነህ። ዓለም የሚያልፍበት አንተም የምትጠፋበት ጊዜ ይመጣል ልክ ከእናትህ ማህጸን ራቁትህን እንደመጣህ እንደዚሁ ራቁትህን ትመለሳለህ።(ኢዮ. 1፥21)
- ዓለምን ከነክብሯ ከነሀብቷና ከነስሟ ለቀሃት እንድትሄድ በመገደድ እንደ ማንኛውም ሰው ወደ መሬት ትወርዳለህ። ከዚያም ከዓለም ያገኘኸውን ደስታ ታወቂነት ወይም ምንም ይሁን ምን ሥጋህን ከሞት ሊከላከልልህ አልያም ሥጋን ከሚበሉት ትል ሊከላከልልህ አይችልም። በፍርድ ቀን ከዓለም ሀብትና ንብረት ውጭ በእግዚአብሔር ፊት ትቆማለህ። መልካም ይሁን ክፉ የሰራኸው ሥራ እንጂ የዓለም ቁሳዊ ነገር አይከተልህም።
- ስለዚህ ውድ ወንድሜ ምኞትህንና ተስፋህን በዓለም ላይ በማድረግ መታወክህ ለአንተ ጥሩ አይደለም ይህችን ምድር እሾህንና አሜኬላን እንዳበቀለችልህ ትዘነጋለህን!!! ከእኛ በፊት የነበሩና ምድርን ሊረግጧት የማይገባት የቅዳሳን አባቶችና እናቶች አሠራርና ፈለግ ተከተል ቅድስናቸውን ያገኙት ይህችን ዓለም በመውደድ ሳይሆን በመናቅ ነበር ሁኔታዎች ሁሉ ተመቻችተውላቸው ሳለ በዓለም ስላሉ ነገሮች ለማንኛውም ጉጉት አልነበራቸውም ።
- ውድ ወንድሜ አሁንም ምኞት አሉህ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና (ማቴ.6፥21) የሥጋን ምኞቶችን ስለተቆራኘ መንፈሳዊ ነገሮች በአንተ አመለካከት ዋጋቸውን ያጣሉ ይህ የክብር ጌታ እንደተፈተነው ዓይነት ፈተና ነው። (ማቴ.4፥8-9)
- አሁን አስተውል እነዚህን ነገሮችን ብትይዝ በጥሩ ምኞት ያላሰርካት ነፍስህን ብታጣ ጥቅሙ ምንድን ነው? ነፍስህ ነጻነትን ትሻለች።
- ከስጋ ምኞት ተላቀን የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን " የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።"(ገላ.5፥22) እንዳለው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን ገንዘብ አድርገን እንድንኖር እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን!!
- በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው ራሱንም ሌሎችንም ያከብራል።ከሌሎች አንፃር ግን ራሱን ከፍ አድርጎ አይመለከትም።
- በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው ፊፅሞ ሌሎችን አይገስፅም።በማንም ላይም አይቆጣም።
- በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው ሰዎችን ሳይገስፅና በማንም ላይ ሳይቆጣ ለእውነት ይቆማል።
- በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው ደካማነቱንና ኃጢአቱን ስለሚያውቅ ሌሎችን ያከብራል : ራሱንም እንዲሁ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለማክበር ብቻ ሳይሆን በእርግጥም እንደዚህ በማድረጉ ምኞት ስለሚሰማው በዕድሜና በደረጃ ከእርሱ የሚያንሱትን ሰዎች ያከብራል።
- በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው እራሱን በሌሎች ፊት ከፍ የሚያደርግ ልምዶችን አይናገርም።ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነቱን በምስጢር ይይዘዋል እንጂ ።
- በዚች ምድር ላይ ለማንም ያልተደረጉ ነገሮች ለእመቤታችን ቢደረጉላትም ስለተደረገላት ተአምርና ድንቅ ነገር ለማንም አትናገርም ነበር።የብዙ ልምዶችና የብዙ

ምስጢራት ሀብታም ነበረች። ነገር ግን "ይሄን ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር።" (ሉቃ. 2:51)

- ድንግል ማርያም በታላቅ ክብሯ ሴቶችን ሁሉ ትበልጣለች
- ይህ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እርሷ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል ፦ " መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ ።" ምሳ 31*29 በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ብዙ ሴቶች ክብር አግኝተዋል ሁሉም ያገኙት ክብር ግን ከአንች ክብር አይበልጥም ።
- ቅድስት ድንግል ከመጀመርያው አንስቶ በእግዚአብሔር ጎሊና እና ፈቃድ ስትታሰብ የኖረች እናት ናት ።
- አምላካችን እግዚአብሔር ለቀደሙ ወላጆቻችን በገባላቸው የድኃነት ቃል ኪዳን ውስጥ የሴቲቱን ዘር የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ገልጦአል ። ዘፍ 3*15
- የሴቲቱ የተባለው ለድንግል ማርያም ሲሆን ዘሯ የተባለው ደግሞ በመስቀል ላይ ሆኖ የእባቡን ራስ ለቀጠቀጠው ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።
- እናንተ ግን የተቀበላችሁትን ማንኛውንም ዓይነት በረከት ከእግዚአብሔር እንደተቀበላችሁት አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ከሰዎች ወይም በራሳችሁ እንዳገኛችሁት አድርጋችሁ አትቁጠሩ::
- ምክንያቱም የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው:ክፉ የተባሉ ነገሮች ሁሉ የሚመጡት ከእርሱ አይደለም::
- ይህን በማወቅ ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ልትደርሱ ትችላላችሁ::
- ላስደናቂው ነገር ግን እግዚአብሔር-እግዚአብሔር ነው:
- ስለሆነም እኛ የእርሱን ችሮታዎች ለሌሎች የምንሰጥ ውለታዎችም የማንክድና ችሮታዎቹን የማንረሳ ሰዎች ብንሆን እግዚአብሔር ለእኛ መልካም ማድረጉን ላያቋርጥም!ይህ በራሱ እርሱን ወደ መውደድ የሚጠራን ምክንያት አይደለምን?

□የተስፋ ሕይወት□

❀የተስፋ ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን : በስራው :ለሰዎች ሁሉ ባለው ፍቅሩና በድንቅ አሰራሩ መታመንን ይፈልጋል።ልቦናዎቻችን በተስፋ ይሞሉ ዘንድ እኛ ራሳችንን ከምንወደው በላይ እርሱ እንደሚወደንና እኛ ለእኛ መልካም ነው ብለን ከምናስበው እጅግ የበለጠ እርሱ ለእኛ ያውቅልናል።❤□

♂እኛ ተቃራኒውን ልናስብ ብንችልም እግዚአብሔር ለአንተ የሚሰራው ድንቅ ስራ ከረቂቅ ጥበቡና ከመልካምነቱ የመነጨ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።□♂

□አንተ በእግዚአብሔር እጅ ብቻ እንጂ በሌሎች ሰዎች እጆች ወይም በዲያብሎስ እጆች ውስጥ ወይም ደግሞ ለአጋጣሚና ለፈተና የተጋለጥክ አለመሆንህን ልታውቅ ይገባል።□

□አንተ በእግዚአብሔር እጅ ያለህና በመዳፉ□ የተቀረጽክ ነህ (ኢሳ. 49 : 16)

□እርሱ ከክንፎቹም በታች ተማምነህ እንድትጠለል አድርጎሀል (መዝ. 91 : 4)

□እርሱ በቀንና በሌሊት ከአንተ ጋር ነው : መውጣትና መግባትህንም ይጠብቃል (መዝ. 121 : 5)

❤□እርሱ ስለሚወድህለም ልጄ ብሎ ጠርቶሀል (1ኛ ዮሐ. 3:1)

□እርሱ እረኛህ ስለሆነም ምንም የሚያሳጣህ ነገር የለም (መዝ. 22 : 1)

□እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ስለሆንን የጋጣው በጎች ነን። እርሱም መልካም እረኛ ስለሆነ በጎቹን አይዘነጋም።(ዮሐ. 10 : 11)

- **እንደ አባትነቱም ልጆቹን አይረሳም።□**

□የብርሃን እናቱ ሆይ ካንቺ በነሳው ስጋ እኛነታችንን አከበረ።መዐዛሽ □ስቦት አንችን በወደደ ጊዜ ድህነታችን ተሰራ።ድንግል ሆይ እውነተኛው የህይወት እንጀራ □: ጣፋጩን የነፍስ መጠጥ □ አማናዊው የፅድቅ ብርሀን □የፈነጠቀብሽ ነሽና ከትውልድ መሀል ብፅዕናሽን እንናገራለን።ጥማችንን የቆረጠ ጥዑም ወይን፡ረሀባችንን ያጠፋ እውነተኛው መብል ካንቺ ወጥቶልናልና እንወድሻለን።ምስራቃዊት በራችን ሆይ ከሴቶች አንችን የሚመስል የለም።ባንቺ ላይ ስለተደረገልን ታላቅ ነገር ዛሬም ለዘላለምም ስምሽን እናገናለን።

□ዝምተኛይቱ ድንግል ሆይ አንቺ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ የአይሁድ ሴቶች አይደለሽም።በትሕትና ተልመሽ በንፅሕና አጊጠሽ የባህርያችንን መመኪያ ያስገኘሽልን የፅድቅ በራችን ነሽ።

□አንችን ማመስገን የነፍስ ምግብ የህሊና እርካታ ነው።ስናመሰግንሽ እናርፋለን ስናርፍ እናመሰግንሻለን።ክብርሽ ከሰማይ ምስጋናሽም ከአርያም ነውና አንችን ለማመስገን ልቦናችን ይብራ።❤□

ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ

እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ፅድቅ ዘበአማን

ወሰቴ ሕይወት ዘበአማን

- ❤□"እመቤቴ ማርያም ሆይ በሔኖክ መፅሐፍ ውስጥ ትእዛዟ የተጻፈ የመዐዛ ዕጽዋት የሚከቧት የትንቢት ተራራ ነሽ።"

አባ ጊዮርጊስ

- "ክብርት የምትሆን ይህች የክርስቲያን ሰንበት ምን ትደንቅ? እንደ አብ የሰለጠነች እንደ ወልድ የምትገዛ እንደ መንፈስ ቅዱስም የምትኖር ናት። ይህች ቅድስት የክርስቲያን ሰንበት ምን ትደንቅ?
- ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት። ኑ እናክብራት : ኑ በዓል እናድርጋት ። የበዓላትን መጀመርያ ይህችውም ክብርት የምትሆን የክርስቲያን ሰንበት ናት። ትናንት በመግባትዋ ደስ እንዳለን እንዲሁ በመውጣቷ ደስ ብሎን እንሸኛት። በእርስዋ ስጋችንን በማሳረፍ እየተጋን።□
- ዕረፍታችን ግን በደዌ እንደ ታመመ ሰው በመተኛት አይደለም። ቀንና ሌሊት በመትጋት ነው እንጂ። የዚህች ዕለት ወዳጆችዋ እንሆን ዘንድ።"❤□❤□

(□ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ. 160- 174)

ማግኔት ተቃራኒውን እንደሚስብ እግዚአብሔርም ቅዱስ ሳለ ኃጢአተኞችን ያቀርባል። የብርሃን ባሕርይው ማራቆት ነው። እግዚአብሔር ግን የሚሰውር ብርሃን ነው።

□ኃጢአት ሰርተን ወዲያው ፀሐይ አትጠፋም : አየር አይቋረጥም።የመሸው ሌሊት አልነጋም አይልም። በታሪክ ውስጥ ግን ሰው ከመበደል እግዚአብሔር ይቅር ከማለት ያረፉበት ጊዜ የለም።የሰውን ደካማነት አይቶ እግዚአብሔር ንስሐን የሕይወት ውሀ አድርጎ ባይሰጠን ኖሮ ሰው ሰው ለመባል ባልበቃ ነበር። አምላካችን መሐሪ ነውና ብንበድለውም በይቅርታውና በፍቅሩ ይምረናል። በደላችንን በንስሐ ስንናዘዝ ይቅር ብሎ ከእቅፉ ውስጥ ያስገባናል።የአባቱን ሀብት አባክኖ ልቡ እንደተሰበረው ልጅ ተመልሰን ወደ ቤቱ ስንመጣ በምሕረት ዓይኖቹ ያየናል።ርኁቀ መዐት ቅሩበ ምሕረት ነውና ይምረናል።

□የእግዚአብሔር እቅፍ ይሞቃል□

❖ <u>በረከቱ ይደርብንና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አላዋቂ ለሆኑት መናፍቃን እንዲህ ጽፎላቸው ነበር</u>

.....እርሱ የመጀመርያውን ሰው አዳምን ያጠፋው ዘንድ እጅግ ተንኩሎ ተጠብቦበት ነበር ። በተንኮል አነጋገር አዳምን እንደ ተጠበበበት እንግዲህ እኔ ሁሉን ለማዳን በይበልጥ ለምን አልጠበብበትም ? እንደዚሁ እኔም እርሱ ባመጣው ተንኮል ላጠምደው ትሕትና በተመሉ ቃሎች ተጠበብኩበት ። በመለኮታዊ አነጋገርም ለሰይጣን አልተገለጽኩለትም አባት ሆይ የሚቻል ከሆነ ይህ ጽዋ [ሞት] ከእኔ ይለፍ አልኩ እንጂ ።

ዓሣ አጥማጅ መቃኑን በመብል ሸፍኖ ወደ ባሕር ውስጥ በሚጥለው ጊዜ ሲሰበው ለዓሣው እንደሚያስጠመጀው አንድ ጊዜም ሊጎርሰው ጉረሮውን እነደሚከፍት እንዲሁም እኔ መለኮቴን መብል አድርጌ ጣልኩለት ። ለዘላለሙ በማትመረመር ተዋሕዶ በሥጋዬ ውስጥ ያለ የመለኮት መቃጥንን ጣልኩለት ።

በሚያጠምድበት ላይ የተደረገው የሚጎረስ ትል [ወላፍ] ካልተቀሳቀሰ ዓሣው መንጠቆውን ለመጉረስ አይጎመጅም ።ስለዚህ ሥጋዬን እነደሚጎረስ [ወላፍ] ትል አድርጌ አሳየሁት ። እኔ ሰው ያይደለሁ ትል ነኝ አልኩ ። ይህን ሰምቶ በዚህ በሥጋየ ውስጥ ያለችን መቃጥን ሩጦ ሂዶ ይጎርስ ዘንድ ። እኔም በመቃጥኜ እስበዋለሁ ። #በኢዮብ_መጽሐፍ_ከይሲን_በወጥመድ_ትስበዋለህ_ተብሎ_የተጻፈውን_ይፈጸም_ዘንድ ። እኔም ፈርቶ እንደሚሸሽ ሰው ሆኜ ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች ተከዘች አባት ሆይ የሚቻል ከሆነ ይች ጽዋ[ሞት] ከእኔ ይለፍ አልኩ ።

ሰይጣን እነዚህን የትሕትና ቃሎች ሰምቶ በአሳቡ ይህ እንደማንም ሰው ነው እቆራኝዋለሁ አለ ። አባቶች እነ አብርሃምን ፤ ይስሐቅን ፤ ያዕቆብን እንደዋጧቸው ። ይህንም እቆራኝዋለሁ እንደሚፈራ ሰው አየዋለሁና አለ ። እርሱ እየተገዛ በሥጋ የተዋሐደ መለኮት ሊቆራኝ ቃጣ ግን የማይጠፋ የመለኮት ፍም ሆኖ አገኘው ነገር ግን ውስጡን አቃጠለው እንደተጻፈ ለአለም እሳት አምጥቻለሁና ።

እንደ እሩቅ ብዕሲ ያላምጠኛል በውስጡም ጥርሶቹን የምሰብር የጸናሁ ዓለት ሆኜ ያገኘኛል ። ከዛሬ ጀምሮ ሰውን እንዳያላምጥ ያውቅ ዘንድ አምላክ ጥርሶቹን በአፉ ውስጥ ይሰብራልና ያለው የመጽሐፍ ቃል ተፈጸመ ።

ይህች ጽዋ ታልፉ ዘንድ ስለ ሞት የተደረገ ጸሎት እንዳይመስልህ ። ከዚህ ወደ መስቀል መውጣትን ችል ያልኩ እንዳይመስልህ ሞትም እንድትመጣልኝ ስጸልይ አባቴ የእኔ ፈቃድ ያይደለ የአንተ ፈቃድ ይሁን አልኩ ።

መለኮቴን በነገር ሸፍኜ የእኔ ፈቃድ ያይደለ የአንተ የአባቴ ፈቃድ ይሁን ብይ እነደ ሰው ተናገርኩ ። ሰይጣን ግን የእኔ ፈቃድ የአባቴ ፈቃድ እንደሆነ አያውቅም ። የአባቴ የሆነ ሁሉ የእኔ ነው ብዬ እንደተናገርኩ አያውቅም ። ደግሞም እኔና አብ አንድ ነን እንዳልኩ ። እኔ በአብ እነዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ ታውቁ ዘንድ ያልኩትን ። አብ በማንም በማን አይፈርድም ፋርድን ሁሉ ለወልድ ሠጠው ብዬ እነደተናገርኩ ። አብን እነደሚያከብሩ ወልድን ያከብሩ ዘንድ ይገባል ። አባቴ ሁሉን ሰጠኝ እንዳልኩ ረስቶታልና ። እርሱ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፉ ባልኩት ቃል ተታሎ ጠፍቷልና ።

ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ያለው ጌታችን ሞትን ፈርቶ ሳይሆን ሰይጣንን ለማቅረብ እንደሆነ ይወቁ ።

<u>አዳም በበደለ.....</u>

ጌታ በመስቀል ላይ ሲሞት በለበሰው ስጋ እንጂ በመለኮቱ አይደለም።ክርስቶስ በአምላክነቱ ሞት የለበትም (1ኛ ጴጥ. 3:18):: ጌታችን ሰው የሆነው የሰውን ኃጢአትና ሞት ለማስወገድ ነው።ስለዚህም ጌታችን በለበሰው ስጋ እንደሚታረድ በግ ለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኗል። እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ በማለት ስለ ክርስቶስ ተጽፏል (ዮሐ.1:29):: ስለዚህም ክርስቶስ የዓለምን ሐጢአት ሁሉ በመሸከም በእኛ እግር ተተክቶ በመስቀል ላይ ሞቶልናል።አዳም በበደለ መድኃኔ ዓለም ካሠ የተባለውም እውነት ነው።

□ይህ ፍቅር ልዩ ነው። ነፍሱን ለወዳጁ መስጠት የሚችል ሊገኝ ይችላል። እሱም በጭንቅ ነው።ከብዙ ጥቂት ነው። ስለ ጠላቶቹ የሚሞት ግን በጭራሽ አይገኝም። ከክርስቶስ በስተቀር። ገና በኃጢአታችን ሙታን ሳለን ጌታ ኢየሱስ ለኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳያል።❤□

□የወደደን እርሱ በሞቱ አድኖናል።ጀርባችንን ስንሰጠው ፊቱን መልሶልናል። ከእቅፉ ስንወጣ እጆቹን ዘርግቶ ፈለገን። ባገኘንም ጊዜ በትከሻው ተሸክሞ ይዞን አረገ።እስከ መጨረሻም ወደደን።

❤□በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን ያገኘንቀት ይህ ፍቅር ምንኛ ድንቅ ነው?❤□

❤□ከዲያብሎስ አገዛዝና የጨለማ ኃይል ወደ ነፃነትና የሚደነቅ ብርሀን የወጣንበት ይህ መውደድ እንዴት ግሩም ነው?❤□

❤□የሲኦልን መውጊያ ሰብረን በሞት ጀርባ ላይ ቆመን የዘመርንበት ይህ የቤዛነት ስራ ምን ያህል እፁብ ነው?❤□

❤□ያረጀውን አዳማዊ አሮጌ ማንነታችን በአዲስ ክርስቶሳዊ ማንነት የቀየረ ይህ የመስቀል መስዋዕት እንዴት መልካም ነው?❤□

□እግዚአብሔር መልካም ነው።ከፍቅር አቅም በላይ እስከ ሞት ድረስ በመስቀሉ የወደደን ክርስቶስ ድንቅ ነው።□

❤□"የአብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባህርይ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።" (መፅሐፈ ቅዳሴ ቁጥር 43)

□በእውነት ይህ ጌታ ያልተመሰገነ ማን ሊመሰገን ነው? በምስጋና ውለታውን እንመልስ። ማድረግ የምንችለው ይህ ብቻ ነውና□

□የድንግል ማርያም ልጅ መድኃኔዓለም ተመስገን□

ሰይጣን ክፉ ነው። ቢሆንም ደካማ ነው። እርሱ ጋር ካለው ኃይል እኛ ጋር ያለው ጸጋ እግዚአብሔር ይበልጣልና። እኛው ራሳችን በፍቃዳችን ከረድኤተ እግዚአብሔር እያራቅን በሂድን ቁጥር ግን እርሱ እየፈራ እየተንቀጠቀጠም ቢሆን እየቀረበ ይመጣል። ቤቱ ዘበኛ ከሌለው አልያም እንዲሁ ክፍት ከሆነ ሌባ እየፈራም ቢሆን እንደሚገባ። ለቀዳማይቱ ሔዋን ያደረገውም እንደዚህ በቀስታ ነበር። አስቀድሞ በጎልዮ (በሐሳብ) ይሞክራል። በጣም መንቻካ ከመሆኑ የተነሣም ይህን ደግሞ ደጋግሞ ያደርገዋል። ሐሳቡን ለመቀበል ዝግጁዎች እንደሆንን

ሲረዳም ሐሳቡን ፈጥነን ወደ ገቢር (ተግባር) እንድንለውጠው ሹክ ይለናል። ይህም እንደ ሐሳቡ ደጋግሞ ያደርጓል። በተለይ ምቹ.ሁኔታዎችን ሲመለከት ይህን ደጋግሞ ይሞክራል። እንደ ተዘጋጀን ሲያውቅም ክፉ መርዙን እፍ ይልብናል። ከዚያም ሙሉ ለሙሉ ይቆጣጠረናል።

በጣም የሚገርመው ደግሞ ከወደቅን በኋላ የመጀመርያው ከሳሻችን እርሱ መሆኑ ነው። "አሁን አንተ መንፈሳዊ ነኝ ትላለህ፤ ሆኖም ደግሞ እንዲህ በመሰለ ርካሽ ኀጢአት ትወድቃለህ" እያለ ሰላም ያሳጣናል። ለሁሉም ግን ወደ እግዚአብሔር መመለሱ ይሻላል። ነፍሳችንን ቃለ እግዚአብሔርን አናስርባት። በየጊዜው ምክርን ከሐኪሞቻችን (ከንስሐ አባቶቻችን) እንሻ።

"እግዚአብሔርን እንደ ባልንጀራችሁ ቁጠሩት"

(ቅዱስነታቸው ኣቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ)

###########

- እግዚአብሔርን ለመውደድ ከፈለጋችሁ እንደ ባልንጀራችሁ ኣድርጋችሁ ቁጠሩት።
- ይልቁንም እርሱ የመጀመሪያ ባልንጀራችሁ ይሁን፤
- ወደ ማንም ከመጣደፋችሁ በፊትም ወደ እርሱ ተጣደፉ።
- ምስጢራችሁን ለእርሱ ግለጡለት፤
- ሁሉንም ነገር ንገሩት፣
- ከእርሱ ጋር መሆናችሁ የሚሰማችሁ የመደላደል ስሜት ጥልቀትም ይታወቃችሁ።
- ኣሳቦቻችሁንም በሙሉ ንገሩት፣
- የውስጣችሁንም ውስጥ ግለጡለት፤
- ይህንንም በግልፅነት፣በምሉ እውነት፣በመተማመን እና ክፍት በሆነ ልብ ኣሳዩት።
- ከእርሱ ጋር በመነጋገራችሁም ስልቹ ኣትሁኑ። ይልቁንም""ጌታዬ ሆይ፦የምነግርህ ብዙ ነገር አለኝ""በሉት።

ለእኔ ያለህን ፍቅር ኣምናለሁ፣ኣንተ ለእኔ መልካም የሆነውን ነገር እንደምታደርግልኝም እርግጠኛ ነኝ።ኣንተ ይህን ለማድረግ በቂ ኃይል ኣለህ።ኣንተ ይህ ኃይል ካለህ እኔ ለምወዳቸው ሰዎች የምነግራቸውን ነገር ለኣንተ የማልነግርህ ለምንድር ነው"?።

"እግዚአብሔር በማንኛውም ስራችሁ ውስጥ ከእናንተ ጋር የስራ ባልደረባችሁ እንዲሆን ሞክሩ"።

እርሱ ከምናምናቸው ሰዎች በላይ ለቃሉ ታማኝና ሁሉን የሚችል ኤልሻዳይ ስለሆነ።

☐ •• "ገንዘቤ አምላኬ" ••□□☐

✍□. . . በዚህ ሰዓት እንደሰው ከሁሉም በላይ ሊያሳስበን የሚገባ ነገር፣ ጎዳና ቤታቸው ያደረጉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ነው። የሚሆኑት ጨንቋቸው። በሰው እግር ላይ እየተጠመጠሙ ሳንቲም ቢለምኑም "ገንዘቤ አምላኬ" ብሎ ሳንቲም አምላኩ ያደረገው ሰው የተባለው ፍጡር ግን። "አሁንስ አበዛችሁት!" እያለ ረግጧቸውና ገፍትሯቸው የሚሄድ ሆኗል። (ይህን ማየት ልብን ያደማል!) ነገር ግን እነዚህ ልጆች ገና ጥቂት ሳንራመድ "አባት.. አባት በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ምግብ ቤቶች የተራረፈ ምግብ (ቡሌ) ስለማይሰጡን እኮ ነው" እያሉ እንባቸው እየተናነቃቸው ብሶታቸውን ያወጣሉ። (ከምር በጣም ያሳዝናል! በጣም ያማል...) በዚህ ጊዜ ሕይወት ለእነርሱ በጣም ከባድ ናት። ሞት ጥላው አንጣቦባቸው አይዟችሁ የሚላቸው እንኳ አጥተው በጭንቅና በፍርሃት ተውጠዋል።

#ወዳጆቼ! ሰው መድኃኒትም ቤትና ገንዘብም ቢያጣ ሰው ካጠገቡ ካለ ግን መድኃኒቱና ጥላው ሰው ሆኖ በተስፋ ይኖራል። ሰው ካጣ ግን ተስፋ በመቁረጥ "እየኖረም የሞተ" (ህልው ምውት) ይሆናል። "ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው" የሚባለውም ለዚህ ነው።

ለመሆኑ. . . እነሱስ ሰው አይደሉም!? ታድያ ሰው ችግሮት ለሰው ካልጠየቀ ለማን ይጠይቅ። (መቼም አስተሳሰባችን የእንስሳ ከሆነ ቢቆይም) ግን ደግሞ ሆዳችን ለመሙላት እንደ እንስሳ ሳር አንግጥም። እሺ "መንግሥት ምን እያሰበ ነው?" እንል ይሆናል፤ ግን እኛስ ምን እያሰብን ነው? መቼም እኛም በአጋጣሚ በመንገድ ስናልፍ ብናገኛቸው ረግጠናቸው እንደማናልፍ፤ ሳንቲም ፈጣሪውን እንዳደረገና ተስፋ መስጠት ብርቅ እንደሆነው ሰው እንደማንሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

✨ይህን ሳስብና በዐይኔ ሳይ ብዙ ጥያቄዎችን እንድጠይቅ ውስጤ አስገደደኝ። እነዚህ ልጆች ጎዳና ላይ ውለው ጎዳና ላይ እንደሚያድሩ የሚጠፋው ያለ አይመስለኝም። "እንደ በሽታው አካሄድ ከሆነ ደግሞ ቢያንስ ልጆቹ እንደ ዜጋ ለጊዜውም ቢሆንም ተመርምረው አንድ ቦታ የሚቀመጡበት መንገድ አይታሰብም ወይ? እነዚህ ልጆች የማይሄዱበት የማይንቀሳቀሱበት ስፍራ አለ ወይ? ልብሳቸው ቢያድፍ ሰውነታቸው ቢቆሽሽ ሰው አይደሉም ወይ? ለምን ይሆን የእናት ሀገር የኢትዮጵያ ልጆች መሆናቸው የተዘነጉትና የልጅነት መብታቸው የተነጠቁት ለምን ይሆን? ጥያቄ ጭሮብኛል።

ነገሮች እንዴት እየሄዱ እንዳሉ ያሳስባል። "ሀገሬን እወዳለው፣ ደሜ፣ አጥንቴ ገለመሌ ቅብርጥሴ!" ሲል የነበረ ሁሉ ማንነቱን ክዶ ቃሉን በልቶ ለገንዘብ ሲያደገድግ ማየት፣ ገንዘቡን ሃይማኖት አድርጎ ሲያጎበድድ መመልከት ያማል። "ይሉኝታ እሴቴና መገለጫዬ ነው፤ ከአባቴ ቃል ውልፍት... ለኔ ያለው የትም አይሄድም... የኔ እድል ከኔ ውጪ የት ገብታ...?" እያለ አካኪ ዘራፍ ይል የነበረው ሁሉ ከሰው ይልቅ ለገንዘብ ሲያደላ ማየት ይቀፋል። ሰው የሰውን ችግር ተገን አድርጎ ከጎሊና ሕግና ከሀገር ሕግ ውጪ የምግብ ሽቀጦች ላይ እየጨመረ በገዛ ወገኑ ላይ ሞት ሲፈርድ መመልከት ያሳስባል!

ብቻ ይህ የጭንቅ ጊዜ ስንቱን አስተዛዝቦናል! ምንም ይሁን ምንም ግን ከእነዚህ ወንድሞችና እህቶች የሚበልጥ ምንም ነገር አይኖርም። አወቅናቸውም አላወቅናቸውም፣ በዕድሜ አነሱም ተለቁም፣ ከምንም ቦታ መጡም አልመጡም፣ ሥራ ሠሩም አልሠሩም የኛ ኃላፊነት መፍረድና ልባችንን ማደንደን ሳይሆን የቻልናትን ነገር ማድረግ ነው። ፈጣሪ የሚያየው በርኅራኄና በቅንነት ያደረግናት ነገር እንጂ ያልረቡ ምክንያቶቻችን አይደለም።

✔□#ሰብአዊነት_ይሰማህ፣ #ርኅሩኅህና_አዛኝ_ልብ_ይኑርህ፣ #ቸርና_ለሰው_ሁሉ_አዛኝ_ሁን፣ #ልብህን_አታደንድን፣ በተለይ ደግሞ #አትፍረድ!□□

✍□#ወዳጄ! ፈጣሪ ጸሎትህና ለቅሶህ እንዲሰማህ ከፈለክ፥ አንተም የሌሎችን ልመናና ጩኸት ስማ። ከፈጣሪ የምትፈልገው መልስ የምሕረት፣ የርኅራኄና መልካም መልስ ከሆነ አንተም ለሰው ሁሉ መልካምና ርኅሩህ ሁን። ፈጣሪህም በሰማይም በምድርም ዋጋህ ይከፍልሃል።

□ "ገንዘቤ አምላኬ!" ከማለት ይሠውረን። ፈጣሪ መላ የሰው ልጆችን ይጠብቀን□□ አሜን□□

ዝምተኛይቱ+

በዝምታዋ ወንጌል ሰብካናለች።ዝምታዋ ከቃላት በላይ ሆኖ የእያንዳንዳችንን ህይወት ይፈትሻል።ድንግል ማርያም በተለያዩ ሁኔታዎች መህል ሆና በዝምታዋ ወንጌልን ኖራበታለች።የአስተዋይነቷና ልክ የሌለው ትህትናዋ መገለጫ እንዲሁም የባህርይዋ ጌጥ ነው ዝምታ።

□በነፍሷ የመከራ ሰይፍ እንደሚያልፍ አረጋዊው ስምየን ሲነግራት ድንግል ማርያም ሁሉንም በልቧ ትጠብቀው ነበር።(ሉቃ.2: 34 - 51)

□ቀዳሚም ተከታይም የሌለው አንድ ልጇን ሲሰቅሉባትም ርህሩህ ልቧ በሐዘን እየደማ ፊቷ በእንባ ርሶ ከመስቀሉ ስር ሆና የልጇን ዓይኖች በዝምታ ታይ ነበር። ቁንቁዋ እንባ ነበር እንጂ አንድም ቃል ከአንደበቷ አልወጣም።

□ይህችን በንፅህና ያጌጠች : በትህትና የተሸለመች ቅድስት እናት አለመውደድ ምንኛ ከባድ ነው? ለክብሯ አለመዘመርስ ምን ያህል ትዕቢት ነው?

❤□የህይወትን ፍሬ ያገኘንባት የወይን ሐረጋችን

❤□የህይወትን ውሀ የቀዳንባት ምንጫችን

❤□የፅድቅ ፀሐያችን የፈነጠቀባት ምስራቃችን

□አዛኝቷ ድንግል ከፍጡራን በላይ ናት።ታጋሿ እናት ዝምተኛይቱ : ታዛኟ ወላዲተ ቃል የህይወት መምህራችን ናት። እርሷን በማክበር ከትውልድ መህል መቆጠር እንዴት መታደል ነው□

ተ□ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም

የጸሎትና የተመስጦ ሕይወትዋ

ከአባት ከእናቷ ቤት ተለይታ በቤተ መቅደስ እንድትኖር ያደረገ እግዚአብሔር ነው ። የብሕትውና ኑሮን ተምራለች ። የአርምሞ ሕይወት ውሰጥ አልፋለች ። የእናት አባቷን ፍቅር ገና በሕፃንነት ዕድሜዋ ካጣች በኋላ የመራችው ሕይወት በእግዚአብሔር ፍቅር ተጠምዳ የመኖር ሕይወት ነው ። የብሕትውና የዝማሬ የጸሎትና የተመስጦ ሕይወትን ገነዘብ አደረገች ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ከመዝሙራት በማጥናት ኖረች ። በቅድስት ኤልሳቤጥ ፊት የተናገረችው መዝሙር ለዚህ ነገር ማሣያ ነው ። ምክንያቱም ኸተናገረቻቸው ቃላት አብዛኛዎቹን የወሰደቻቸው በቅዱስ መጽሐፍ ከሚገኙ አንቀጾች ነው ።

አርምሞ ከመንፈሳዊነት መገለጫዎቿ መካከል አንዱ ነው ። እነደ ታናሽ ብላቴናነቷ በቤተልሔም የተመለከተችው ክብር እጅግ ታላቅ ቢሆንም ይህንን ሁኔታም ለመሸከም ከዕድሜዋ በላይ ቢሆንም ዙሪዋን በተአምራት ብትከበብም የመላእክትን የእረኞቹን ምስጋና ብታዳምጥም የጥበብ ሰዎች ወርቅ ዕጣን ከርቤን ሲገብሩለት ተቀብላ ብታከፋፍልም የኩራትን ነገር አላሰበችም ። ስለ አንዲቱም ነገር አልተናገረችም " ሁሉን ነገር በልቡናዋ ትጠብቀው ነበር " ተባለላት ። ቅዱሳት መጻሕፍት የሰጡላት ምስክር ይኼንን ነው ። / ሉቃ 2*19/ ይህ ሁሉ ነገር ለእኛ ትምህርት ይሆነን ዘንድ ተጻፈ ። እናታችንን በነገር ሁሉ እንመስላት ዘንድ ትንሽ በመናገር ብዙ በመጸለይና በማሰላሰል በተመስጦ ሕይወትም እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን ።ነገር ግን ለመናገር ጊዜ አለውና የምትናገርበት ጊዜ በደረሰ ጊዜ ለወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ የሚችለውን ያህል ነገረችው ። ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካላት እውቀት እጅግ በጣም ጥቂቱን ክፍል ለምሳሌ የግብፅ ስደቷን ጌታ ከአይሁድ አለቆች ጋር በቤተ መቅደስ ያደረገውን ውይይትና የመሳሰሉትን ለዓብነት ይጠቀሳሉ ።

የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በረከቷ ይደርብን

- ***ክብጹዕነታቸው***

እንደሚታወቀው በቤተ ክርስቲያን ታርክ ሁለት ታላላቅ ትምህርት ቤቶች ነበሩ ። አንደኛው የእስክድርያ ሲሆን ሁለተኛው የአንጾኪያ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ነው ።

የእስክንድርያው ትምሕርት ቤት ጌታችንን በተመለከተ የሚሰጠው ትምህርት ከአምላክነቱ ጀምሮ ሰው ወደ መሆኑ የሚወርድ የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ ሲሆን የአንጾኪያው ትምህርት ቤት ግን ከሰውነቱ ጀምሮ ወደ አምላክነቱ የሚያመራ የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ ይከተላሉ ።

እነዚህ የትምሕርት አሰጣጥ የራሳቸው ተጽዕኖ ነበሩዋቸው ። የእስክንድርያው ትምሕርት ሰሚውን ወደ ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲመራ የአንጾኪያው ግን በክርስቶስ ሰውነት ላይ ያተኮረ ትምሕርት የሚሰጥ በመሆኑ ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚመራ ነው ።

የአንጾኪያው እነ ቅዱስ ኤፍሬምን ፤ እነ ቅዱስ ዩሐንስን አፈወርቅን እነ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግን ሲያፈራ ። የእስክንድርያው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ፤ እነ ቅዱስ ቄርሎስ እና በቅርብ ደግሞ ብጹዕነታቸውን አቡነ ሼኖዳ ሳልሳዊን አፍርቷል ።

የብጹዕነታቸው ትምሕርት ለግብጽ ምእመን ብቻ ሳይሆን በአለም ያሉ ክርስቲያኖች በሙሉ እሚጠቀሙበት ሆኗል ። በርካታ መጽሐፍትን የጻፍ ሲሆን ምእመኑ ፈርሃ እግዚአብሔር እንዲኖረውና ዲያብሎስ ከሚያመጣው ፈተና እራሱን በልምምድ አሸንፎ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ኖሮት ምግባር ሰርቶ ዋጋውን ከክርስቶስ እንዲቀበል ማድረግ ነው ።

የዚህ ፔጅ ተከታታዮች በሙሉ የምንጽፍላችሁን የብጹዕነታቸውን ትምህርት በጥሞና እየተከታተላችሁ ቀስ በቀስ እራሳችሁን ወደ መንፈሳዊነት እንድታቀርብ ነው ።

መንፈሳዊ ሰው ማለት አገልግሎት ላይ ያለ ብቻ አድርገን የምናስብ ጠቂቶች አይደለንም ። መንፈሳዊነት ማለት ግን አንድ ሰው አምኖ ከተጠመቀ በሗላ የአምላኩን ትእዛዝና ፍቅር እየጠበቀና እየተጋደለ ምግባር ትሩፋት እየሰራ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቅ ማለት ነው ። ብዙዎቻችን እንፈልጋለን ግን ከተጫነብን የዓለም ገለባ መውጫ ቀዳዳ ጠፍቶብን ስንኳትን እንገኛለን ።

ብጹዕነታቸው ልዩ የሚያደርጋቸው አምላክ በሰጣቸው ጸጋ ተጠቅመው አሁን ያለንበትን የዓለምን ክፍ ስራ በመግለጥ እንድናውቅበትና እንዴት ድል ነስተን እንደምናሸንፈው ረቂቁን አጉልተው በሚገባን መልኩ ፅፈው አስተላልፈውልናል እኛም እግዚአብሔር እንደፈቀደ እያቀረብን እንገኛለን ። ይህን አታላይ የሆነ አለም በጥንቃቄ ለመሻገር በአሁኑ ግዜ ወደ እግዚአብሔር መቅረቡ መልካም ነውና በይበልጥ መጸሐፎቻቸውን እየገዛችሁ ብትጠቀሙ ለህይወታችሁ ጥሩ ነው

- **በረከታቸው ይደርብን !!**

ድንግል ማርያም

እመቤታችን ለአምላክ እናትነት በተለይ በንጽሕናና በቅድስና የተፈጠረች ድንግል ናት።ሰው የሆነውን አምላክ ወልዳለች እንጂ በሥጋ የወለደችው ሌላ ልጅ ፈፅሞ የላትም።የአንድ የኢየሱስ ክርስቶስን እናት ሌሎችንም ልጆች እንደ ወለደች አድርጎ እንዴት ይታሰባል? ክርስቶስን ለማዋረድ ወይስ ለማክበር? እኛስ በወንጌል እንደተፃፈው አንድ ክርስቶስን ብቻ እንደወለደች እናምናለን።ሌላም ልጅ ልትወልድ አትችልም።ምክንያቱም ድንግልናዋ የዘላለም ነውና።

- "ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ....ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምንም አላደፈችም" ሃይማኖተ አበው ገፅ 174 (ቅዱስ ቴዎዶጦስ)

- ✓ "አንተ ሐሳብህን ልትመራዉ እንጂ፤ ሐሳብህ አንተን ሊመራ ቦታ አትስጠዉ፥ እዉነተኛ ክርስቲያን ስሜቱ የሚመራዉ ሳይሆን ስሜቱን የሚወመራ ነዉ።"
- ✓ ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሰው ሆኖ በተወለደባት በመጀመሪያው ዕለት አስቀድሞ የተመለከተው የእናቱን ፊት ነበር፤ ነፍሱን በአባቱ እጅ አደራ ከመሥጠቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜም የተመለከተው ፊት የእናቱን ነበር።
- ✓ #የጾም_ቀናትን_ጨርሰን_የፍስክ_ቀናት_ሲመጡ_ትደሰታላችሁን?
  ወይስ በዓላቱ ሲመጡ ለምን እንደሚከበሩ እያሰባችሁ ትደሰታላችሁ?
  በትንሣኤ ክርስቶስ በሞት ላይ ያደረገዉን ድል ለረጅም ዘመን የተዘጋ የገነት በር እንደተከፈተ እያሰባችሁ ትደሰታላችሁ?
  እነዚህን በዓላት ባሰብን ጊዜ የተደበቀ በረከት እና ጸጋ አላቸው።
  እነዚህን በዓላት ባሰብናቸው ጊዜ በሕይወታችንም ግሩም ሥራ የሚሰሩ በዓላት ናቸው።

- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

♦□ፍቅር ክርስቶስ ሞተ በእንቲአነ፣ ወኃያል ተንሥአ ከመ ይስብክ ትንሣኤነ።♦□

"ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፤ በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን፤ አሠሮ ለሰይጣን፤ አግዐዞ ለአዳም፤ ሰላም እምይዕዜሰ፤ ኮነ፤ ፍስሐ ወሰላም።"

✞• በእግዚአብሔር ወልድ ፍጹም መገለጥ አምናችሁ "ትንሣኤክ ለእለ አመነ ብርሃነክ ፈኑ ድቤነ፤ ትንሣኤህ ለምናምን ለኛ ብርሃንህ ላክልን ወደኛ" ለማለት ዐቢይ ጸምን በጸም፣ በጸሎት፣ በስግደት ሥጋችሁና ነፍሳችሁን ለትንሣኤው ጌታ በማስገዛት ብርሃነ ትንሣኤው ለተቀበላችሁ የቅድስት ቤተክርስቲያን ልጆች ሁላችሁ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!!!

#በእውነት_ጌታችን_በሞቱ_ፍቅሩ_በትንሣኤው_ኃይሉ_ገለጠልን።
#ያፈ_ከራድዮን_ጌታ_የእኛን_ሞት_በሞቱ_ተቀብሎ_የእርሱን_ሕይወት_በትንሣኤው_ሰጠን
✞• ከመራብ፣ ከመጠማት፣ ከመከራ፣ መቃብር ከመውረድ በኋላ ያለው ደስታ ምንኛ የሚደንቅ ነው? ከሁሉም በላይ ደግሞ የጌታችንን ትንሣኤ የሚመስል ፍጹም ደስታና ሰላም የሚሰጥ ነገር ምንም ሊኖር አይችልም። አማን በአማን "ኮነ ፍስሐ ወሰላም"

♦□ የተወደዳችሁ የክርስቶስ ቤተሰቦች ሆይ! አሁን በክርስቶስ ነጻነታችን ታውጇል፣ ቀንበራችን ተወግዷል፣ ሞታችን ተሽሯል፣ በደላችን ተደምስሷል፣ የሞት መውጊያ ተሰብሯል፣ ሲኦል ድል ተነሥቷል፣ ክርስቶስ በሥልጣኑና በኃይሉ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቷል፣ ዲያብሎስ ተዋርዷል። በእውነት! ክብር የክብር ክብር ለኃያሉ የትንሣኤው ንጉሥ ይሁን!

#ክርስቶስ_ተነሣ፥ ሰይጣን ወደቀ፤

#ክርስቶስ_ተነሣ፥ መላእክት ሐሴት አደረጉ፤

#ክርስቶስ_ተነሣ፥ ሕይወት ነገሠ፤

#ክርስቶስ_ተነሣ፥ ማንኛውም ፍጡር በመቃብር የማይቀር ሆነ፤

#ክርስቶስ_ተነሣ፥ ላንቀላፉት ሁሉም በኩራቸው ሆነ።

እርሱ ክርስቶስ #ሕይወት ነው። #ሞት_ደግሞ_ሕይወት_ክርስቶስን_ሊገዛው_አይችልምና፦ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ" ብሎ እንደሰበከው #እርሱ_ተነሥቶ_ሞትን_ቀበረው። አካላዊ ቃል ክርስቶስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት ቀኑ ጨለማ ነበር፤ ሲወለድ ደግሞ ጨለማው በራ፤ በመስቀል ሲሰቀል ቀኑ ጨለመ፤ ከሞት ሲነሣ ደግሞ ሌሊቱ በራ። በእውነት እርሱ እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ፥ የዘለዓለምን ኀሳር ሰጣቸው።

♦□ከትንሣኤው በፊት #አክራጦን/ደመ ክርስቶስ ተከፍሎልናል። አዎ! ቅዱስ ደሙ በዕለተ ዓርብ አፍስሶ ከኃጢአታችን አጥቦናል። ስለኛ የመሥዋዕቱ አቅራቢ ሆነ፤ የሚሠዋው መሥዋዕትም የመሥዋዕቱ ተቀባይም እርሱ ራሱ ሆነ። ይህ ሁሉ የተፈጸመው በመስቀሉ ነው። አስቀድሞ በኦሪት "ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ፥ እንዲሞትም ቢፈረድበት፥ በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው፥ በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደርም፤" (ዘዳ. ፳፩፥፳፪-፳፫) ተብሎ ነበር። በዕለተ ዓርብ ግን በመስቀሉ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ቀደሰው። እኛም "መስቀል ምክህነ፥ መስቀል ቀርነ መድኃኒትነ፥ ለእለ አመነ መርሐ ይኩነነ ዝንቱ መስቀል መድኃኒተ ኮነ ለአሕዛብ፤ መስቀል መመኪያችን የመዳናችን ቀንድ ነው፤ ላመንን መሪ ይሁነን ይህ መስቀል ለሕዝብ መድኃኒት ሆነ።" የምንል ሆነናል። #ለምን? ቢባል "ወገብረ ሰላመ በመስቀሉ፤ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ" (ኤፌ. ፪፥፲፮) ብለን በመዶሻው ቃል እናጸናዋለን።

✞• የብርሃናት ጌታ ክርስቶስ የጨለማው ዘመን ደፋው፤ ጣዖቱ ዲያብሎስንም ሻረው፤ በሞቱም ሞትን ደመሰሰው፤ "በሞቱ ለሞት ደምሰሶ" እንዲል ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ በቅዳሴው። ይህን ሁሉም የሆነው በፈቃዱ ነበር። "በፈቃዱ ዘተውጎበ ለሕማም ሐመ ከመ ሕሙማነ ያድኅን" እንዲል። "ለምንስ በፈቃዱ ይህ ሁሉ ሆነ?" ብንል፤ ቅዱስ መጽሐፍ "በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና" ይለናል። (ሮሜ ፭፥፲፭)

- ✓ በኃጢአታችን ምክንያት ከእርሱ ጋር ተጣላን፤ በአጋንንት እሥራት ወደቅን፤ ክብራችን ተገፈፈ፤ ገነት ተዘጋችብን። ስለዚህም ሰው ከውድቀት በኋላ ሲፀነስ በዘር፣ በጽነት ምክንያት ዲያብሎስ ከሥራዊቱ አንድ አንድ እየላከ በማኅፀን ይቆራኝ ነበር። ከተወለደ በኋላም ኃጢአት ሲያሠራው ጣኦት ሲያስመልከው ይኖር ነበር፤ ኋላም በጊዜ ሞት ጽሉም ገጹን ሕሱም ራእዩን እያሳየ ያስደነግጠዋል፤ ሲደነግጥ ደሙ ይደርቃል፤ ደሙ ሲደርቅ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች "እስመ ነፍስ ተኀድር በደም" እንዲል። በኋላም ሥጋው በመቃብር ነፍሱም በሲኦል ይቆራኝ ነበር። "አሜሃ ይትፌነዋ ነፍሳት ውስተ ሲኦል፥ እስከ ይመልእ አብያተ ሞት ወለ ዝሞተ እምኔሆሙ የዓሥሩ ነፍሶ ውስተ ሲኦል።" እንዲል። ከዚህ ሁሉ እንዲያድነን፦ ያለ ዘርዐ ብእሲ ተፀንሶ ተወለደ፣ በገዳምም በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣው፤ በፈቃዱም "አመነጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ" ብሎ ነፍሱን ከሥጋው ለየ፣ ወደ ሲኦልም ወርዶ የሙታንን ነፍስ #የሕይወት_ምርኮ_ማረከ (የጥፋት የሚሆን የስልምናሶር የናቡከደነፆር ምርኮ አለና፥ ከዚያ ለመለየት የሕይወት ምርኮ ልንል ይገባናል)፤ አባቶቻችን እንዳስተማሩን "ወአዕረጎሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለ ዘርዑ እምሲኦል፤ ወአጎለፎሙ ለጻድቃን ምስሌሁ እምኀጉ-ል፤ ወኃደጎሙ ለእኩያን ህየ ውስተ ትውክልና፤ ምስለ መላእክቲሆሙ እስከ ዕለተ ደይን፤" እንላለን።

✞• ጠላትም "መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘእምሥልጣንየ ሰብአ ለቢሶ ዘህሎ ኀቤየ ሊተ ሞአኒ፥ መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘነኪር እምሕግየ፥ መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘኮነ ሲሳየ ለኃይለ ነደ እሳት ወሞትኒ፤ ተቆራኝቻቸው የነበሩ ነፍስንና ሥጋን ተዋሕዶ እኔን ድል የነሣኝ ይህ ማነው? አንድም፦ ከሥልጣኔ የለየኝ ማነው? ሲል ነው። ('መኑ' የፍርሃት፣ አንክሮ፣ የመጠርጠር፣ የመመርመር

ቃል ነው።) ከሕጌ የወጣ (የተለየ) ይህ ማነው? አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ለነደ እሳት ለሞት ምግብ ሆኖ የነበረ ይህ ማነው?" በማለት ተናግሯል። ሞትንም ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላም ወደ ውሳጤ መንጦላዕት ገብቶም በየማነ አብ ተቀምጧል።

#በሞቱ_ፍቅሩ፣ #በትንሣኤው_ደግሞ_ኃይሉን_ገለጸልን።

♦□ የተወደዳችሁ የክርስቶስ ቤተሰቦች ሆይ! በእውነት ከትናንት ወዲያ (በዕለተ ዓርብ) ድንግል እናቱ ከልጇ መከራና ሞት የተነሣ ሐዘኗ በርትቷልኀ እናትና አባቷ እንዲሁም በስደቷ ጊዜ ያጽናናትና ያገለግላት የነበረው አረጋዊው ዮሴፍ እንዳያጽናኗት በምድር ላይ በሕይወት የሉም። ድንግል አንድ ልጇን እየተቀባበሉ ሲደበድቡት፣ ከመሬቱ ከድንጋዩ ሲጥሉት፣ በደም የተነከረውና አይሁድ ቀደው የተካፈሉት ልብሱን፣ በደሙ የራሰው መሬቱ ሁሉ በዓይኗ ስትመለከት በእውነት ሐዘኗ ከባድ ነበር። ሐዋርያት እንኳ እንዳያጽናኗት ከዮሐንስ በቀር ሁላቸው ፈርተው ሸሽተዋል።

♦□ ከእጁ በረከትን የቀመሱት፣ በተአምራቱ በትምህርቱ ያደነቁት ሁሉ ዛሬ ከእርሱ ጋር የሉም፤ በዚህ ጊዜ ድንግል ሐዘኗ ጸና። ፋሲካዬ ወደ ለቅሶ፣ ደስታዬ ወደ ሐዘን ተለወጠ አለች። ምን ታድርግ? ራሔል መቃብራቸውን ላላየቻቸው ልጆቿ ካለቀሰች ድንግል የአንድ ልጇን መቃብር እያየች እንዴት ዝም ትበል? ራሔል ላልወለደቻቸው ልጆቿ መጽናናትን እምቢ ካለች ድንግል በድንግልና ጸንሳ፣ በድንግልና ለወለደችው ልጇ እንዴት አታልቅስ?

- ✓ በእውነት ዛሬ ግን በልቧ የጠበቀችውን ሁሉ ሆኖላት ልጇ ወዳጇን ዐየችው፣ 'ልጄ ጌታዬ' ስትለው 'እናቴ' ብሎ ደስታዋን ፍጹም አደረገላት። በሐዘን ከእርሱ ጋር ወደ መቃብር የወረደችው እመ አምላክ ዛሬ በትንሣኤው በደስታ ተነሣች።

#ወዳጆቼ! ለመሆኑ በዕለተ ዓርብ ያዘነችው እናት በዕለተ እሑድ በተነሣው አንድ ልጇ ከሰማይ መላእክትም ከሰው ልጆችም ሁሉ በላይ እንዴት ደስታዋን አይበልጥም!? በእውነት የእርሷስ ደስታ እጅግ የተለየ ነበረ።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ አለ፦ "ከትላንትና ወዲያ #በዕለተ_ዓርብ፦ አይሁድ እየተዘባበቱበት "ራስህን አድን" ይሉት ነበር፤ #ዛሬ_እሑድ፦ ግን እርሱ ጥሎት የተነሣበትን መቃብር መላእክት እየሳሙት ነው፤ #በዕለተ_ዓርብ ሞቶ በመቃብር በተቀበረ ሰው ልማድ በታተመ መቃብር በዝምታ ነበር፤ #ዛሬ_እሑድ ግን ሕያው ሆኖ ለሙታንም ሕይወትን በመስጠት ሁሉንም ወደ ሕይወት አስነሣቸው። #በዕለተ_ዓርብ፦ ጦር፣ ሆምጣጤ እና ሃሞት፣ እሾህ እንዲሁም ስቅለት ነበር፤ #ዛሬ_ግን መላእክት በክብር እና በደስታ ዘመሩለት፤ #ከትናንትና_ወዲያ፦ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር ልጅ ነፍሱን በአባቱ እጅ አደራ ሰጠ፤ #ዛሬ_ግን ሁሉንም የማዘዝ ሥልጣን ያለው እርሱ ነፍሱን ከሥጋው ጋር አዋሐዳት። #ትናንትና_ወዲያ_ዓርብ፦ የመሰቀያውን መስቀል አቆመ፤ #ዛሬ_እሑድ፦ ግን ጥንካሬ፣ የሙታን ትንሣኤና ኀይል ሆነ፤

#ከትናንት_ወዲያ_ዓርብ፦ ስምዖን አላውቀውም በማለት በተደጋጋሚ ካደው (ማቴ. ፳፮፥፷)፤ #ዛሬ_እሑድ_ግን ሞትን ድል ነሥቶ በመነሣቱ መቃብሩን ለማየት ሲሮጥ ሄደ (ዮሐ. ፳፥፬)፤

የዕለተ ዓርብ መከራው ለሐዋርያት ጉባኤ መሸመቂያ አዘጋጀ፤ እሑድ ግን አዲስ ራእይና ደስታ ሆነ። #ትናንት፦ ንጉሡ በመቃብር ተኝቶ ነበር፤ #ዛሬ_ግን ወይኑ እንደተወው ጎያል ተነሣ (መዝ. ፸፯፥፷፭)፤ #ባላፈው_ቀን ቅዱሳት አንስት በመከራ እና በለቅሶ ውስጥ ነበሩ (ሉቃ ፳፫፥፳፬)፤ #ዛሬ_ግን፦ እርሱን እንደ አትክልተኛ አይተውት ታላቅ ደስታ ሐሴትን አደረጉ፤ #በአሳዛኙ_ሰንበት ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው እርሱ በኩረ ሙታን ከሙታን መሃከል ነበር፤ #እሑድ_ግን፦ በመላእክት ጉባኤ ታጀበ (ማር. ፲፮፥፭)። #በዕለተ_ዓርብ፦ የሐዋርያት ጉባኤ በሐዘን ተበተነ፤ #ዛሬ_ግን፦ ትንሣኤውን በመደነቅ ለማየት የደቀ መዛሙርት ጉባኤ ወጥተው ነበር፤ በሌላኛው ቀን በዓርብ ሸሽት፣ በመበታተንና ራሳቸውን መደበቅ ነበረባቸው፤ #ዛሬ_እሑድ ግን ለመሮጥ፣ በአንድ ላይ ለመሰብሰብ እና የምሥራቹን ለማምጣት ቻሉ። #ትናንት_ዓርብ እረኛው ተመትቶ የእርሱም ጠቦቶች ተበታትነው ነበር (ማቴ. ፳፮፥፴፩)፤ ዛሬ እሑድ ደግሞ ተኩላዎቹ ፈረጠጡ፤ መንጋዎቹ በደስታ ተመሉ፤ #ትናንት_ዓርብ፦ ይሁዳ ገንዘብ ተቀበለ፤ ቀያፋ ምክር ሲሰጥ ሃናም ሲያወግዝ ተሰማ፤ ጸሓፍት በሁካታ ውስጥ ነበሩ፤ ጲላጦስ ተቀምጧል፤ ጌታችንም ምሰሶውን ይዞ ቆሟል፤ ስምዖን ክዷል፤ እንድርያስ ሸሽቷል፤ ዮሐንስ ርቀቱን ጠብቋል፤ ፊሊጶስ አይታይም፤ ማቴዎስ ተደብቋል፤ በርተሎሜዎስ ፀጉረ ልውጥ ሆኗል፤ ቀነናዊው ተርበትብቷል፤ ሁሉም በያለበት ተበትኗል።

#ዛሬ_እሑድ፦ ግን ቀያፋ ጎፍረት ተከናንቧል፤ ሃና ግራ መጋባት ውስጥ ገብቷል፤ ይሁዳም ብሩን በትኖ ራሱን አጥፍቷል፤ ጸሓፍትም መናገር ተስኗቸዋል፤ የምኩራብ አለቆች በጎፍረት ራሳቸውን ሸፍነዋል፤ ሌዋውያን እርስ በርሳቸው እየተወቃቀሱ ነው፤ ጲላጦስ ተደንቋል፤ የዚህ ሁሉ ጠንሳሾች ከነጭራሹ በቦታው የሉም፤ የተኩላ መንጋዎች ተበትነዋል። እረኛው ከበጉ ጋር ይነጋገራል፤ መንጋዎቹን ሲሰበስባቸው መዐዛውን ሳቡት፤ #ድንግል_ማርያም_ተደስታለች፤ ሰሎሜም በጎኔት ተመልታለች፤ ማርታ መልካም ዜና ይዛለች፤ ዮሐና የሰላም ዜና ታመጣለች (ሉቃ. ፳፬፥፲)፤ ደቀ መዛሙርት ራሳቸውን ገልጠዋል፤ ሐዋርያት ከተደበቁባቸው ቦታዎች ወጥተዋል፤ ስምዖንና ዮሐንስ ወደ መቃብሩ ሮጠዋል፤ ማቴዎስና በርቶሎሜዎስ ጭንቀታቸውን ረስተዋል፤ እንድርያስና ያዕቆብ በደስታ ውስጥ ናቸው፤ ቶማስ ተናዝዟል፤ ፊሊጶስ ምስጋናን አቅርቧል፤ ወደ መቃብሩ የሚወስደው መንገድ የመብረቅ ነጐድጓድ (በእንቅስቃሴው) አስምቷል፤ ጎልጎታ ጭር ብሏል፤ ለቅሶ (ዋይታ) ወደ ግራ ተሸጋግሯል፤ መጽናኛ በመቃብሩ በስተቀኝ ባለው በር ላይ ቆሟል፤ የታረደው በግ የሰርግ ስፍራ ደቀ መዛሙርቱ እና መላእክቱ በተገኙበት እርስ በርሳቸው መልካም ዜናውን ሲያውጁ ነጐድጓድ መብረቅ አስተጋባ፤ ሞት በሰማርያ ቅጽሮች ላይ እንደነበረው ጦረኛ በሲኦል በር ላይ ተረጋግጧል (፪ኛ ነገ. ፮፥፲፯)፤ ትንቢትም ፊቷን ገልጣ በሞት ላይ በመዘባበት "ሞት ሆይ፥ መውጊያኽ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ?" (፩ቆሮ. ፲፭፥፶፭፤ ኢሳ. ፳፭፥፰፤ ሆሴ. ፲፫፥፲፬)፤ አለች፤ በሕማማቱ የተሰቀለው ጌታ ወደ ሲኦል ወርዶ የሞት ቅርሶችን በመመዝበር ዙፋኑን ወደ መሬት ገልብጦታል፤ በሲኦል ውስጥ ድምፁን አሰምቷል፤ እናም የሲኦል ደጃፍ ተሰብሯል፤ ግድግዳዎቿም አንዳቸው ለአንዳቸው ውድቀቷን አወጁ፤ ዛሬ ተመልካች በፊቧት "ወደቀች፤ የሙታን መኖሪያ ባቢሎን ወደቀች፤ ከተማዋ ወደ ምድር ተጣለች ከቶ ማንም ሊያነሣት የሚችል የለም አሉ"

#ዛሬ፦ ሐሰተኛ ካህናት ከከሓዲው ይሁዳ የተረፈውን ብር ለመቃብሩ ጠባቂዎች ሰጧቸው፤ ትላንት ይሁዳ ሰረቀ፤ ዛሬ ደግሞ ጥበቃዎች መማለጃ (ጉቦ) ተቀበሉ፤ የእውነት ጠላቶች በጉቦ ኪሶቻቸውን አቆሸሹ፤ ግን እውነቱን ለመደበቅ አልተቻላቸውም፤ ጎያሉ ጌታ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ ደካማ ሰዎች ዙሪያውን ከበቡት፤ ነጻ ወጥቶ በእነርሱ ላይ በቀልን እንዳያደርግባቸው ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር፤ በመቃብር አድሮ ሳለ እንኳን ጠላቶቹን ማንቀጥቀጥ የሚችለው እርሱ ባያስፈራቸው ኖሮ ስለምን መቃብሩን ይጠብቁት ነበር? (ማቴ. ፳፯፥፷፬) ጨለማ ጠዋት እንዳትነጋ መጠበቂን ቀጠለች፤ ግን የቀኑ ጊዜ ሊረዱት በማይችሉት መልኩ ሲመጣ ጠላቶቹ የብርሃን ጥላዎች ተዋጡ"

#የፈ_ከራድዮን_ጌታ_የእኛን_ሞት_በሞቱ_ተቀብሎ_የእርሱን_ሕይወት_በትንሣኤው_ሰጠን

#እንደ_በጎች_ትቅበዘበዙ_ነበርና_አሁን_ግን_ወደ_ነፍሳችሁ_እረኛና_ጠባቂ_ተመልሳችኋል።

፳፭፤ የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።

፳፮፤ እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤

፳፫፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤

፳፬፤ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤

፳፭፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።

፩ኛ የጴጥሮስ መልእክት ፪

በርባንን የፈታሁት እኮ ወድጄ አይደለም!

#ሁኔታዎች_አስገድደውኝ_ነው።

ሕዝቡ "በርባን ይፈታልን! ክርሰትቶስ ግን ይሰቀል!" ማለታችንን ስንሰማ መቼም ሁላችንም ማዘናችንና "ምን ዓይነት ክፉዎች ናቸው?" ብለን መውቀሳችን አይቀርም። ወዳጄ ሆይ! እባክህን እስቲ አይሁድንና ጲላጦስን ለአፍታ እንተዋቸው! አንተ ብትሆን ኖሮ ከጌታና ከበርባን ማናቸውን ትፈታለህ?

የእስክንድርያው ትምሕርት ቤት መምህር የነበረው ሊቅ "በሥጋው ክፉ ነገርን የሚሠራ ሁሉ በርባንን ፈትቶ ክርስቶስን አሰረው፤ መልካም ነገርን የሚያደርግ ደግሞ ክርስቶስን ፈትቶ በርባንን አስሮታል" ይላል።

ወዳጄ ሆይ አንተ በሰውነትህ ላይ ፈትተህ የለቀቅከው ማንን ነው? በርባንሰ ነው ወይንስ ጌታን ነው? በርባንን ፈትተኸው ከሆነ ዛሬውኑ በንሰሐ ተመልሰህ ፈጣሪህን በሰውነትህ ውስጥ አክብረው።

"በርባንን የፈታሁት እኮ ወድጄ አይደለም! ሁኔታዎች አስገድደውኝ ነው" ብለህ አንደ ጲላጦስ ለራስህ ይቅርታ ማድረግና እጅህን መታጠብ አይበጅህም። ይልቅስ አሁኑኑ ጌታህን ፈትተህ በርባንን የተባለ ኃጢአትን ስቀለው! ያን ጊዜ የክርስቶስ መሆንህ ይታወቃል።

"የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉ" ተብሎ ተጽፎአልና። ገላ ፭÷፳፬ (http://t.me/popeshenoudaa)

ሕማማት

በዲያቆን ሔኖክ ኃይሌ

♦□ምትን ያጠፋ ዘንድ ስለኛ ሞተ!♦□

✍□የተወደዳችሁ የክርስቶስ ቤተሰቦች ሆይ! ዕለተ ዓርብ የጌታችንን መከራ መስቀሉ የምናስብበትና ከእርሱ ጋር ቀራንዮ ላይ የምንገኝበት ዕለት ልትሆን ይገባል። በእውነት ክብር ምስጋና ይግባውና፥ የሚሠዋ በግ እርሱ ነው፤ የሚሠዋ ካህን እርሱ ነው። ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም መሥዋዕት የሚቀበል እርሱ ነው። በፈቃዱ መከራን በሥጋው የተቀበለ መከራንም ሁሉ የታገሠ እርሱ ነው። እንደ በግ ሊሠዋ መጣ፤ በግ በሚሸልተው ሰው ፊት እንደማይናገር አልተናገረም። በአንደበቱም ሐሰት አልተገኘበትም። ስለ መተላለፋችን ግን ራሱን ስለኛ ለማት አሳልፎ ሰጠ።

ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍስን በትምህርት በማዳኑ፣ ዕዉራነ ሥጋን በተአምራት ዕዉራነ ነፍስን

በትምህርት በማብራቱ፣ ልሙጻነ ሥጋን በተአምራት ልሙጻነ ነፍስን በትምህርት በማንጻቱ፣ አጋንንትን በማውጣቱ፣ ሙታንን በማንሣቱና ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን በማስተማሩ አይሁድ ከፍተኛ ቅንአት አደረባቸው። የሐሰት ምስክሮችን በማቆምም "ይሙት" ብለው የሞት ፍርድ ፈረዱበት። ጌታ በኢሳይያስ አድሮ በምዕ ፶፥፮ አዳምን ዲያብሎስ በገጸ ልቡናው ምራቀ ምክሩን እየተፋ ሲኦል አውርዶት ነበርና ለርሱ ካሣ ሊሆን ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ተተፍቶበታል።

- ራሱንም በዘንግ መቱት "ወኩሉ ርእስ ለሕማም፤ ራስ ሁሉ ለሕመም ኾኗል" (ኢሳ. ፩፥፭)፤ ከዚያም ፊቱን በሻሽ ሸፍነው "መኑ ውእቱ ክርስቶስ ዘጸፍዐከ፤ ክርስቶስ በጥፊ የመታህ ማነው? ንገረን እስቲ ዕወቀን" እያሉ ዘብተውበታል፤

ኤልሳቤጥ፣ ቤርዜሊ፣ መልቴዳ በዕለተ ዓርብ በዐይናቸው ያዩትን የጌታን ሕማማት በተናገሩበት ድርሳን ላይ ይህንን ሲገልጹ፦ "ጌታችን ኢየሱስን አፉን በመቱት ጊዜ ከንፈሮቹ ጥርሶቹም ታመሙ፤ ከጌታችንም ከኢየሱስ አፍ ብዙ ደም ፈሰሰ፤ አሕዛብን በሚያጠፋበት ስለቱ በሁለት ፊት የሆነ የተሳለ ሰይፍ ከአንደበቱ የሚወጣ ሲሆን፥ ዳግመኛ አይሁድ ጌታችን ኢየሱስን ፊቱን ፰ ጊዜ በጡጫ መቱት። ይኸውም በጌትነት ክብር በደብረ ታቦር በተገለጸ ጊዜ ተለውጦ እንደ ፀሓይ ያበራ መልኩ ፊቱ ነው። እርሱ የማይጠልቅ ፀሓይ የማይጠፋ ፋና፤ በወዳጆቹም ላይ ዘወትር የሚያበራ ፀሓይ ነው፤ ሰነፎች አይሁድም ከምድር ነገሥታት ይልቅ የሚያስፈራ ፊቱን ሲመቱት የጌታችን የኢየሱስ የፊቱ ግርማ ሦስት ጊዜ ወደ ምድር የኋሊት የጣላቸው መሆኑን አላሰቡትም።" በማለት በቅንአት የሰከሩ የዝንጉኣን የአይሁድን ነገር አስምረዋል።

ዓለምን ለማዳን ሲል አካላዊ ቃል ክርስቶስ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራዎች ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም በቅዳሴው ላይ ሲተነትናቸው፦ "በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ ረፈቀ ምስለ

አርዳኢሁ መጠወ ነፍሶ ለሞት በፈቃደ አቡሁ ወበሥምረተ ርእሱ…" (ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በተቀመጠባት በዚያች ሌሊት በአባቱ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ ሰውነቱን ለሞት ሰጠ፤ ሁሉን የያዘውን ያዙት ሁሉን የሚገዛውን አሠሩት የሕያው የአምላክን ልጅ አሰሩት፤ በቀኣጣ ጐተቱት በፍቅር ተከተላቸው፤ በሚሸልተው ፊት እንደማይናገር እንደ የዋህ በግ በኋላቸው እየተከተላቸው ወሰዱት፤ ሊቃነ መላእክት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከፊቱ የሚቆሙለትን በዐደባባይ አቆሙት ኃጢአትን ይቅር የሚለውን ኃጥእ አሉት፤ በመኳንንት

በሚፈርደው በርሱ ፈረዱበት፤ ለሱራፌል ዘውድ የሚያቀዳጃቸውን የእሾህ ዘውድ

አቀዳጁት፤ ለኪሩቤል የግርማ ልብስ የሚያለብሳቸውን ለመዘበት ቀይ ግምጃ አለበሱት ኪሩቤል በእሳት ክንፍ ተሸፍነው በፊቱ የሚሰወሩለትን እርሱን ክፉ ባሪያ እጁን አጽንቶ ፊቱን ጸፋው፤

የመላእክት ሠራዊት በፍጹም መደንገጥ ለሚሰግዱለት እየዘበቱበት በፊቱ ተንበረከኩ ይህን ያህል ትሕትና እንደ ምን ያለ ትሕትና ነው?፤ ይህን ያህል ዝምታ እንደ ምን ያለ ዝምታ ነው?፤ ይህን ያህል ቸርነት እንደ ምን ያለ ቸርነት ነው?፤ ይህን ያህል ሰውን ማፍቀር እንደ ምን ያለ ፍቅር ነው?፤ ‹ነያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው፤ በደል የሌለበትን እንደ በደለኛ ሰቀሉት፤ ሕይወት የሠራውን ከበደለኞች ጋራ ቈጠሩት፤ አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ወዮ፤. . . የወልድ መከራውን የሚናገር ምን አፍ ነው? ምን ከንፈር ነው? ምን አንደበት ነው? የፍቁር የጌታ ሕማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል ጎሊናም ይመታል ነፍስም ትንቀጠቀጣለች ሥጋም ይደክማል፤ የማይሞተው ሞተ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ) በማለት ሕማማቱን በስፋት አስተምሮታል።

ወንጌላውያንም እንደጻፉት ጌታችንን አይሁድ ‹ነሙስ ማታ ከያዙት በኋላ "ወወሰድዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እም‹ነበ ቀያፋ ‹ነበ ዐውድ ወኀሕ ውእቱ" ይላል በማለዳ ከቀያፋ ወደ ገዢው ግቢ ወደ ፍርድ ዐደባባይ አስረው በማለዳ ወደ ጲላጦስ ዘንድ ወስደውታል (ማቴ.

፳፯፥፲፩፤ ማር. ፲፭፥፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፩፤ ዮሐ. ፲፰፥፳፰) ይኸውም አዳምን ከመልአከ ገሀነም ፊት አስረው ወስደው አቁመውት ነበርና ለካሣ ሊሆን ነበር። ይህ የጌታችን ትሕትና ብዙዎችን አስደንቋል፤ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንትም በቅዳሴያቸው ላይ

"በይእቲ ሌሊት አ‹ነዝዎ ወጸቢሖ ረበናተ አይሁድ ወሊቃነ ካህናት ምስለ ጲላጦስ መስፍን ወነበሩ ዐውደ ለኰንኖቱ…" (በዚያች ሌሊት ያዙትን በነጋም ጊዜ የአይሁድ መምህሮችና የካህናት አለቆች ከገዢው ከጲላጦስ ጋራ ሊፈርዱበት በዐደባባይ ተቀመጡ፤ እንደ ሌባ የኋሊት አሰሩት እንደ የዋህ በግ በፍቅር ተከተላቸው፤ ሊፈርዱበት በዐደባባይ ተቀመጡ፤ የመላእክት ሠራዊት በመፍራት የሚቆሙለትን በፊታቸው አቆሙት፤ ክፉ ባሪያ እርሱን ያልበደለውን ፊቱን በጥፊ ይመታው ዘንድ እጁን አጸና፤ የመላእክት አለቆች በፍጹም ድንጋጤ ለሚሰግዱለት ለርሱ በትዕቢት ይሰግዱ ዘንድ አጐነበሱለት) በማለት ዐርብ ጠዋት አይሁድ ጌታን ወደ ፍርድ ዐደባባይ እንዴት እንዳቀረቡት በስፋት አስተምረዋል።

ይዘብቱትና ይቀልዱበት ዘንድ ጨካኙ ሄሮድስ የራሱን ልብሱን አውልቆ አለበሰው። ቅዱሳት አንስት የሚሆን ኤልሳቤጥ፣ መልቴዳ፣ በርዜዳ ይህንን ሲገልጹ "ከዚያም ልብሶቹን ገፍፈው የመንግሥት ልብስ የሚሆን ነጭ ሐር የካህናት ልብስ የሚሆን ቀይ ሐር ሕብራቸው ቀይና ጥቁር የሚሆን ልብስ አለበሱት፤ የአጣቢኡ ሳሙና ማንጻት የማይቻለው እንደ መብረቅ የሚያንጸባርቅ እንደ በረድ የሆነ ነጭ ልብስ የሚለብስ ሲሆን፤ ለኪሩቤል የመብረቅ ልብስን ለሱራፌል ግርማ ያለው ልብስን የሚያለብሳቸው እርሱን እንደዚህ በምድር በመዘባበት ቀይ ሐርና ነጭ ልብስ አለበሱት" በማለት አስተምረዋል።

ልዑል አምላክ ዘመኑ ሲፈጸም ስለሚቀበላቸው ሕማማተ መስቀል አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት አድሮ በመዝ ፷፩፥፲፮ ላይ "ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፋተኞች ጉባኤም ያዙኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፤ አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም" በማለት ውሻ ከአፉ ያወጣውን መልሶ ለምግብነት እንዲፈልገው፤ አይሁድም ኦሪትን እለፊ ካላት በኋላ ሲሠሯት በመገኘታቸው በውሻ መስሎ ትንቢት ያናገረባቸው ሲሆን፤ ዳግመኛም ከ፯፻ ዓመት አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስም አድሮ በምዕ ፶፥፮ ላይ "ጀርባዬን ለግርፋት ጕንጩንም ለጥፊ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም" በማለት ያናገረው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም ጌታችንን አይሁድ ገርፈውታል።

በሀገራቸው የሚሰቀል አይገረፍም ነበር፤ በተጨማሪም በኦሪት ልምድ ከአርባ አትርፎ መግረፍ የተከለከለ ሲሆን እነርሱ ግን ፴፱ ጊዜ ከገረፉ በኋላ ቍጥር ተሳሳትን እያሉ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እንደ በረድ ነጭ እስከሚሆን ድረስ ገርፈው እንደ ብራና ወደዚያና ወደዚህ ወጥረው ሲሰቅሉት አጥንቱ ታይቶ የሚቈጠር ሁኗል። አራት ቤት ጭፍሮችና ጲላጦስ በገመድና ባለንጋ ፮ሺሕ ከ፮፻፷፮ ጊዜ ገረፉት፤ አምስት እልፍ ነው የሚሉም አሉ፤ የግርፋቱን ቍጥር እያሳሳቱ ገርፈውታልና፤ የሚሞት እንዳይገረፍ የማይሞት እንዲገረፍ እያወቁ፤ በግፍ ገርፈው በግፍ ገደሉት የተገረፈባቸውም አለንጋና ገመድ በደም ታለሉ፤ ከግርፋቱም ጽናት የተነሣ ሥጋው

ሁሉ አለቀ፤ ሺሕ ከ፮፻ ከሚሆኑ ቍስሎቹም ወገን ዐጥንቶች ታዩ፤ ጥቁርና ሰማይ የሚመስሉ ቍስሎቹ ግን ሺሕ አንድ መቶ ከዘጠና ናቸው፤ የማይገረፍ አምላክ በዚህ ሥጋ ተገረፈ፤ ጲላጦስ እጁን ከታጠበ በኋላ ጌታችንን የገረፈው በጆሮ ለሚሰማው በዐይን ለሚያየው ሰው ዕጹብ ድንቅ ነው፤ በመገረፉም አይሁድን ደስ አሰኛቸው፤ ጌታችን ኢየሱስ ግን በመገረፉ ሰው ሁሉ ከተገረፈባት ኃጢአት ፍዳ አዳነን።

ክብር ይግባውና በአምላካችን ፊት ላይ አይሁድ ምራቃቸውን ተፍተውበታል፤

የሕይወት መገኛ እርሱን የእሾህ አክሊልን አቀዳጁት፤ መላእክትን የብርሃን ራስ ቁር የሚያቀዳጃቸው የነገሥታት ገዢ የሚሆን

እርሱን የሾህ አክሊል አቀዳጁት፤ በሾህ አክሊልም ከራሱ ክፍል ያቆሰሉት ሺሕ ናቸው፤ ከራሱም ቍስሎች ደም እንደ ውኃ በዝቶ ፈሰሰ፤ ፊቱም ደምን ለበሰ ሰውነቱም በደም ተጠመቀ፤ የጽዮን ልጆች እናቱ ያቀዳጇትን አክሊል ተቀዳጅቶ አዩት፤ ተድላ ደስታ የሚያደርግበትና የሙሽርነቱ ቀን ነውና፤ በቀኝ እጁ ዘንግ አስያዙት፤ ሲያሽሟጥጡ በፊቱ እየወደቁ እጅ ነሡለት፤ የመላእክት ሠራዊት እየደነገፁ የሚሰግዱለትን የአይሁድ ንጉሥ ቸር

ውለሃል አሉት፤ ሥልጣናትና ሊቃናት እየፈሩ ለሚሰግዱለት ለርሱ በትዕቢት እጅ ነሡት፤ አምስት የሚሆኑ መዘባበቻቸውን ከጨረሱ በኋላ በምራቁ ሁለተኛ ዐይኖችን በሚፈጥር በርሱ ፊት ላይ ምራቃቸውን ተፉበት፤ ዳግመኛም ፊቱን በጥፊ መቱት፤ ኪሩቤል ፊቱን ከማየት የተነሣ በእሳት አክናፍ የሚሰወሩት ያልበደላቸውን እርሱን አይሁድ በጥፊ መቱት፤ ፊቱ እንደ

መንፈስ ቅዱስና እንደ አባቱ ሲሆን በተዋሐደው ሥጋ ፊቱን ጸፉት ከፊቱ ግርማ የተነሣ ፍጥረቱ ሁሉ የሚርዱለት የሚንቀጠቀጡለት የፈጣሪያቸውን ፊቱን ጸፉት፤ መገሥፈሪያ በመመታቱና የሾህ አክሊል በመቀዳጀቱ ራሱ የቄሰለ ከመሆኑም በላይ የያዘውን በትር ከእጁ ተቀብለው ራሱን መቱት፤ ነገር ግን የሾህ አክሊልን በመቀዳጀቱ በምድራችን ላይ የበቀሉትን አሜከላና እሾኽ ርግማንን አጠፋልን፤ በእውነት ራሱንም በዘንግ በመመታቱ የታላቁን እባብ ሰባቱን ራሶቹን ዐሥሩን ቀንዶቹን አጠፋልን።

ንጹሐ ባሕርይ ጌታችንን አይሁድ መስቀሉን አሸክመው ቀራንዮ ወደሚባል ቦታ ከወሰዱት በኋላ ሁለት ወንበዴዎችን በቀኝና በግራ ጌታችንን በመሃከል አድርገው ሰቅለውታል። ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕ ፶፫፥፲፪ ላይ "ከዐመፀኞችም ጋር ተቈጥሯልና" የሚለው ትንቢቱን ሊፈጽም ሲሆን ምስጢሩ ግን በዕለተ ምጽአት እኛን ኃጥኣንን በግራ ጻድቃንን በቀኝ ታቆማለኽ ሲያሰኛቸው ነበር (ማቴ. ፳፭፥፴፫፤ ራእ. ፩፥፯)።

ቅዱሳት አንስት ኤልሳቤጥ፣ መልቴዳና በርዜዳ ስለዚህ ነገር ሲገልጹ "ወሰቀልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ዲበ ዕፀ መስቀል እንዘ ገጹ መንገለ ምሥራቅ ወእዴሁ ዘየማን መንገለ ደቡብ ወእዴሁ ዘፀጋም መንገለ ሰሜን..." (ጌታችን ኢየሱስንም በዕንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉት፤ ፊቱን ወደ ምሥራቅ ቀኝ እጁን ወደ ደቡብ፤ ግራ እጁን ወደ ሰሜን አድርገው ሰቀሉት...ከርሱም ጋር ሁለቱን ወንበዴዎች አንዱን በቀኝ አንዱን በግራው በመሃከላቸው ጌታችን ኢየሱስን አድርገው ሰቀሉ፤ ሕዝቡም ርሱም እንደነርሱ ወንበዴ ነው

ይሉት ዘንድ ሰቀሉት፤ ርሱ ግን ወድዶ ከወንበዴዎች ጋር በዕንጨት መስቀል ተሰቀለ፤ ልዑላን መላእክት ፈርተው በፊቱ ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ የሚያደርጉለት ርሱ በሚሰቅሉት ፊት ራሱን ዝቅ አደረገ፤ በከሃሊነቱ ሰማይና ምድርን ያጸና ከግርማውም የተነሣ ሰማያትና ምድር የሚንቀጠቀጡለትን እርሱን ደካማ ዕንጨት ተሸከመው፤ እርሱ ግን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ከራሱ ያስታርቀን ዘንድ ከሰማይ ዝቅ ብሎ ከምድር ከፍ ብሎ በዕንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፤ እርሱም ስለእኛ በሥጋው በዕንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ከኃጢአታችን ይለየን ዘንድ በቸርነቱ ያድነን ዘንድ ተሰቀለ (፩ጴጥ. ፪፥፳፬)፤ እርሱ ግን ሰማያትን ይቀድስ ዘንድ በአየር ያሉ አጋንንትን ያወርዳቸው ዘንድ በዕንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ሙሴ አርዌ ብርትን በገዳም እንደ ሰቀለው ርሱም በዕንጨት ላይ ተሰቀለ፤ በርሱ ያመነ ሁሉ ይድናል እንጂ እንዳይጐዳ የክብር ባለቤት ርሱ ግን ስለ እኛ በዕንጨት ላይ ተሰቀለ። አውቀውስ ቢሆን የክብር ባለቤት ጌታን ባልሰቀሉት ነበር (፩ቆሮ. ፪፥፰)፤ ሰማይ ዙፋኑ ሲሆን

ምድርም በእግሮቹ የተረገጠች ስትሆን ስለኛ በዕንጨት ተሰቀለ (ኢሳ ፷፮፥፩)፤ እርሱ ግን ተጠብቆለት ስላለ ስለ ደስታው የመስቀልን መከራ ንቆ አቃልሎ ተቀበለ ኀፍረትንም ናቃት፤ ለተሰቀለው ለርሱ የማይሰግድ ቢኖር የተለየ የተወገዘ ይሁን፤ እርሱ ግን ስለ ዓለሙ ደኅንነት

በማእዝነ ምድር ወደ ላይ ወደ ታች ወደ ግራ ወደ ቀኝ ሆኖ እንደ መጋረጃ በዕንጨት ላይ ተሰቀለ፤ እኛን ከጻድቃን ጋራ አንድ ያደርገን ዘንድ እርሱ ከበደለኞች ጋር ተቈጠረ) በማለት በስፋት የነገረ ስቅለቱን ምስጢር አስተምረዋል።

ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስም በዕለተ ዐርብ በጌታችን ስቅለት ዕለት ስለተደረገው ታላቅ ተአምር ሲገልጽ "ጐየ ፀሓይ ወጸልመ ወርኀ ወከዋክብትኒ ተ·ነብኡ ከመ ኢያብርሁ ለምእመናን በጊዜ ስቅለቱ ቅዱስ እንዘ ፍጹም በገሃሁ ወርኀ ኢያብርህ..."(ፀሓይ ብርሃኑን ነሣ ጨረቃም ጨለመ፤ ከዋክብትም በከበረ ስቅለቱ ጊዜ ለምእመናን እንዳያበሩ ብርሃናቸውን ነሡ፤ ጨረቃም በምልአቱ ሳለ አላበራም፤ ፀሓይ ብርሃኑን በነሣ ጊዜ ፍጡራን ሁሉ በጨለማ ተያዙ፤ የፈጠራቸው ፈጣሪያቸው እንደ ሌባ እንደ ወንበዴ በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ እንዳያዩ ቀኑ ጨለመ፤ ባለሟሉ መልአክም ከሐድያንን ያጠፋቸው ዘንድ ሰይፉን በእጁ መዝዞ ይዞ ከመላእክት መሃከል ወጣ፤ የክርስቶስም ቸርነት በከለከለችው ጊዜ ያ መልአክ የቤተ መቅደሱን መጋረጃ በሰይፉ መታው ቀደደውም፤ ከላይ እስከ ታችም ወደ ሁለት አደረገው። መላእክትም ሁሉ በሰማይ ሁነው እርሱን

አይተው በአንድነት ሲቈጡ የአብ ምሕረቱ የወልድ ትዕግሥቱ የመንፈስ ቅዱስ ቸርነቱ ከለከለቻቸው፤ ፀሓይ ብርሃኑን ነሣ፤ በጨለማ ተይዞ ሲድበሰበስ ዓለምንም ተወው፤ ይህ ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሱን ከሥጋው ከመለየቱ አስቀድሞ ተደረገ) በማለት በስፋት አስተምሯል።

+++ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን +++

‹‹ጲላጦስም የካህናት አለቆችንና መኳንንትን ሕዝቡንም በአንድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፡- ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህንን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት ፤ እነሆም በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም። ሄሮድስም ደግሞ ምንም አላገኘም ፤ ወደ እኛ መልሶታልና ፤ እነሆም ለሞት የሚያደርሰው ምንም አላደረገም። እንግዲያስ ቀጥቼ እፈታዋለሁ አላቸው›› (ሉቃ. ፳፫፥፲፬-፲፮)

ጲላጦስ የጌታችንን ንጹሕ መሆን ካወቀ በኋላ ‹ቀጥቼ እፈታዋለሁ› አለ። ንጹሕ በመሆኑ ምክንያት የተቀጣ ከጌታችን በቀር ማን አለ? ጲላጦስ አይሁድን ደስ ለማሰኘት ስለፈለገ ያን ሁሉ ጥያቄና መልስና ሕጋዊውን የፍርድ ሒደት ማስፈጸም ትቶ በንጹሑ ጌታ ላይ ግርፋት እንዲወርድበት ፈረደ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ›› ብሎ እንደተናገረው ትንቢት ጲላጦስ በእርጋታ ጀምሮት የነበረውን ሕጋዊ የምርመራና የፍርድ ሒደት አሽቀንጥሮ ጥሎ (አስወግዶ) ከሕግ ውጪ በዚያች ቀን በአይሁድ እጅ የተዋረደውን ጌታ ያለ ፍትሕ እንዲገረፍ ወሰነበት። (ሐዋ. ፰፥፴፫)

ጲላጦስ ‹‹ኢየሱስን ይዞ ገረፈው›› (ዮሐ. ፲፱፥፩) የጲላጦስ አሳብ ‹በመሰቀሉ ፈንታ ግርፋት ቢገረፍ ሕይወቱን ካዳንኩለት ቢቆስል ምንም አይደለም› የሚል ነበር። አይሁድም የግርፋቱን ጽናት አይተው ይሙት ማለታቸው እንደሚቀር ተስፋ አድርጎ ነበር። በዚህ ምክንያት ከትናንት ምሽት ጀምሮ ታስሮ ሲንገላታ ያመሸውን ፣ በሐናና ቀያፋ ግቢ ውስጥ ሲደበደብና በጩኸ ሲመታ ያደረውን ጌታ በምሕረት የለሾቹ የሮም ወታደሮች እጅ እንዲገረፍ አሳልፎ ሠጠው።

የሮማውያን ግርፋት እንደ አይሁድ ግርፋት በጅራፍ ብቻ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ እንደገለጠው ጅራፉ በቆዳ ከተሠራ በኋላ በላዩ ላይ ስለታማ የሆኑ የብረት ኳሶች ፣ ሾለው የተሳሉ የአጥንት ስብርባሪዎች ይደረጉበታል። በዚህ አሰቃቂ የግርፋት መሣሪያና በጨካኞቹ ወታደሮች እጅ ወድቀው ሥቃዩን መቋቋም ተስኖአቸው የሞቱም ብዙዎች ናቸው።

በጅራፉ ላይ የተሠሩት የብረት ኳሶችና የአጥንት ስብርባሪዎች በሚገረፈው ሰውነት ላይ ሲያርፉ ሥጋውን እየነጨ የሚነሡ ስለሆኑ ጅራፉ በሰውነት ላይ ማረፉ ብቻ ሳይሆን ከሰውነት ላይ የሚነሣበትም ቅጽበት እጅግ ለመግለጽ የሚከብድ ሥቃይ የሚያደርስ ነው። የግርፋቱ መጠን በጨመረ ቁጥር የደም ሥሮችና አጥንቶች እስከሚታዩ ድረስ የሚጎዳ ፣ የጎድን አጥንቶችን መሰባበር ፣ ከፍተኛ የሆነ ውጪያዊና ውስጣዊ የደም መፍሰስ ፣ የሳንባ መጎዳት የሚያስከትል አሰቃቂ ሒደት ነው።

በዚያች ቀን ጌታችንን ለመግረፍ የተመደቡት ወታደሮች እስራኤልን በብርሃን ዓምድ በሌሊት የመራቸውን አምላክ ፣ ሙሴና አሮንን በደመና ዓምድ ያነጋገራቸውን አምላክ በድንጋይ ዓምድ ላይ ለመግረፍ ዕርቃኑን አሰሩት። የካህናት አለቆችን ደስ ለማሰኘት ሲሉም በሙሉ ኃይላቸው በታላቅ ጭካኔ እጅግ ብዙ ግርፋትን አዘነቡበት። አንድ ገጣሚ እንዳለው በሙሴ አድሮ የፈጣሪን ክብር ለማየት የለመነው የሰው ልጅ ፈጣሪ በጊዜው ‹ጀርባዬን ታያለህ› ብሎ የገባለትን ቃል ቢፈጽምለትና ጀርባውን ቢያሳየው ግርፋትን አዘነበበት። (ዘጸ. ፴፫፥፳፫) በእርግጥም ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ‹‹ከጲላጦስ ግርፋትን ይቀበልበት ዘንድ ጀርባን ፈጠረ›› እንዳለው አምላክ ሰው የሆነውና ጀርባን ለራሱ ያዘጋጀው ስለ ሁላችን ኃጢአትን ግርፋትን ሊቀበልበት ነበር።

የሮማውያን ግርፋት ቅዱስ ጳውሎስ እንደተገረፈው እንደ አይሁድ ግርፋት በመጠን ተወስኖ ‹አንድ ሲኅድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ› እያለ የተገረፈው ሰው በሕይወት ተርፎ እያስታወሰ የሚናገረው ዓይነት ግርፋት አይደለም። (፪ቆሮ. ፲፩፥፳፬)

ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን ግርፋት ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ጊዜ እንደሆነ ስታስተምር አምስት ሺህ ነው ፣ አራት ሺህ ነው የሚሉም አሉ። ይህን አሰቃቂ ግርፋት በሺህ ለሚቆጠር ጊዜ መገረፉን ግን ሁሉም ሊቃውንትና የታሪክ ሰዎች ተስማምተውበታል። ጌታችን እጅግ መገረፉን የሚያሳየን መስቀሉን ባሸከሙት ጊዜ በየሥፍራው እስኪወድቅ ድረስ አቅም ማጣቱ ነው።

የጌታን ግርፋቱንስ መቁጠር ቢቻልም እንኳን ሥቃዩን ግን እንዴት ልንቆጥረው እንችላለን? ቤተ ክርስቲያናችን ከሥጋው አልፎ አጥንቶቹ እስከሚታዩ ድረስ ስለ ተገረፈው አምላክ በዕለተ ዓርብ የምታነበውና የምታዜመው ራሱ ክርስቶስ አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት አድሮ ስለሕማሙ የተናገረው የትንቢት ቃል የሥቃዩ መጠን ጥቂትም ቢሆን ለማሰብ ያግዘናል፡-

‹‹እንደ ውኃ ፈሰስሁ ... አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ ፤

ልቤ እንደ ሰም ሆነ .... በአንጀቴም መካከል ቀለጠ...

አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ ... እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም ...

አጥንቶቼ ተነዋወጡ››

(መዝ. ፳፪፥፲፬፣፲፯፤፲፱፤፴፩፥፲)

ቅዳሴያችን እንዲህ ይላል ‹‹የወልድን መከራውን የሚናገር ምን ዓይነት አፍ ነው? ምን ዓይነት ከንፈር ነው? ምን ዓይነት አንደበት ነው? የፍቅር ጌታ ሕማማቱ በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል ፤ ሕሊናም ይመታል ፤ ነፍስም ትንቀጠቀጣለች ፤ ሥጋም ይደክማል›› በእውነትም የጌታችንን ሥቃይ ለመግለጽ ምንም ዓይነት ቋንቋ ፣ ምንም ያህል ቅኔ አቅም አይኖረውም።

ቅዱስ ኤፍሬምም :-

<<በክርስቶስ የተወደዳችሁ ሆይ ኑ! ወዲህ ቅረቡ ፤ በዚች ዕለት በዳዊት ከተማ የሆነውን አብረን እንይ! በተስፋው ቃል ሲጠበቁ የነበሩት የተመረጡት የአብርሃም ዘሮች ዛሬ ምን እንዳደረጉ እንመልከት! ጌታ ሆይ ረዥሙን ሥቃይህን ማን ሊገልጸው ይችላል?>> ይላል።

ይህ ሁሉ የሆነው ስለ እኛ ኃጢአት ነበር። ኦሪት የሚገረፍ ሰው <<የግርፋቱም ቍጥር እንደ ኃጢአቱ መጠን ይሁን>> ትላለች። (ዘዳ.፳፭፡፪) ጌታችን ማንም ስለ ኃጢአቱ ሊወቅሰው የማይችል ንጹሕ ቢሆንም <<እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ>> ስለተባለ ግርፋቱም በተሸከመው የእኛ ኃጢአት መጠን ሆነ።

<<እርሱ ስለመተላለፋችን ቈሰለ ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ ፤ የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ>> በአጋንንት እጅ ልትገረፍ የጸጋ ልብስዋን አውልቃ ዕርቃንዋን በሲኦል የወደቀች ነፍሳችንን ነጻ ያወጣት ዘንድ እርሱ በጨካኝ ወታደሮች እጅ ዕርቃኑን ተገረፈ።

<<እኛን ከሚገባን ግርፋት ያድነን ዘንድ ኢየሱስ የማይገባውን ግርፋት ተገረፈ>> <<የተገረፈባቸውም አለንጋና ገመድ በደም ታለሉ (ተነከሩ) ፤ ከግርፋቱ ጽናት የተነሣ ሥጋው ሁሉ አለቀ>> ሐዋርያው ጴጥሮስ <<በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ>> በማለት እንደተናገረ <<በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን>> (፩ጴጥ. ፪፡፳፬፤ኢሳ. ፶፫፡፭)

☐ ሰሙነ ሕማማት ☐

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከትንሣኤ በፊት ያለው አንድ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት

(የሕማማት ሳምንት) በማለት ትዘክረዋለች። ሕማማት የሚለው ቃል ሐመ፣ ታመመ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማሙና ሞቱ የሚዘከርበት ሳምንት ነው። ሰሙነ ሕማማት በላቲን Hebdomas Sancta or Hebdomas Maior፣ በግሪክ ደግሞ Ἁγία καὶ Μεγάλη Ἑβδομάς , Hagia kai Megale Hebdomas (ታላቁ ሳምንት) ተብሎ ይጠራል። በኛ ደግሞ ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ሰሙነ ሕማማት ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ባሉት ቀናት ጌታችንን ለመያዝ አይሁድ የመከሩበት፣ ምክራቸውን ያፀኑበት፣ ጌታችንን ሳይዙ እህል ላለመቅመስ ክፉ መሐላ የተማማሉበት፣ጌታችንን የያዙበት፣ የገረፉበት እና በዕለተ ዐርብ በቀራንዮ የሰቀሉበት ሳምንት ይህ ሰሙነ ሕማማት ተብሎ ይጠራል። ሰሙነ ሕማማት እስከ አራተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከጾሙ ተለይቶ ለብቻው ይከበር ነበር። በኋላ ግን በባሕረ ሐሳብ ቀመር መሠረት ጾሙም፣ ሕማማቱም፣ ትንሣኤውም ተያይዘው እንዲከበሩ ተደረገ። ምዕራባውያን ከዐርባ ጾም ውስጥ የመጨረሻውን ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ያደርጉታል። የምሥራቃውያን

(ኦርየንታል) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ግን አርባውን ጾም ጨርሰን

ከሆሣዕና ቀጥሎ ያለ አንድ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት አድርገን እናከብራለን።

በሌላ በኩል ሰሙነ ሕማማት የኦሪት ዘመን ምሳሌም ነው። በዘመነ ኦሪት (አዳም ከገነት ከተባረረበት እስከ ጌታችን በቤተ ልሔም እስከተወለደበት ዘመን) የሰው ልጅ የጽድቅ ሥራው ለመንግሥተ ሰማያት የማያበቃው ነበር። ይልቁንም ነቢዩ ''ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ሆነ'' ኢሳ. 64፥6 እንዳለ የአዳም ዘር በሙሉ እስከ ዕለተ ዐርብ ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ እስካዳነን ድረስ በዲያብሎስ ባርነት ሥር ነበርንና ሰሞነ ሕማማትም የዘመነ ፍዳ ምሳሌ ነው። ይህንንም ለማሰብ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት በሰሙነ ሕማማት ከጸሎተ ሐሙስ በስተቀር ቅዳሴ አይቀደስም፣ ስብሐተ ነግህ አይደርስም፣ ሥርዓተ ማኅሌት፣ ሥርዓተ ተክሊል፣ ጸሎተ ፍትሐት አይጸለይም፣ ጸሎተ አስተሰርዮም አይደረግም፣ ጥምቀተ ክርስትና አይፈጸምም፣ በመስቀል መባረክ፣ ኑዛዜ መስጠትና መቀበል፣ እግዚአብሔር ይፍታሕ ማለት አይኖርም። ከላይ የተዘረዘሩት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አስቀድሞ በዕለተ ሆሣዕና ይከናወናሉ።በሰሞነ ሕማማት ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይ ሰውም የፍትሐት ጸሎት አይደረግለትም። ይህ ማለት በዕለተ ሆሣዕና በአካለ ሥጋ እያለን ካህናት አባቶቻችን የፍትሐት ጸሎት ያደርጉልናል።

ሰሙነ ሕማማት የተለየ ሳምንት ነውና፣ እንኳን ሥጋዊ ደስታና ሳቅ ጨዋታ መንፈሳዊ ደስታም የሚገባ አይደለም።

በሰሙነ ሕማማት ምእመናን እርስ በርስ በመሳሳም ሰላምታ አይለዋወጡም። ይህም ይሁዳ ጌታችንን በመሳም አሳልፎ ሰጥቷልና ያንን ለማሰብ ነው። በሰሞነ ሕማማት መጻሕፍተ ኦሪት፣ መጻሕፍተ ነቢያት፣ የዳዊት መዝሙር ይነበባል። በዚህ ልዩ በሆነ ሳምንት ካህናትና ምእመናን በነግህ፣ በሠልስት፣ በቀትር በተሰዓትና በሠርክ ወደ ቅድስት ቤተ ክርሰቲያን በመጓዝ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርሰቶስ ሕማማተ መስቀል የሚያዘክረውን ምዕራፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት በማንበብና በመጸለይ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማሙንና ሞቱን ያዘክራሉ። "እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ፣ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን" ኢሳ. 53፥4-7 ተብሎ የተነገረው ቃል ተፈጽሞ ጌታችን ለድኅነተ ዓለም ሲል በአጭር ደረት በጠባብ ደረት ተወስኖ የተቀበለው ጸዋትወ መከራ የሚዘከርበት ሳምንት ነው። ነቢያት መቼ ወደ ዚህ ዓለም መጥተህ ከዓመተ ፍዳ ታድነናለህ? ሲሉ የተማፀኑበት ጸሎት፣ የጌታችንን ስለእኛ ሲል የመያዙን፣ የመገረፉን እና የመሰቀሉን ነገር ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው በትንቢት መነፀር እየተመለከቱ የተጻፉ የነቢያት መጻሕፍት ይነበባሉ፣ ይጸለያሉ።

ከቤተ ክርስቲያናችን ሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት ውስጥ የረቡዕ እና ዐርብ ጾም የሚጾምበት ምክንያትም በሰሙነ ሕማማት አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ ከዕለተ ሰኞ ጀምሮ እስከ ረቡዕ ድረስ

ክፉ ምክር ሲመክሩ ቆይተው በዕለተ ረቡዕ ምክራቸውን ያፀኑበት ቀን ሲሆን በዕለተ ዐርብ ደግሞ ጌታችንን የሰቀሉበት ቀን ስለሆነ ነው። በሰሞነ ሕማማት ሳምንት በቤተ ክርስቲያን ግብረ ሕማማት የተባለ መጽሐፍ ይነበባል። ግብረ ሕማማት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳምና ለዘሩ ድኅነት የተቀበለውን መከራ

የሚዘክር መጽሐፍ ነው። ግብረ ሕማማት ማለት የሕመም፣ የመከራ ሥራ ማለት ነው። የጌታን መከራውን ሥቃዩን ሕማሙን በሰዓትና በጊዜ ከፍሎ የሚናገር፣ እንዲሁም ምን በማን መጸለይ እንደሚገባውም በዝርዝር የሚገልጽ በመሆኑና የጌታችንን ሕማም በምናስብበት በሰሙነ ሕማማት በዋነኝነት አገልግሎት ላይ የሚውል በመሆኑ ግብረ ሕማማት ተባለ። መጽሐፉ ግብረ ሕማማት እንዲባል

በውስጡ የታዘዘ መሆኑን የአማርኛው ትርጉም መቅድም ይገልጻል። በግብረ

ሕማማት መግቢያ ላይ ‘ሐዋርያት ለስብከት ወንጌል በሚፋጠኑበት ጊዜ፣ ስለ እርሱ ስለ ጌታችን ታሪኩና ተአምራቱን ይከታተሉ ከነበሩት መካከል የተከበሩና የታወቁ ሊቃውንት በኢንፎስና በገማልያል እጅ ተዕፎ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በክብር ቦታ ተቀምጠ የተገኘ ነው’ ይላል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ዕለታተ ሰሙነ ሕማማት 'ሐመ' ማለት ታመመ ማለት በመሆኑ የሰውን ዘር ሁሉ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ለማውጣት ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃዱ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራዎች የሚያሳስብ ነው። ዕለታቱ የዓመተ ኩነኔ ወይም የዓመተ ፍዳ ምሳሌዎች ናቸው። ክርስቲያኖች የክርስቶስን ውለታ እያሰቡ እጅግ የሚያዝኑበት፣ የሚያለቅሱበት፣ የሚሰግዱበት ቤት ንብረታቸውን ትተው ከሌላው ቀናትና ጊዜያት በተለየ መልኩ ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚማጸኑበት፤ ጧት ማታ ደጅ የሚጠኑበት፤ ኃጢአታቸውን በቤተ ክርስቲያን አደባባይ ለካህኑ የሚናዘዙበት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚገኝ ሳምንት ነው። በዚህ ሳምንት በመራብ፣ በመጠማት፣ በመውጣት፣ በመውረድ፣ በመስገድ፣ በመጸለይ፣ በመጾም በየሰዓቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸዋትወ መከራዎች በማሰብ አብዝቶ ይሰገዳል።

✯ የሕማማቷ ሰኞ (ሰኑይ) ✯

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ሲመላለስ በሆሣዕና ማግሥት ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሁለት ነገሮችን አከናውኗል፤

- አንደኛ ከቅጠል በስተቀር ፍሬ ያልተገኘባትን ዕፀ በለስ ረግሟል። ሁለተኛ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን አስወጥቷል (ማቴ. ፳፩፥፲፪-፲፯፤

ማር. ፲፩፥፲፯፤ ሉቃ. ፲፱፥፵፭-፵፮)። በቅዱስ ማቴዎስ አገላለጥ "በማግሥቱ

ተራበ" የሚል ቃል እንመለከታለን። ነቢዩ ኢሳይያስ "እግዚአብሔር ለዘለዓለም

አይራብም፤ አይጠማም፤ አይደክምም፤" ይላል (ኢሳ. ፵፮፥፳፰)። በቅዱስ ወንጌል

በመጀመሪያ ቃል እንደ ነበር፤ ያ ቃል ቀዳማዊ እንደ ሆነ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ነበር፤ ያም ቃል እግዚአብሔር እንደ ሆነ ተጽፏል (ዮሐ. ፩፥፩-፪)።

ጌታችንም በመዋዕለ ትምህርቱ ሲያስተምር፦ "የእኔስ መብል የላከኝን የአባቴን ፈቃድ አደርግ ዘንድ፤ ሥራውንም እንፈጽም ዘንድ ነው፤" ሲል ተናግሯል (ዮሐ. ፬፥፴፬)። ታዲያ ጌታችን #ለምን_ተራበ?

ሰማያውያን መላእክት እንዳይራቡ አድርጎ የፈጠረ፤ እስራኤልን ገበሬ በማያርስበት፣ ዘር በሌለበት፣ ዝናብ በማይጥልበት ምድረ በዳ የመገበ፤ ድኅረ ሥጋዌ በአምስት አንጀራና በሁለት ዓሣ ከአምስት ሺሕ የሚበልጡ ሰዎችን የመገበ ጌታ "ተራበ" ተብሎ ሲነገር እጅግ ይደንቃል። በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው በመሆኑ አልተራበም አንልም። የጌታችን ረኃብ የድህነት (የማጣት) አይደለም። የክርስቶስ ረኃቡ የበለስ ፍሬ ሳይሆን የሃይማኖትና የመልካም ሥነ ምግባርን ፍሬ የሻ መሆኑን ለማጠየቅ "ተራበ" ተባለ። "በለስ ብሂል ቤተ እስራኤል እሙንቱ" እንዲል። ጌታችን የፈለገውን ባለማግኘቱ #ጉባኤ_አይሁድን_ረግሟል።

በአይሁድ ጉባኤ የነገሠውን ኃጢአት፤ በበለስ አንጻር መርገሙን ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "በአንጻረ በለስ ረገማት ለኃጢአት፤ በበለስ አንጻር

ኃጢአትን ረገማት" ብሏል። እስራኤልም በአንድ ወገን የተጠበቀባቸውን ፍሬ ባለማፍራታቸው ተረግመዋል። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እስራኤል ከፍቅር ይልቅ እርግማን እንዳገኛቸው፤

አሕዛብ ደግሞ የቃሉን ትምህርት ሰምተው የእጁን ተአምራት አይተው ያመኑበትን የእግዚአብሔር የጸጋ ልጁ ለመሆን መብቃታቸውን ሲመሰክር እንዲህ ይላል፤ "አሕዛብ አስተጋብኡ ጽጌሬዳ በጎሩቱ ወሶኩሰ ተርፈ ኀበ አይሁድ ዘውእቱ ሕፀተ ሃይማኖት፤ አሕዛብ በእግዚአብሔር ቸርነት አበባ ሰበሰቡ፤ በአይሁድ ዘንድ ግን እሾሁ ተረፈ። ይኸውም የሃይማኖት ጉድለት ነው፤" ብሎ ተርጒሞታል። እሾህ

የእርግማን፤ አበባ የእግዚአብሔር ጸጋ ልጅነት ምሳሌ ነው።

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች! ዛሬ ጌታችን ወደ መቅደስ ሕይወታችን ቢመጣ ምን

ያገኝ ይሆን? ፍሬ ወይስ ቅጠል? የእግዚአብሔር ቃል "ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤" ይለናልና እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እናፍራ (ማቴ. ፫፥፰፤ ገላ. ፭፥፳፪)። ጌታችን በዳግም ልደት ሲመጣ ከሰው ልጅ ሃይማኖት መገኘቱ አጠራጣሪ እንደ ሆነ ተናግሯል። "የሰው ልጅ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ሃይማኖት ያገኝ ይሆንን?" ሕይወታችንን በአምላካዊ ሥልጣኑ የቃኘ አምላክ ለፍርድ በመጣ ጊዜ የእምነት ፍሬ አፍርተን እንዲያገኘንና ዘላለማዊ መንግሥቱን እንዲያወርሰን የጽድቅ ሥራ ለመሥራት እንትጋ።

♦□ ⛧ የሕማማቷ ሰሉስ ⛧♦□

♦□በማቴዎስ ወንጌል ፳፩፥፳፮፤ ፳፮፥፵፮፤ ማርቆስ ወንጌል ፲፪፥፲፪፤ ፲፫፥፴፯፤ በሉቃስ ወንጌል ፳፩፥፴፤ ፳፩፥፴፰ የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በዕለተ ሰሉስ የሚነገሩ ትምህርቶችን ይዘዋል።

✨ ይህ ዕለት የጥያቄ ቀን በመባል ይታወቃል። በዕለተ ሰኑይ ባደረገው አንጽሖተ ቤተ መቅደስ ፈሪሳውያን ቀርበው "ከቤተ ሌዊ ሆነህ ክህነትን ምክንያት አድርገህ፣ ከቤተ ይሁዳ ሆነህ ንግሥናን ምክንያት አድርገህ እንዳይባል ከሁለቱም ወገን አይደለህም ማስተማርህ፣ ተአምር ማድረግህ፣ ቤተ መቅደስ ማጽዳትህ በየትኛው ሥልጣንህ ነው ብለው ስለጠየቁት የጥያቄ ቀን ይባላል። ፈሪሳውያንን ጌታችንን ከገሊላ ወገን ይመስላቸው ነበር እንጂ ከቤተ ይሁዳ መሆኑን አያውቁም ነበር። (ዮሐ. ፯፥፭) ስለዚህ የቤተ መቅደስን ሥርዓት ማስጠበቅ የሌዋውያን የካህናቱ ሥልጣን ነው፣ የሀገርን ሥርዓት ማስጠበቅ ደግሞ የነገደ ይሁዳ የነገሥታቱ ሥልጣን ነው። አንተ ከነዚህ ወገን ሆነህ ተቀብተህ ስትሾም አላየንምና በየትኛው ሥልጣን ነው ይህን የምታደርግ ብለው ጠይቀውታል። (ማቴ. ፳፩፥፳፫-፳፯፣ ማር. ፲፩፥፳፭-፴፫/ ሉቃ. ፳፥፲፰) "በማን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን የሰጠህ ማነው?" የሚል ነበር። ይህ ጥያቄ ጌታችን ሰኞ ዕለት ሁለት ነገሮችን ማከናወኑን ተከትሎ የተነሣ ጥያቄ ነው። ይኸውም ጌታችን ሲያደርጋቸው የነበሩ ተአምራትና ድንቅ ድንቅ ሥራዎች የካህናት አለቆችን ስላስቀኗቸው ጌታችንን ከሮማ መንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ለማጋጨት የቀየሱት ስልት ነው። ጌታችን በቤተ መቅደስ የነበሩትን ነጋዴዎችን አባሯል፤ መደባቸውን ገለባብጧል። ነጋዴን ማባረርና መደብን ማስለቀቅ መንግሥታዊ ሥራ ነው። ጌታችን "በራሴ ሥልጣን" ቢላቸው ፀረ መንግሥት አቋም አለው በማለት ከሮማ መንግሥት ዘንድ ለማሳጣት ነበር ዕቅዳቸው።

ጌታችን ግን የፈሪሳውያንን ጠማማ አሳብ ስለሚያውቅ "የዮሐንስ ጥምቀት ከየት ነው? ከሰማይ ነው ወይስ ከምድር?" ሲል ጠይቋቸዋል። ጌታችን ፈሪሳውያን ላቀረቡለት ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ አልሰጠም። ምክንያቱም ጥያቄው ለከሳሾቹ ዓላማ መሳካት አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥር ጥያቄውን በጥያቄ መልሶላቸዋል። እነርሱም "ከሰማይ ነው" ቢሉት "ለምን አላመናችሁበትም?" እንዳይላቸው፤ "ከሰው ነው" ቢሉት ደግሞ ሕዝቡ ዮሐንስን እንደ አባት ይፈሩት፣ እንደ መምህር ያከብሩት ነበርና ሕዝቡ እንዳይጣሏቸው ስለፈሩ "ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም" ብለው መለሱለት። እርሱም "እኔም በማን ሥልጣን እነዚህን እንደማደርግ አልነግራችሁም" አላቸው። ይህን ጥያቄ መጠየቃቸውም እርሱ የሚያደርጋቸውን ተግባራት ሁሉ በራሱ ሥልጣን እንዲያደርግ አጥተውት አልነበረም፤ ልቡናቸው በክፋትና በጥርጥር ስለተሞላ ነበር እንጂ።

ዛሬም ቢሆን መልካም ሥራን በሠራን ጊዜ ከልዩ ልዩ ወገኖች የሚመጡ ፈተናዎች ለመልካም ሥራችን እንቅፋት ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን። ብዙ ወገኖች "ለቅን አሳባችን ለምን ሰዎች ክፉ ነገር ይመልሱልናል?" በማለት ሲጠይቁ ይሰማል። ለቅን አሳባችን ከዓለም ዘንድ ተቃራኒ ነገር እንደሚጠብቀን ለመረዳት "ዓለም የሚወደው የገዛ ወገኑን ነው" የሚለውን

የጌታችንን ትምህርት ልብ ይሏል። በዘመናችን አሳልፈው ሊሰጡን የሚፈልጉ ሰዎች ፈታኝ ጥያቄ እንደሚያቀርቡልንም ከወዲሁ ልንገነዘብ ይገባል።

እንደዚሁም በዚህ ዕለት ጌታችን ረጅም ትምህርት በማስተማሩ "የትምህርት ቀን" ይባላል። ቀድሞ እንዳልነው የሃይማኖትን ምሥጢር ለማወቅ የሚሹትን፣ ደክመው የበደሉትን፣ ከፍቅረ እግዚአብሔር የራቁትን ትኩረት በመስጠት ሊረዱት በሚቻላቸው ትምህርት ማስረዳት ይገባልና። ይህንን ሊያስተምር አርአያ ሊሆነን ነው። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከሥጋዊ ነገር ርቆ በዚህ ሰሞን የሃይማኖት ትምህርት ሲማር፣ ሲጠይቅ መሰንበቱ መጽሐፋዊ ሥርዓት ነው። በማቴ. ፳፩፥፳፫፣ ፳፩፥፵፮፣ ማር. ፲፪፥፪፣ ምዕ ፲፫፥፴፯፣ ሉቃ.፳፥፱፣ ፳፩፥፴፰

✞•• የሕማማቷ ዕለተ ረቡዕ ••✞

የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማምት በጌታችን ላይ ይሙት በቃ ብለው ለመወሰን የሰበሰቡት ሸንጎ ‹ሲኒሃ ድርየም› ይባላል። በዚህ ሸንጎ ላይ በአብዛኛው የተሰየሙት ሰዱቃውያን ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ነበሩ። ሸንጎው በአጠቃላይ ሰባ ሁለት አባላት የነበሩት ሲሆን የሚመራውም በሊቀ ካህናቱ በቀያፋ ነበር። በዕለቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ይዘው እንደሚገድሉት አይሁድ በዚህ ሸንጎ መክረዋል። ከዳተኛው ይሁዳም ጸሐፍት ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች በጌታን ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ያውቅ ስለነበር "ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ? እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፤" በማለት ጌታችን አሳልፎ ሊሰጣቸው እንደሚችል ተስማምቷል።

ጌታችን ያስተምር በነበረበት ወቅት የአስቆሮቱ ይሁዳ ከምእመናን ለሚገባው

ገንዘብ ሰብሳቢ (ዐቃቤ ንዋይ) ነበር። ከሚሰበሰበው ሙዳየ ምጽዋት ለግል

ጥቅሙ እየቀረጠ የማስቀረት የእጅ አመል ነበረበት። ይሁዳ ፍቅረ ንዋይ

እንደሚያጠቃው ድብቅ አመሉ ጎልቶ የወጣው ጌታችን በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ በቀባችው ጊዜ ነው። በዚያች ዕለት ይሁዳ የተቃውሞ ድምፅ ካሰሙት አንዱ ነበር። "ይህ ሽቱ ተሸጦ ለድሆች ቢሰጥ መልካም ነበር፤" በማለት ያቀረበው አሳብ

"አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓች" እንደሚባለው ነበር። ሽቱ ሲሸጥ የሚያገኘው ጥቅም

አለ፤ ሽቶው በጌታችን እግር ሥር ከፈሰሰ ለእርሱ የሚተርፈው የለም። ይሁዳ

ተቆርቋሪ መስሎ ያቀረበው አሳብ ተቀባይነት በማጣቱም ማኩረፊያ ያገኘ መስሎት በቀጥታ ከካህናት አለቆች ዘንድ ሔዶ ጌታንን በሠላሳ ብር ለመሸጥ ተዋዋለ። ይህ ታሪክም በሦስቱ ወንጌላት ውስጥ በሚከተሉት ምዕራፎች ተመዝግቦ እናገኛዋለን፤ ማቴ. ፳፮፥፫-፲፭፤ ማር. ፲፬፥፩-፲፩፤ ሉቃ. ፳፪፥፩፮። የአስቆሮቱ ይሁዳ እንደ ሌሎች ሐዋርያት ከጌታችን ተምሯል። በረከተ ጎብስቱን

ተመግቧል። ልዩ ልዩ ተአምራት በጌታችን እጅ ሲደረጉ ሁሉ ተመልክቷል። ጌታችንም ከሌሎች ሐዋርያት ሳይለየው እግሩን አጥቦታል። ከዳተኛው ይሁዳ ግን

ለሐዋርያነት የጠራውን፣ ተንበርክኮ እግሩን ያጠበውን ጌታ ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል።

"የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሔዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ

ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት!" ተብሎ እንደ ተጻፈ (ማቴ. ፳፮፥፳፬)። ሌሎች

ሐዋርያት ከጌታችን ዘንድ ፍቅሩን ገንዘብ ሲያደርጉ ይሁዳ ግን እርግማንን ነው

ያተረፈው። "ገንዘብ የኃጢአት ሥር ነው፤" ተብሎ እንደ ተነገረ የኃጢአት ሥር

የተባለው ገንዘብ የክርስቲያኖችን ሕይወት ያዳክማልና ምእመናን እንደ ይሁዳ በገንዘብ ፍቅር እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሰው "ይህን ዓለም ቢያተርፍ ነፍሱን ከጐዳ ምን ይጠቅመዋል?" ተብሎ የተነገረውን ቃል ልብ ማለት ጠቃሚ ነው። ክርስቲያን ነን በማለት የክርስትናውን ስም በመያዝ እምነታቸውን፣ የቆሙበትን ዓላማ በመገንዘብ የሚለውጡ ሰዎች ዛሬም እንደ ይሁዳ ጌታችንን እየሸጡት እንደ

ሆነ ሊገነዘቡት ይገባል። ለድሆች መመጽወት ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። ዳሩ ግን በድሆች ስም የሰውን ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል እጅግ የከፋ ኃጢአት ነው።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ለገንዘብ ብለው ድሆችን ለረኃብ ለችግር ባልንጀራቸውን

ለመከራ እና ለሞት አሳልፈው ሲሰጡ ምንም አይጸጽታቸውም። እውነተኛ

ክርስቲያኖች ግን ሕይወታችንን ለገንዘብ ፍቅር ሳይሆን ለእምነታችንና ለባልንጀራችን አሳልፈን መስጠት ይኖርብናል። በፍቅረ ንዋይ ተጠምደን ሰዎችን አሳልፎ በመስጠት ለአይሁዳዊ ሽንጐ ምቹ ሆነን መገኘት እንደሌለብን መገንዘብ አለብን።

"ይህ ስለእናንተ ነገ በመስቀል የሚፈስ ደሜ ነው ከእርሱ ጠጡ" ማር. ፲፬፥፳፬

✨•• የሕማማቷ ሐሙስ ••✨

♦□ በዚህች ቀን የተፈጸሙ ድርጊቶች እንደ ቤተክርስቲያናችን ትምህርት ሰፊ ሐተታና ምሥጢር ያላቸው ሲሆኑ አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በታች ያለውን በማስተዋልና በልባችን ጽላት በመጻፍ እናንበው እያልኩ፤ ለዚህም ከሣቴ ምሥጢር መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ይርዳን! አሜን!

፩. #ጸሎተ_ሐሙስ

- ጸሎተ ሐሙስ የተባለው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ይለምን፣ ይማልድ የነበረን ሥጋን የተዋሐደ ፍጹም አምላክ፤ ፍጹም ሰው መሆኑን ለማጠየቅ ለአርአያነት ጠላቶቹ መጥተው እስኪይዙት ድረስ ሲጸልይ በማደሩ ምክንያት ነው፤ (ማቴ. ፳፮፥፴፮-፴፮፣ ዮሐ. ፲፯)

፪. #ዕለተ_የምሥጢር

- ከሰባቱ ምሥጢራት አንዱ በዚህ ዕለት ተመሥርቷልና፤ ይኸውም "ይህ ስለእናንተ በመስቀል ላይ የሚቆረሰው ሥጋዬ ነው፥ እንካችሁ ብሉ፤ጽዋውንም አንሥቶ አመሰገነ፥ ይህ ስለእናንተ ነገ በመስቀል የሚፈስ ደሜ ነው ከእርሱ ጠጡ" በማለት እኛ ከእርሱ ጋር፣ እርሱ ከእኛ ጋር አንድ የምንሆንበትን መንገድ ከጠላት ዲያብሎስ ሰውሮ፣ ለደቀ መዛሙርቱ የገለጠበት ቀን በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው። በዚህ ዕለት ቅዳሴ ይቀደሳል፤ የሚቀደሰውም በለሆሳስ ሲሆን እንደ ቃጭል ሆኖ የሚያገለግለውም ጸናጽል ነው። የዚህም ምሥጢር አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ ሲመጡ ድምጻቸውን ዝግ አድርገው፣ በለሆሳስ እየተነጋገሩ መምጣታቸውን ለማሰብ ነው፤ በቅዳሴውም ጸሎተ ተአምኖ፣ ኑዛዜ አይደረግም፤ ሥርዓተ ቁርባን ግን ይፈጸምበታል፤ ይህም ጌታችን የሰጠውን ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ለማሰብ ነው። በዚህ ዕለት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በንስሐ ታጥቦ ተዘጋጅቶ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ይኖርበታል።

፫. #የሐዲስ_ኪዳን_ሐሙስ

- ጸሎተ ሐሙስ (የፋሲካ እራት) ምክንያቱም መሥዋዕተ ኦሪት ማለትም በእንስሳት ደም የሚቀርበው መሥዋዕት ማብቃቱን ገልጦ፣ ለድኅነተ ዓለም ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበበት ዕለት በመሆኑ ነው። "ይህ ጽዋዕ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን

#ሐዲስ_ኪዳን_ነው። ከእርሱም ጠጡ" በማለቱ ይታወቃል። (ሉቃ. ፳፪፥፳) ኪዳን ማለት በሁለት ወገን መካከል የሚደረግ ውል፣ ስምምነት፣ መሐላ ማለት ሲሆን፤ በዚህ መሠረት ጌታችን ለአዳምና ለልጆቹ ሁሉ ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን በራሱ ደም የፈጸመበት ዕለት መሆኑን በማሰብ የቃል ኪዳኑ ፍጻሜዎች፣ ጠባቂዎች መሆን እንደሚገባን እንማራለን።

፬. #ሕጽበተ_እግር (ትምህርት በእንተ ትህትና)

- "ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ። ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ እርሱም፦ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ፥ እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውላለህ አለው። ጴጥሮስም፦ የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም፥ ካላጠብሁህ፥ ከእኔ ጋር እድል የለህም ብሎ መለሰለት። ስምዖን ጴጥሮስም፦ ጌታ ሆይ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው። ኢየሱስም፦ የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፥ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፤ እናንተም ንጹሐን

ናችሁ፥ ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም አለው። አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፤ ስለዚህ ሁላችሁ ንጹሐን አይደላችሁም አለ። እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንስቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው፦ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ እኔ መምህርና ጌታ ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።" ዮሐ. ፲፫፥፭-፲፭

♦□ በዚህ ዕለት በወንጌላት የተመዘገቡ ድርጊቶችን ቀጥለን እንመልከት፦

❶. የፋሲካ ዝግጅት የተደረገበት ዕለት ነው፤ ዝግጅቱም በሦስቱ ወንጌላት ላይ ተመዝግቧል። (ማቴ. ፳፮፥፲፯-፲፱፣ ማር. ፲፬፥፲-፲፮፣ ሉቃ. ፳፪፥፯-፲፫) ፋሲካ ማለት ማለፍ ማለት ነው፤ ይኸውም እስራኤላውያን በግብጽ ምድር ሳሉ መልአኩን ልኮ እያንዳንዱ እሥራኤላዊ የበግ ጠቦት እንዲያርድና ደሙን በበሩ ወይንም በመቃኑ እንዲቀባ ለሙሴ ነገረው፤ ሙሴም ለሕዝቡ ነገረ፤ ሁሉም እንደታዘዙት ፈጸሙ፤ መቅሰፍተ ከእግዚአብሔር ታዞ መልአኩ የደም ምልክት የሌለበትን የየግብጻውያን ቤት በሞተ በኵር ሲመታ፤ የበጉ ደም ምልክት የእስራኤላውያንን ቤት ምልክቱን እያየ ማለፉን ለማመልከት ነው። (ዘዳ.፲፮፥፩-፲፫) በዚህ መነሻነት በየዓመቱ እሥራኤላውያን በመጀመሪያ ወራቸው በዐሥራ ዐራተኛው ቀን በግ እያረዱ የፋሲካን በዓል ያከብራሉ። ሀገራችንም አስቀድማ ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ ይህ ድርጊት ይፈጸምባት ነበር። በአንጻሩም ዛሬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ፋሲካ ተብሎ የተጠራበት ምክንያት በዚህ በፋሲካ በዓል ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ደሙን ስላፈሰሰልን ነው። በደሙ መፍሰስ ሞተ በኵር የተባለ ሞተ ነፍስ ቀርቶልናልና። "ፋሲካችንም ክርስቶስ ነው።" (፩ቆሮ. 5፥6፣ ፩ጴጥ. ፩፤፲)

❷. በዚህ ዕለት እንደ ማግሰኞው ትምህርት ለደቀመዛሙርቱ ረጅም ትምህርት አስተምሯል ምሥጢረ ሥላሴ (የአንድነቱና ሦስትነቱ ትምህርት)፤ ምሥጢረ ሥጋዌ (የአምላክ ሰው መሆን)፤ በዮሐ.፲፬፥፲፮የሚገኘው በጠቅላላ የዚህ ዕለት ትምህርት ነው። የትምህርቱም ዋና ዋና ክፍሎች ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንና የዳግም ምጽአቱ ነገርነ ው። እነዚህም በስፋትና

በጥልቀት መማር እንደሚገባ ሲያስረዳን፤ በተአምራት ሊገልጥላቸው ሲችል በረጅም ትምህርት እንዲረዱት አድርጓል። ተማሪዎቹን እሱ እያስተማራቸው ሳለ ያልገባቸውን እየጠየቁ ተረድተዋል። ከዚህም እያንዳንዳችን በቤተክርስቲያን ተገኝተን መማርና ያልገባንን ጠይቆ መረዳት እንደሚገባን እንማራለን።

❸. በዚህ ዕለት ከደቀመዛሙርቱ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ የተባለ ጌታ ሆይ፣ መምህር ሆይ ብሎ በመሳም አሳልፎ የሰጠበት ዕለት ነው ጭፍሮቹም በዚሁ ዕለት ሌሊት የክብር ባለቤት የሆነውን ጌታችንን ይዘው ወደፊት፣ ወደኋላ እየገሠቱት፣ እያዳፉ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወስደውታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የትህትና እናት ናትና የአምላካቸውን ምሳሌ የተከተሉ አባቶቻችን ካህናትም በዚህች ዕለት በየዓመቱ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የምእመናንን እግር ያጥባሉ።

በመጨረሻም ይህን የሊቁ ግሩም ቃል እያሰብን ከጌታችን ጋር ወደ ቀራንዮ እንጓዝ። በማለት እፈጽማለሁ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል፦

"ሁሉን የያዘውን ያዙት፤ ሁሉን የሚገዛውን አሠሩት፤ የሕያውን አምላክ ልጅ አሠሩት፤ በቁጣ ጎተቱት፤ በፍቅር ተከተላቸው። በሚሸልተው ፊት እንደማይናገር እንደ የዋህ በግ በኋላቸው እየተከተለ ወሰዱት፤ ሊቃነ መላእክት በመፍራት እና በመንቀጥቀጥ ከፊቱ የሚቆሙለትን በአደባባይ አቆሙት፤

ኃጢአትን ይቅር የሚለውን ኃጥእ አሉት፥ በመኳንንት የሚፈርደውንም በእርሱ ፈረዱበት፤ ለሱራፌል ዘውድ የሚያቀዳጃቸውን የሾህ ዘውድ አቀዳጁት፤ ለኪሩቤል የገርማ ልብስ የሚያለብሳቸውን ለመዘበት ቀይ ግምጃ አለበሱት፤ ኪሩቤል በእሳት ክንፍ ተሸፍነው በፊቱ የሚሰወሩለትን እርሱን ክፉ ባሪያ አሥሮ ፊቱን ጸፋው፤ የመላእክት ሠራዊት በፍጹም መደንገጥ የሚሰግዱለት እየዘበቱበት በፊቱ ተንበረከኩ።

ይህን ያህል ትሕትና እንደምን ያለ ትሕትና ነው? ይህን ያህል ትእግስት እንደምን ያለ ትእግስት ነው? ይህን ያህል ዝምታ እንደምን ያለ ዝምታ ነው? ይህን ያህል ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው? ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው በደል የሌለበትን እንደ በደለኛ ሰቀሉት። ሕይወትን የሠራውን ከበደለኞች ጋር ቆጠሩት፤ አዳምን የሠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፤ ወዮ በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ተቸነከሩ።

♦□ወዮ በአዳም ፊት የሕይወት እስትንፋስን እፍ ያለ አፍ ከሃሞት ጋር የተቀላቀለ የኮመጠጠ መፃፃን ጠጣ፤... ወዮ የወልድን መከራውን የሚናገር ምን አፍ ነው? ምን ከንፈር ነው? ምንስ አንደበት ነው? የፍቁሩ የጌታ ህማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያልና፤ ህሊናም ይመታልና፤ ነፍስም ትንቀጠቀጣለችና፤ ሥጋም ይደክማል የማይሞተው ሞተ፤ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ፤ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ። የምትወዱት ሰዎች ፈጽሞ አልቅሱለት።"

በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ስያሜዎች ያሏቸው በርካታ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዕለት ነውና ጸሎተ ሐሙስ ይባላል። የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን የተዋሐደ አምላክ፣ መሆኑን ለመግለጥና ለአርአያነት ጠላቶቹ መጥተው እስኪይዙት ድረስ ሲጸልይ ያደረበት ነውና ጸሎተ ሐሙስ ተባለ። (ማቴ. 26፥36-46 ዮሐ.17)

#ሕፅበተ_ሐሙስ_ይባላል፡-

ጌታችን በዚህ ዕለት የደቀመዛሙርቱን እግር በፍጹም ትሕትና ዝቅ ብሎ አጥቧል። ይህም የሚያሳየው የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ለማጠብ የመጣ መሆኑን ነው። ይህን ለማስታወስ ዛሬም ካህናት በተለይም ሊቃነ ጳጳሳት፣ የደብር አስተዳዳሪዎች፤ «በመካከላችን ተገኝተህ የእኛንና የሕዝብህን ኃጢአት እጠብ እኛም የአንተን አርአያ አንዘነጋም የሌላውን እግር እናጥባለን፤» ሲሉ በቤተ ክርስቲያን የተገኙትን ምእመናንን እግር በወይንና በወይራ ቅጠል ያጥባሉ።

#የምስጢር_ቀን_ይባላል፡-

ከሰባቱ ምስጢራት አንዱ በዚህ ዕለት ተመሥርቷልና። ይኸውም «ይህ ስለ እናንተ በመስቀል ላይ የሚቆረሰው ሥጋዬ ነው። እንካችሁ ብሉ» ጽዋውንም አንስቶ አመሰገነ «ይህ ስለ እናንተ ነገ በመስቀል የሚፈስ ደሜ ነው ከእርሱም ጠጡ» በማለት፤ እኛ ከእርሱ ጋር፣ እርሱ ከእኛ ጋር አንድ የምንሆንበትን ምስጢር ከጠላት ዲያብሎስ ሰውሮ፣ ለደቀ መዛሙርቱ የገለጠበት ቀን በመሆኑ የተሰጠ ሥያሜ ነው። በዚህ ዕለት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በንስሐ ታጥቦ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል ይዘጋጃል።

#የሐዲስ_ኪዳን_ሐሙስ_ይባላል፡-

ምክንያቱም መሥዋዕተ አሪት ማለትም በእንስሳት ደም የሚቀርበው መሥዋዕት ማብቃቱን ገልጦ፣ ለድኅነተ ዓለም ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበበት ዕለት በመሆኑ ነው። «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን ሐዲስ ኪዳን ነው። ከእርሱ ጠጡ» በማለቱ ይታወቃል (ሉቃ. 22፥20) ኪዳን ማለት በሁለት ወገን መካከል የሚደረግ ውል፣ ስምምነት፣ መሐላ ማለት ነው። በዚህ መሠረት ጌታችን ለአዳምና ለልጆቹ ሁሉ ዘለዓለማዊውን ቃል ኪዳን በራሱ ደም የፈጸመበት ዕለት ስለሆነ የሐዲስ ኪዳስ ሐሙስ ተባለ።

#የነጻነት_ሐሙስ_ይባላል፡-

ለኃጢአትና ለዲያብሎስ ባሪያ ሆኖ መኖር ማብቃቱ፣ የሰው ልጅ ያጣውን ክብር መልሶ ማግኘቱ የተረጋገጠበት ቀን ስለሆነ ነው። ጌታችን ስለ ሰው ልጅ ነጻነት ሲናገር «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ባርያ ጌታዉ የሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ» በማለት (ዮሐ. 15፥15)፤ ከባርነት የወጣንበት ልጆች የተባልንበትን ቀን የምናስብበት በመሆኑ ሊቃውንቱ የነጻነት ሐሙስ አሉት። እያንዳንዱ ክርስቲያንም ከኃጢአት ባርነት ርቆ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያወዳጀውን መልካም ሥራ በመሥራት ሕይወቱን መምራት ይኖርባታል። ባሮች አልላችሁም ተብለናልና።

እርሱ አምላኬ ነው ቲ ተ □

☞ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም ውስጥ በድንግል እቅፍ ውስጥ ብታገኙት እንዳይመስላችሁ እርሱ አምላኬ ነው።

☞በዩርዳኖስ ማህል ቆሞ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ በገዳመ ቆሮንቶስ ሲራብና ሲጠማ ሲፅልይ ብታዩት እንዳይመስላችሁ እርሱ በእሳት የሚያጠምቀው ፤ መናን ከሰማይ ውሀን ከአለት የሚያፈልቀው ጸሎትን የሚቀበለው እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ ከተናቀችው ከናዝሬት ከገሊላ ቢመጣ በአህያ ጀርባ ላይ ተጭኖ ኢየሩሳሌም ሲገባ ብታዩ እንዳይመስላችሁ በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በሱራፌል የሚመሰገነው አለምን የፈጠረው እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ በምድራዊ ንጉስ በጲላጦስ ፋት ቆሞ ፤ሲከሱት ፤ በደለኛ ነው ብለው በሀሰት ሲወነጅሉት ፤ ብታዩት ። እንዳይመስላችሁ ስለ እኔ ተገብቶ ነውና እርሱ አምላኬ ነው ።

☞የእሾህ አክሊል በእራሱ ላይ ደፍቶ ቀይ ልብስ ደርቦ በአይሁድ ፍት እርቃኑን ቆሞ ብታዩት ። በእኔ ተገብቶ ነውና ። የብርሀን አክሊል ያለው የማይተረጎም ልብስ የሚጎናጸፈው ። እርቃኔን የሸፈነው እርሱ አምላኬ ነው

☞መስቀል አሸክመው እንደ በደለኛ ሲገፉት ሲገርፉት ፤ ሲጎትቱት ፤ በጥፉ ሲፅፉት ፤ በርግጫ ሲረግጡት ፤ በገመድ ሲጎትቱት፤ ምራቅ ሲተፉበት በብጫ ሲመቱት ብታዩት ። የእኔን ሀጥያት ተሸክሞ ነውና እንዳይመስላችሁ እርሱ መዳህኒቴ ነው ።

☞ ከፕራይቶርዮን እስከ ቀራኒዬ ጎልጎታ ደም እየጎረፈው ፤ ወዝ እየነጠበው ፤እልፍ ግዜ ተመሬት ሲወድቅ ሲነሳ መስቀል ሲጎትት ፤ አቅም ሲያጥረው ብታዩት ፤ እውነት እላችኋለሁ እርሱ የእኔን በደል ተሸክሞ ነውና እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ በቀትር ግዜ ተፈርዶበት በወንበዴ መሀል በእንጨት መስቀል ተሰቅሎ እጅ እግሩ ተቸንክሮ ከኮረብታው ላይ ብታዩት እንዳይመስላችሁ ወንበዴ ። እኔ ተላልፌ ቀጥፌ በበላሁት በለስ ነውና በእኔ ተገብቶ ነው እንጅ እርሱ አምላኬ ነው።

☞ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ እያለ ከመስቀል ላይ ሲጸልይ ፤ ሲፈሀ ብታዩት ። እውነት እውነት አላችኋለሁ የእኔን ጨህት እየፈሀ ነውና እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ በእለተ አርብ ጀንበር ሲያዘቀዝቅ ጎኑን ተወግቶ ደም ፤ውሃ ፤ ሲፈሰው አንገቱን ደፍቶ ስጋውን ለመቃብር ነፍሱ ወደ ሲኦል ሲያወርድ ብታዩት እኔን ከሲኦል ወደ ገነት እየመለሰኝ ነውና እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ ሲገንዙት ፤ በበፋታ ሲሸፍኑት ፤ በአዲስ መቃብር ስጋውን ብታዩት ሦስት ቀን ሦስት ለሊት በከርሰ መቃብር ቢቆይ እንዳይመስላችሁ ። ሲኦልን በዝብዞ ገነትን እየከፈተ ነውና እርሱ አምላኬ ነው ።

☞ እውነት እላችሃለሁ እንዳይመስላችሁ እሩቅ ብዕሲ እርሱ አምላኬ ነው !!!! ።

✍ ዛሬ በዚች ዕለት ንፅሕት ከሆነችው ከልጅ ልጄ ተወልዶ ደሙን አፍስሶ ፤ስጋውን ቆርሶ ፤በደሌን ክሶ ፤ ከወደኩበት አንስቶ ፤ጨለማውን ያጠፋልኝ መድህን አለም ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ሰው እንዳይመስላችሁ እርሱ አምላኬ ነው ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰምህ፡-

"ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! መንፈሳዊ ምስጋና ሁሉ ለአንተ ይገባል። ዋጋው የማይታወቅ ነጋዴ ገንዘቡን ሁሉ ሰጥቶ የተወዳጀው እውነተኛ ዕንቁ ደንጊያ አንተ ነህ። ይህንን የዕንቁ ደንጊያ በሰውነታችን ውስጥ ያበራ ዘንድ ደግሞ ዛሬ ለእኛ አድርግልን። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! የተቀደሰው ስምህ የልባችን ደስታ የሰውነታችን ሽልማት ጌጥ ነው።

አቤቱ ምድርንና ዓለሙን ሁሉ ዞርሁ ያለ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር ጣፋጭ ስምን አላገኘሁም። በምድር ላይ የሚደረግ ረድኤትና ኃይል ሁሉ ያለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር አይሆንም። እግዚአብሔርን ያገለገሉ የሰው ወገኖች ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። የከበረና የተመረጠውን እጅ መንሻ ሁሉ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አልተቀበልንም። ሰማይና ምድር ያለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከሁከት አልጸኑም።

የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከማር ከወለላና ከሃከር ይጥማል። ማርና ሃከር በሚበሉበት ጊዜ ይጠገባሉ፤ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግን አይጠገብም። የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በምጠራ ጊዜ ከንፈሮቼ ማርን ያንጠባጥባሉ። ማር፣ ስኳርና እንጀራ ቢሆኑም እንደ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእኔ ዘንድ ጣዕም የላቸውም። የጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሻለኛልና ከሰማይ በታች ካለ ፍጥረት ሁሉም ይበልጣልና።

ቸርነትህ ብዙ ነው፤ አይነገርምም። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በሚያምንብህና በሚወድህ አፍ ሁሉ ስምህ የታወቀ ነው። በሕግ ከታወቁ ምስጋናዎች ሁሉ ከውስጣቸው የሚመስልህ የለም። የዓይኖቼ ብርሃንና የሥጋዬ ብርታት ከከበረው ስምህ ወገን ነው። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! እስከ ሕይወቴ መጨረሻ የከበረ ስምህን በአንደበቴ ዘወትር የተሾመ አድርገው። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትያን ሰውነት ሁሉ የጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአንድነት ያከብራሉ፤ ያመሰግናሉ።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ከኃጢአት ወገን የሚሆን የክፋት መንፈስን ሁሉ ከእኔ አስወግድ። መዳኛችን በሚሆን በዚህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክርስቲያኖች ሁላችሁም ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ።

የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጣፋጭ ነው፤ በገነት ካለ ፍሬም ይልቅ ይጣፍጣል። አባታችን ዳዊት በአመሰገነበት በከበረ መዝሙር የጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ፈጽሞ እናመሰግናለን፤ እናከብራለን።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ብዙ የሆነ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በእኔ ላይ አሳድር። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አንተን ደስ የማያሰኝህን ሓሳብ ሁሉ ከእኔ ታርቅ ዘንድ ወዳንተ እለምናለሁ፤ ከአንተም እሻለሁ። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በጌትነትህ ከእኔ ጋር ቸርነትህን አድርግ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እንሰግድልሃለን! ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እንሰግድልሃለን! መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ ማኅየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንሰግድልሃለን። አሜን!"

(ምንጭ፥ ግብረ ሕማማት)

ተ□ተመስጠ

"አቤቱ በቀኖጣህ አትቅሠፈኝ፥

በመዓትህ አትገስጸኝ።"

ዳዊት እዚህ ላይ ኃጢአቱን ተናዝዟል ቀኖጣና መቅሰፍት የሚገባው ሰው መሆኑን ተናዝዟል። ይሁን እንጂ ይህ በፍጥነት እንዳይከናወንበት ጠይቋል።

እርሱ #ለእግዚአብሔር " በቀኖጣህ አትቅሠፈኝ ፥" ነው ያለው። እርሱን ይህን ያለው ደካማ ሰው ስለሆነና #የእግዚአብሔር ቀኖጣ ለመሸከም ስለማይችል ነው . . . ጌታ ሆይ፡- በቀኖጣህ የምትገሥጸኝ ከሆነ ልታጠፋኝም ሆነ ላትጠብቀኝ ትችላለህና የሚለው። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በነብዩ ኤርምያስ ተነግሯል፡-" አቤቱ ቅጣኝ ፥ ነገር ግን እንሳታዋርደኝ በመጠን ይሁን እንጂ በቀኖጣ አይሁን።" ኤር10 ፡ 24 ።

እርሱ ከቀኖጣ ለማምለጥ ምንም ዓይነት ምክንያት አላቀረበም ይልቁንም " አቤቱ በቀኖጣህ አትቅሠፈኝ ፥" ነው ያለው። ምክንያቱም " በህያው #እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።" ዕብ 10 ፡ 31።

#እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት እጅግ በተቆጣ ግዜ ዓለምን በውኃ አስጥሚት ነበር። ከዚህ በኋላ በርህራሄ ተመልሶ ለሕዝቡ ሲያዝንላቸው በምድር ላይ ያለውን ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደማያጠፋ ምልክት ሰጥቶአቸዋል፥ ዘፍ 9፡ 15። #እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ በተቆጣ ግዜ እርሱንና ሰራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞአቸዋል፥ ዘጸ 14፡ 28።

#እግዚአብሔር በቆሬ፥ በዳታንና በአቤሮን ላይ ቀኖጣው በበደደች ግዜ ምድር ተከፍታ እንድትውጣቸው አድርጓል፥ ዘህ 16 ፥32።
እኛም በየዕለቱ ኃጢአት እንሠራለን ምናልባት የእኛ ኃጢአት የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት ሊመስል ይችላል።

በዚህም ግዜ"አቤቱ በቀኖጣህ አትቅሰፈኝ" እያልን ወደ እርሱ እንሮሃለን።

#እግዚአብሔር የሰዎች ስሜት አያቆስልም ልቦቻቸውንም አይጎዳም።

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እርሱ የታመመውን ሰው ባለው እንክብካቤ ሁሉ እንደሚያድን ሀኪም ነው እንጂ በቅሬታ ወይም በማጨናነቅ እንደሚያክም ሃኪም አይደለም።

"ለበጎ ነው"

"አንድ ንጉስ ከአጃቢው ጋር በመሆን ለአደን ይወጣል። ለአደን ሲወጡ ንጉሱ ወጥመድ እያጠመደ እያለ ወጥመዱ አምልጦት እጁን ቆረጠው። በዚህም አጃቢው በማዘን "አይዞህ ንጉስ ሆይ ሁሉ ነገር ለበጎ ነው!" ይለዋል። በዚህም ንጉሱ በንዴት እየጮፈ "የኔ እጅ መቆረጥ ነው ለበጎ?" ይለውና እስር ቤት አሳሰረው።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ንጉሱ ብቻውን ሀገሩን ሲዞር ሰው አርደው ለጣዖት መሰዋት የሚያደርጉ ጨካኝ ሰዎች ያዙትና አርደው መሰዋት ሊያደርጉት ሲሉ ቆራጣ እጁን አዩት። በእነሱ ህግ መሰዋት የሚያደርጉት ሰዉ ሙሉ ጤነኛ መሆን ስላለበት ለቀቁት።

ንጉሱ አጃቢው 'ሁሉ ነገር ለበጎ ነው!' ያለው ትዝ አለውና እስር ቤት ሄዶ ስላሰርኩህ ይቅርታ አርግልኝ! ብሎ ታሪኩን አጫወተው። አጃቢውም "ማሰርህ ለበጎ ነበር! እኔም መታሰሬ ጠቅሞኛል።" አለው። ንጉሱ "እንዴት?" አለው አጃቢውም "ባልታሰር ኖሮ ከአንተ ጋር እሄድና አንተ ቆራጣ መሆንህን ሲያውቁ ይለቁህና አኔን ይገሉኝ ነበር" አለው።

ስለዚህ ሁላችንም ስለተደረገልንም ሆነ ስላልተደረገልን እንዲሁም ስለሆነውም ሆነ ስላልሆነው ነገር ሁሉ "ለበጎ ነው" ማለት ይልመድብን።

#አቡነ_ሺኖዳ_ሳልሳዊ

ተ□ በጸሎት ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ።

□ ስትጸልይ በማክበር ውስጥ መሆንን ተለማመድ፣ የልብና የሥጋ ማክበር ይኑሩህ፣ የስሜቶች ሰላም እንዲሁ።

□ ቀስ በቀስ መዝሙራትን ወንጌላትን የዘውትር ጸሎቶችን አጥና።

□ በሁሉም ጊዜ ውስጥ ጸሎት መጸለይ ተለማመድ፡- ስትስራ፣ ስትራመድና ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትቅመጥ እንኳ።

□ ዘውትር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ " ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ።" እያልህ መጸለይ ተለማመድ።

□ በማንባውም ጊዜ ለሌሎች ሰዎች መጸለይን ተለማመድ ለሁሉም ሰዎች ፍቅር አሳይ።

□ ለጠላቶችህና አንተን ለሚሰድቡህ ሰዎች እንድትጸልይ ለሚያዝህን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተለማመድ ተግባራዊ አድርግ።

❖ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

†□ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በመከራ ውስጥ ይመጣል ።

አንድ ሰው መፍትሔ የሌለው የሚመስል መከራ ሊገጥመው ይችላል ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ መከራው የገጠመው ጥቂት ኃጢአቶችን ስለ ፈጸመ መሆኑን ከማስጠንቀቂያ ጋር ይነግረዋል ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቃሉ ንስሓ ከገባህ መከራው ፍጻሜ ያገኛል እያለ ውስጡን ሲመክረው ይሰማል ። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ንስሓው ሲል ለሰውየው ይራራለታል ።

የእግዚአብሔር ድምፅ አንድ ሰው ሲታመም ወይም እርሱ የሚወደው ሌላ ሰው ሲታመም ሊመጣ ይችላል ። በዚህ ጊዜ እንዲጸልይ ወይም ስእለት እንዲሳል የሚመክረውን ድምፅ ከውስጡ ይሰማል ይህ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው ።

የዮሴፍ ወድሞች እህል ሊገዙ ወደ ግብጽ ከወረዱ በኋላ በዚያ ችግር ሲገጥማቸው እርስ በእርሳቸው እንዲህ በማለት ተነጋግረው ነበር ፦ " በእውነት ወድማችንን በድለናል እኛን በማማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውና ። ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን ።"/ ዘፍ 42*21/ ። ከዚህ በኋላ ለዮሴፍ እንዲህ ብለውታል ፦ " ለጌታዬ ምን እንመልሳለን ? ምንስ እንናገራለን ? ወይስ በምን እንነጻለን ? እግዚአብሔር የባሪያዎችህን ኃጢአት ገለጠ ..."/ዘፍ 44*16/ ኃጢአታቸውን እንዲያስታውሱ ጎላም እንዲገሰጹ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር ድምፅ ነው ።

ነቢዩ ዳዊት የጌራ ልጅ በሆነው በሳሚ ሲሰደብ የእግዚአብሔር ድምፅ ውስጡን ስላለፈ ኃጢአቱ እየወቀሰው መሆኑን አዳምጧል ። ስለሆነም በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች "

"እግዚአብሔር ዳዊትን ስደበው ብሎታልና ይርገመኝ ። / 2ኛ ሳሙ 16*10/ በማለት በግልጽ ተናግሯል ።

ረሀብና የመሬት መንቀጥቀጥ በዓለም ሲደርስ የእግዚአብሔር ድምፅ በመላው ዓለም ውስጥ ይሰማል ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ የሚናገረን " ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ።" / ሚል 3*7/ እያለ ነው ። ይህ ድምፅ በረሀቡ ወይም በመሬት መንቀጥቀጡ ጉዳት ለደረሰባቸው ሀገሮች የሚሆን የእርዳታ ጥሪ ለማሰማት ወይም ሌሎቹ ከእነርሱ ትምህርት በመውሰድ ንስሓ እንዲገቡ ለማድረግ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ዝግጅት እንዲያደርጉ ነው ።

ስለዚህ ማንኛውም ዓይነት መከራ ውስጥ ስትገቡ ከውስጣችሁ ያለውን የእግዚአብሔር ድምፅ አድምጡት እርሱ ለእናንተ ሊነግራችሁ የሚወደው ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁና ።

ተ□ዐሰሩ መዓርጋት

የእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን በአንድ ግዜ የፍጹምነትና የቅድስና ደረጃ ላይ አይደርሱም ። ይልቁንም የተወለደ ህፃን ቀስ በቀስ ከመዳህ ወደ መቆም ፤ከመቆም ወደ መራመድ ፤ ከዚያም ወደ መሮጥና መዝለል እንደሚሸጋገር ሁሉ ቅዱሳንም ከወጣኒነት (ከጀማሪነት) ጀምረው በጸጋ እግዚአብሔር እያደጉ ወደ ፋፅምነት ይደርሳሉ ። በዚህ መሰረት ቅዱሳን ደረጃ በደረጃ የሚደርሱባቸውን ዐሥር መዓረጋት አሉ። እነዚህም ሦስቱ "" በንፅሃ ሥጋ"" የሚገኙ አራቱ ""በንጽሐ ነፍስ"" ሦስቱ ደግሞ ""በንጽሐ ልቡና "" የሚገኙ ናቸው ።

☞ #በንጽሐ_ሥጋ ፦ የሚገኙ ሦስት መዓርጋት።

1.ጽማዌ ፦ ዝም ጸጥ ማለት መናገርንና መቀባጠርን መተው ማለት ነው። ሙሉ ሐሳባቸውን ወደ ፈጣሪያቸው ለማድረግ ሥራውንም ለማዘከር ይችል ዘንድ የዚህን አለም ጣጣ ከማሰብና ከማውራት መላ ሕዋሳታቸውን ይከለክላሉ።

2.ልባዌ ፦ ልብ ማድረግ ፤ማስተዋል በጥልቀት ነገሮችን መረዳት ማለት ነው።

3.ጣዕመ_ዝማሬ ፦ ሳይሰለቹና ሳይቸኩሉ ምሥጢርንና ትርጓሜውን እያወጡና እያወረዱ በንቁ ጎሊና ማመስገንና መጸለይ ነው።

☞ #በንጽሐ_ነፍስ ፦ የሚገኙ አራት መአረጋት።

4.አንብዕ ፦ እንባቸውን ከዐይናቸው እንደ ሰን ውኃ ሳያቋርጥ ማፋሰስ ነው።ይህ ማለት ሰውነታቸው በሐዘን ሳይከፋ በስጋዌ ሐሴትም ሳይሞላ ሳይሰቀቁ ከዐይናቸው የሚፈልቁት እንደ ሰን ውኃ የሚፈስ እንደ ነሐሴ ዝናብ የሚመነጭ ከአርሞና ከተደሞ የሚመጣ ነው ።

5.ኩነኔ ፦ በማዕረጋት ሂደት ኩነኔ ማለት ሥጋን ለነፋስ ማስገዛት ማለት ነው። ቅዱሳን ከኩነኔ መዓርግ ላይ ሲደረስ ፈቃደ ስጋቸውን ፈጽሞ ለነፋሳቸው ይገዛል ሥጋ የነፋስ መሣሪያ ይሆናል

።ነፋስ ሥጋን የወደደችውን ታሰራለች ፤ መስገድ ፤መጸም ፤ መጸለይ ፤ሁሉ ቀላልና ጠባያዊ እስኪሆኑ ይደርሳሉ።

6.ፍቅር ፦ እግዚአብሔር ከመፋጠር ያልናቀውን ፋጥረት ሁሉንም አስተካክሎ መውደድ ማለት ነው። ጎጥና ፤ጻድቅ ፤ አማኒና ፤መናፋቅ ፤እንዲሁም ወዳጅና ጠላት ብሎ መለያየት ሳይኖር ማንኛውንም ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በክብር የተፈጠረ ስለ ሆነ ብቻ መውደድ ነው።

7.ሑሰት ፦ ካሉበት ቦታ ሆኖ ካሰብት መድረስ ነው።ይኸውም አንድ ቦታ ሆነው እንደ እግረ ፀሐይ ካሰቡት ቦታ ይደርሳሉ በሌላ ቦታ የሚሰራውን ያውቃሉ ። ለምሳሌ ነብዩ ኤልሳዕ በኢየሩሳሌም ሆኖ የሶርያዊው ንጉስ ወልደ አዴር እልፋኙን ዘግቶ ከባለማሉ ጋር የመከረውን ምክር ማንም ሰው ሳይነግረው ያውቅበት ነበር ተብሎ በመፅሀፉ ቅዱስ እንደተፃፈው ማለት ነው።

☞ #በንፅሐ_ልቦና ፦ የሚገኙ ሦስት መዓርጋት ደግሞ ፦

8.ንፃሬ_መላእክት ፦ በዓፀደ ስጋ ሆነው መላእክትን በየከተማቸውና በየቦታቸው ያያሉ ። በሦስቱ ዓለመ መላእክት በኢዮር ፤ በራማ ፤ በኤረር ፤ ያሉ ቅዱሳን መላእክትን በየነገዳቸውና በየአለቃቸው እንዲሁም በየክፋለ ቦታቸው ሆነው " ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ" እያሉ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ያያሉ።

9.ተሰጥሞ_ብርሃን ፦ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር ባህርይ ገንዘብ በሆነው በሚያስደንቀው ብርሃን ውስጥ መዋኘት ነው።ይህም እነርሱ በዚህ ብርሃን ውስጥ እያሉ ሌላ ለዚህ መዓርግ ያልበቃ ሊያየው የማይችለው ብርሃን ነው። ጨለማ የማይሰለጥንበት እንደ እዚህ ዓለም ብርሃን የማያቃጥል ጨረር ዐይን የማይበዘብዝ ነፋስን ከስጋ መለየት የሚያስችል ደስታ እስኪሰማ ድረስ ግሩም መዓዛ ያለው ነው።

10.ከዊነ_እሳት ፦ የመጨረሻ መዓረግ ሲሆን እዚህ ደረጃ የደረሱ ቅዱሳን ሰውነታቸው ለአጋንንት የሚያቃጥልና የማይቀረብ ይሆናል።

እነዚህን አጠቃለው የያዙ የልብን ንፅህናን ገንዘብ አድርገዋልና ለነፅሮተ ስሉስ ቅዱስ ይበቃሉ። "ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዮታልና"።ማቴ 5@8

✉ "ፍጹም ልትሆን ብትወድ ፥ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ በሰማይም ታገኝዋለህ ።" ማቴ 19፥21

"የግብረ ሰዶማዊነት መነጋገርያ ጉዳይ ሊሆን የሚገባው ባይሆንም ይህን ጉዳይ መነጋገርያ አድርጌ በማንሳቴ እጅግ እያዘንኩ በአገልግሎቴ ተገድጄ ልመክር ግን እወዳለሁ።"

- ***<u>አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ</u>***

ግብረሰዶማውያንና መንግስተ ሰማያት የሥጋ ሰዎች (ሥጋውያን) መንግስተ ሰማያትን ሊወርሱ አይችሉም። ቅዱስ ዮሐንስ በራዕዩ ስለ ሰማያዊቱ እሩሳሌም በተናገረበት ምዕራፍ እንዲህ የሚል እናነባለን ። ‹‹ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰት እና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም›› ራዕ 21፡27 ።።።››› ግብረ ሰዶማዊነት በሞት ያስቀጣ ነበር ... ኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ የሚል ተጽፏል። ‹‹ከሴት ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ ፀያፍ ነገር ነውና።›› ዘሌ 18፡22በዚህ መጽሐፍ ‹‹ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋልና፣ ፈጽመው ይገደሉ። ደማቸው በላያቸው ነው።›› በማለት የሚጠብቃቸውን ጽኑ ፍርድ ያመለክታል። ዘሌ 20፡13 ።።።››› ግበረ ሰዶማዊነት በሐዲስ ኪዳንም የተወገዘ ነው ሐዲስ ኪዳን ስለንጽሕና ሕግ እና ትምህርት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ግብረ ሰዶማዊነትን በማውገዝ የተነገሩ አራት መልእክቶችን

እናገኛለን።

1. ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ በመጀመርያው ምዕራፍ ‹‹እውነት በዐመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢያታቸውና በዐመፃቸው ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጠልና ›› በማለት ይመሰክራል። የእግዚአብሔር ቁጣ ለምን ተጻፈ ለምን ተገለጸ? ዝቅ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ‹‹ስለዚህ እርስበእርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ እርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው›› ሮሜ 1፡18-24 ‹‹አሳልፎ ሰጣቸው›› ማለት ጸጋና ረድኤት መስጠቱን እንደነፈጋቸው ማመልከቱ ነው። ተላልፈውም የመሰጠታቸው ምክንያት ሥጋቸውን ሊያዋርዱ የራሣቸውን የትኩረት ስራ አያስተውሉም ነበርና ነው። ይህን በመሰለም እብደት ስጋቸውን ያረክሱ ነበር የሰውነታችን ክብር የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ በመሆን የሚገለጽ ነው። ነገር ግን በጸያፍ ሥራ በርኩሰት ሥጋችንን የምናጠፋው ከሆነ ውርደት ነው፤ ክብራችን መንፈስ ቅዱስ ይርቀናልና። ‹‹ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ

ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባሕሪያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕሪያቸው በማይገባ ለወጡ ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕሪያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ። ወንዶችም በወንዶች ነውር አድረገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።›› ሮሜ 1፡21-27 በማለት ሐዋርያው የሚገልጸው የሰዶማውያን አይነት ጸያፍ ሥራ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስለሚያፈጥን ነው። በዚህ መልዕክቱም በግልጽ ይህ የሰዶማውያን ሀጥያት አእምሮን የሚያረክስና የልተገባም በመሆኑ በዘመነ ሐዲስም የሚወገዝ መሆኑን ይጠቁማል። ‹‹ለባሕሪያቸው የሚገባውን ስራ ለባሕሪያቸው በማይገባው ለወጡ›› በሚልበት ግዜ ግብረሰዶማዊነት የተፈጥሮን ስርዓት የሚቃረን መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል ። በተጨማሪም ይህ የርኩሰት ሥራ ሥጋን ማዋረድ ፣ ለቅጣትም ተላልፎ መሰጠት እንደሆነ ተናግሯል።

2. ሌላውና ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመርያ በጻፈው መልዕክቱ ያስተላለፈው ትምሕርት እንዲህ ይላል። ‹‹አትሳቱ ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣያትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሰሩ (ግብረሰዶማውያን) የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም ።›› በዚህ ቃሉ የምንረዳው ይህን የመሰለ የሚፈጽም ሁሉ እግዚአብሔር ካዘጋጀው መንግስት ውጭ መሆናቸውን ነው። 1ቆሮ 2፡9

ግብረ ሰዶማዊነትና ፍቅር

. . . ግብረ ሰዶማዊነት በሥጋ ፍቃደ ላይ የተመሰረተ ርኩሰት እንጂ ፍቅር አይደለም። በስጋ ፍላጎት እና በፍቅር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። እንዲህ ላለው የኃጢያት ግንኙነት ፍቅር የሚስማማው ቃል አይደለም። ምክንያቱም በወንጌል ‹‹እግዚአብሔር ፍቅር ነው›› እንላለንና፤ ታዲያ በዚህ ተክተን ‹‹ግብረሰዶማዊነት ፍቅር ነው›› ልንል እንችላለን? ይህ መንፈሳዊና ንጹህየሆነው ፍቅር አካል አይደለም። የገዘፈ የስጋ ፍቃድ መታረም ያለበት ፍትወት እንጂ።

ብዙ አገልጋዮች የተሰጠንን ብዙ ነገር ትተን ትንሿን ነገር ለመጠበቅ ስንሮጥ ብዙ ጸጋዎቻችንን እናጣለን....ለመዘመር ብቻ ስንሯሯጥ ጸሎትን ስግደትን ትህትናን ወርውረን እንሰብራቸዋለን...ለመማር ብቻም ስንሮጥ ፍቅርን ቸርነትን ይቅርታን ወርውረን እንሰብራቸዋለን...አገልግሎት ብቻ ላይ ስንሮጥ ከጸሎት ሕይወት ፈጽመን እንወጣለን። ምን ለማለት ፈልጌ ነው"...ያለ ጸሎት ከሚሆን አገልግሎት ያለ አገልግሎት የሚደረግ ጸሎት የበለጠ ነው ..." ብለዋል አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ለማለት ነው።

+++"ድንኽል ወይስ አልዳንኽም?"+++

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ በአንድ መጽሐፋቸዉ እንዲህ ይላሉ። አንድ ወጣት ልጅ እንዲህ ብሎ ጠይቆኛል፤"አንድ ሰዉ ድንኽል ወይስ አልዳንኽም?" ብሎ ቢጠይቀኝ መልሴ ምንድነዉ? መጀመሪያ ይሄ ሰዉ እዉነተኛ ኦርቶዶክስ እንዳልሆነ ማወቅ አለብህ። በእርግጠኝነት ይሄ ሰዉ ፕሮቴስታንት ነዉ፤ወይንም ቢያንስ በፕሮቴስታንታዊ ባህል ዉስጥ ነዉ የሚኖረዉ፤ባህሉም የፕሮቴስታንት ነዉ። ከዚህ በፊት የተቀበልካቸዉን ምስጢራትንና ጥምቀትን እንደ ምንም ቆጥሮ፣በሃይማኖትህ ላይ ጥርጥር ለመሙላት በመሞከር፣ባለፈዉ

የሕይወት ዘመንህ ሁሉ አሕዛብ እንደነበርክ አድርጎ እንደ ገና እመንና ዳን ሊልህ ነዉ። ይሄ ሰዉ በፍጹም ኦርቶዶክስ ሊሆን አይችልም፤አነጋገሩም ይገልጠዋል። ለማንኛዉም እንዲህ ብለህ ልትመልስለት ትችላለህ፤

"በጥምቀት ከአዳም የወረስ ኀጢአት ድኜያለሁ፤ይሄ ድኅነት የሚገኛዉ በደመ ክርስቶስ የቤዛነትንና የድኅነት ኀይል ነዉ። ነገር ግን የመጨረሻዉ ድኅነት በስጋ ስንለይ የሚገኝ ነዉ። አሁንም በዉጊያ ላይ ነን "መጋዳላችን ከደምና ከስጋ ጋር አይደለምና፣ከአለቆችና ከስልጣናት

ጋር ከዚህ ከጨለማዓለም ገገሮች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሰራዊት ጋር እንጂ።" (ኤፌ.6፣12) ይሄንን ዉጊያ ድል ስናደርግና ስናሸንፍ ድኅነትን እናገኛለን..."

በስጋ እስካለን ድረስ "ድል ነስተናል፤ድኅነትን አግኝተናል" ልንል አንችልም። ስለዚህ ቅድስት ቤተክርስቲያን የቅዱሳንን ልደት አታክብርም ወይም የተጠመቁበትን ዕለት ይልቁንም ከዚህ ዓለም የተለዩበትን ወይንም መስዋዕት የሆኑበትን ቀን ታከብራለች እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፤"ዋነኞቻችሁን አስቡ፣የኑሮአቸዉንም ፍሬ እየተመለከታችሁ

በእምነታቸዉ ምሰሉአቸዉ።" (ዕብ.13፣7)ስለዚህ በቅዳሴ ላይ የቅዱሳንን መታሰቢያ እናደርጋለን፤በእምነት ፍጹማን የሆኑትንና ሕይወታቸዉን በእምነት የፈጸሙትን፣በአጸደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳንን ሁሉ እናስባለን። ይሄም የታላቁ አባ መቃርስን ከዚህ ዓለም መለየት እንዳስታዉስ ያደርገኛል፤ ነፍሱ ከስጋዉ ተለይታ ስትሄድ፣"መቃርስ፣አንተ ድነሽል" እያሉ አጋንንት ነፍሱን አሳደዱት፤ ነገር ግን ገነት እስከሚገባ ድረስ፣"በጌታ ጸጋ ድኜያለሹ"አላላቸዉም ነበር...!

---

† □ በዚህ ዓለም ሳለን የእኛ ማዕረግ የሚወሰነው እንደ እድሜያችን እንደ ተሰጥኦችን ወይም እንደ ችሎታችን ነው ።

#በዘላለማዊው_ሕይወት_ግን_ማዕረጋችን_የሚወሰነው_እግዚአብሔርን_የበለጠ_በምታውቅ_ልብ_ነው ። ምናልባት ብዙዎች የተናቁ የተጠሉና ችላ የተባሉት እነዚያ ተሰጥኦ ወይም ሥልጣን ያላቸውን ሊበልጧቸው ይችላሉ ። ስለዚህ ታናናሽ የተባሉትን በሙሉ እንዳትንቁ ይሁን ። እግዚአብሔር ኢያሪኮን ለማዳን በወደደ ጊዜ የመረጠው ጋለሞታዋን ረዓብን ነበር ። ከዚህ የተነሳ ረዓብ በጌታ የዘር ሐረግ ውስጥ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አንዱ ሆና እንድትቆጠር ሆኗል ። /ማቴ 1 /

ያለፈው ሕይወቷ ስለ ተረሳና ቅድስት ስለ ሆነች ለሚያስታውሳት ሁሉ ሕያው ምሳሌ ወይም አርአያ ሆናለች ።

እግዚአብሔር ጋለሞታዋንና አጋንንት የነበሩባትን ሴት ምን ያህል እንደተከባከባት ስትመለከት ልትደነቅ ትችላለህ ። እርሱ እንዲህ ያለውን እንክብካቤ ለተናቁት ለተጠሉትና ምንም ዓይነት ነገር አይገባቸውም ለተባሉት ሁሉ ያደርጋል ። /1ኛ ቆሮ 1*27-28 /

ከቅዱስነታቸው የህይወት ልምድ ከተሰኘው መፅሐፍ ላይ አንዱን የህይወት ልምድ ልጋብዛችሁ!!!!

<<.....ምንኩስናን ከመቀበሌ ከ አርባ ዓመታት በፊት በጎዳና ላይ በእግሬ ስጓዝ አንድ ባለሙያ ሰው አንድን ቁራጭ ብረት በኦክስጅን ሲበየድ ተመለከትኩት፤ ይህ ቁራጭ ብረት ብየዳውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ለያዘው የሚንቦለቦል እሳት እጁን ሰጥቶ ነበር። ከዚህ በኃላ ለራሴ እንዲህ

አልኩ፡- እግዚአብሔር በኦክስጅን የሚከናወን የብየዳ ሥራውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ የምናማርረው፣ የምንቃወመውና የምንሞገተው ለምንድን ነው?››

#ምን አይነት ጾም ?

ምናልባት በነቢዩ በኢሳያስ ዘመን እንደሆነው ፋይዳው የማይታይ እንዳይሆን ። "ስለምን ጾምን አንተም አልተመለከትከንም ? ሰውነታችንን ስለምን አዋረድን ? አንተ አላወቅህም ? ይላሉ /ኢሳ 58*3/ ጌታም እንዲህ ሲል ይመልስላቸዋል ። "እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ ። ድምጻችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም ። እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን ?... /ኢሳ 58*5/

ወንድሜ በመጀመርያ ጾም ሁሉ እግዚአብሔር የሚቀበለው እንዳልሆነ ማወቅ አለብህ ። በሳምንት ሁለት ቀን የሚጾመው ፈሪሳዊ የቀራጩን ያህል እንኳ ዋጋ አላገኝም ።/ሉቃ 18*12/ ።
#ስለ_ኃጢአት_ሳይሰቀቁ_ራስን_በትህትና_ሳያዋርዱ_የጾሙት_ጾም_ረብ_የለሽ_ነው ።
በኤርምያስ ዘመን የተደረገው የኃጥአንም ጾም እንደዚሁ ከንቱ አልነበረምን ? "በጾሙ ጊዜ ጸሎታቸውን አልሰማም "/ኤር 14*11/

ምክንያቱም ራሳቸውን መግዛት ተስኗቸዋል ። ይጾማሉ ነገር ግን ከሕግ እግዚአብሔር ርቀዋል ። ለሰዎች ይታዩ ዘንድ በግብዝነት እነጾማለን የሚሉ ሁሉ አሁን ሊያስቡበት ይገባል ። ዋጋቸው በምድር በሰው ፊት ቀርቶባቸዋልና / ማቴ 6*16-18/

አሁን አንተም ቆም ብለህ ራስህን መርምር ። እጾም ነበር ነገር ግን ምንም አላተረፍኩም እንዳትል ።ይልቁንም የሚጎድለኝ ምንድን ነው ? ብለህ መርምር የአምላክህን ፈቃድ ፈጽም ። ዋጋ አጥተህ ከሆነ የጾምን ዋጋ የሚያስቀር የኃጢአት ቅሪት አለ ማለት ነው ። ሌሎችም የሚጎድሉህ ነገሮች ይኖራሉ ። ስለዚህ ፦ እንዴት ልጹም የእውነተኛ ጾም ትርጉም ምንድን ነው እና ከጾም የማተርፈው ነገር ምንድን ነው ? ለሚለው ጥያቄዎችህ ምላሽ ታገኝ ዘንድ በጥቅሉ ስለጾም መነጋገራችንን እንቀጥል ፦ ተከተለኝ ።

ጠቃሚ ምክር

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ለደካሞች ትጉላቸው" ብሎ በተናገረው መሠረት ምንጊዜም የሰዎችን ሞራልና መንፈስ ለመጠበቅ እንሞክር። የሐዋርያውን ቃል በንቃት አድምጡ። ለደካሞች ትጉላቸው ሰውን ሁሉ ታገሱ ። ፩ኛ ቆሮ ፭ ÷ ፲፬ ሥሩን የሰደደ ኃጢያትን ነቅሎ ለመጣል ጊዜና ትዕግስት ስለሚጠይቅ እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉትን ደካሞች በጸጋው እስኪጎበኛቸውና ነጻ እስኪያወጣቸው ድረስ ትዕግሥት አድርጉላቸው። አንተም ተፈጥሮህ ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ከዚህ የሚከተለውን የሐዋርያውን ቃል ዘወትር ከፊትህ አስቀድም። ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ የተጨነቁትን ደግሞ ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ ። ዕብ. ፲፪ ÷ ፫ ።

- ❖ **አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ**

----------**----------

✝ ጭንቀት ✝

- ❖ አባታዊ ምክር

እኛ ከእግዚአብሔር እድንርቅ ካደረጉን ነገሮች አንደኛው ጭንቀት ነው ። ኦክስፎርድ ጭንቀት የሚለውን ሲተረጉመው "ከቁሣዊ ነገሮች ፍላጎ ት የሚመጣ ግፊት ወይም ውጥረት ይለዋል " የተሻለው ትርጉሙ ግን አላስፈላጊ ነገሮችን ከመፈለግ የተነሣ የአእምሮ ወይም የስሜ ት ድካም ፤ ውጥረት ፤ ወይም ሕመም ማለት ነው ። ጭንቀት ለሕይወታችን ከምንፈልጋቸው ወይም አላስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ፍላጎት የሚመጣ ግፊት ወይም ውጥረት ነው ። ስለሆነም የጭንቀት መንስኤው ምንድን ነው ? ስንል #ተስፈኝነት ሆኖ እናገኝዋለን ። በአጠገባችን ካሉ ሰዎች ቃል ከገቡልን ፤ ከሚቀርቡን ፤ ከቤተሰቦቻችን ወዘተ የምንጠብቀው አለ ። ተስፈኝነት በሁለት መንገዶችሊመጣ ይችላል ። ✞ስለ ሰወች ያለን ተስፈኝነት አለ ። ሌላው ✞ሰዎች ስለ እኛ አላቸው ብለን የምናስበው ነው ።

በማንኛውም መንገድ የተጨነቀ ሰው ከገጠማችሁ ከሁለቱ በአንዱ ምክንያት እነደሆነ ታረጋግጣላችሁ ። ሌላ ሰው ለእኛ ዝቅተኛ ግምት ሠጥቶን ሊሆን ይችላል ። ወይም እኛ ራሳችንን ዝቅ አድርገነው ሊሆን ይችላል ። ወይም እግዚአብሔር እንደተወን አድርገን ልንወስድ እንችላለን ። ወይም ከእግዚአብሔር እንደራቅን ሊሠማን ይችላል ።

ጭንቀት ከእነዚህ የአንዱ ስሜት ውጤት ነው ።

የቁስ እቃ ፍላጎት እንድንጨነቅ ያደርጋል ። ምን ማድረግ እንዳለብን አናውቅም አንዳንድ ጊዜ አወንታዊ በሆነ መልኩ ለስሜቱ ምላሽ እንሰጣለን ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አሉታዊ መልስ እንሰጣለን ። ሌላ ጊዜ ደግሞ አወንታዊም አሉታዊም ሳይሆን ይቀራል ።

✝ከጭንቀት ለመላቀቅ የሚረዳ ዋነኛው ዘዴ ተፈጥሮአዊ ማንነታችንን ማሰብ ነው ። ቁሣዊ ሆነን አልተፈጠርንም ። የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ነው ። ቤተ መቅደሱ ሆነን ነው የተፈጠርነው ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ነው የተፈጠርነው ። ግፊቱም ፤ ጭንቀቱም ፤ሕመሙና ፤ውጥረቱ ፤በመጣ ጊዜ ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠት ይኖርብናል ። ከእግዚአብሔር ኃይል በላይ የሆነ ግፊት ወይም ውጥረት የለም ። ስለሆነም

እኔ ተሸክሜ ከምጨነቅ እግዚአብሔር እኔን ሆኖ እንዲሸከም አደርጋለሁ ። እርሱ ጫናወቻችንን ያቀላል ።

✝ ዮሴፍ በብዙ ጫናወች ውሰጥ ይኖር ነበር ። ወድሞቹ ጉድጓድ ላይ ሲጥሉት ምናልባት መረዳት በማይችልበት በሕፃንነቱ ጊዜ ነበረ ። እንደገናም ለባርነት ሸጡት ። ከቤተሰቡም ጋር ተለይቶ መኖር ጀመረ ። የንጉሱ የፈርኦን ሚስት በሐሰት ከሰሰችው ። በዚህም የተነሳ እስር ቤት ተጣለ ። በእስር ቤት እያለ ማንም የሚያስታውሰው አልነበረም ። ይህ እንግዲህ መጠነ ሰፊ ወደ ሆነ ጫና ውስጥ ያመጣዋል ። ሆኖም ግን ዮሴፍ እነዴት ለመፍታት ሞከረ ? ችግሩን እነዴት ተቋቁመው ? በእያንዳንዱ ሁኔታ ዮሴፍ ራሱ ዮሴፍ ነበረ ። አልተለወጠም ።በሁሉም ሁኔታዎች ተመሣሣይ ፤ ማንነት ፤ ፍቅር ፤ እምነት ፤ ነበረው ። እግዚአብሔርን አዘውትሮ ይጠራ እና ይለምን ነበረ ። እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ አጠገቡ ነበረ ።

---**---

ዛሬ ደግሞ አባታችን እንዲህ በማለት ይመክሩናል ያጽናኑናል፦

- ነገ ለአንተ የተሸለ ነዉ!!!!!
- ያለህበት ዛሬ ለአንተ እጅግ አሰልቺ ከሆነ ለነገህ ኑር።
- በዚህ ነገህ ዉስጥ አንተን ለማረጋጋት የእግዚአብሔር እጅ ወደ አንተ መዘርጋቱን ተመልከት! ይህንን ካደረግህ በዚህ ነገህ ዉስጥ ለችግሮችህ ብዙ መፍትሔዎችን መመልከት ትችላለህ።
- የአንተ ዛሬ ጨለማ ከሆነ ነገህ በፊትህ የብርሃን መስኮቶችን ይከፈትልሀል
- ቅዱሳን ነገ ለሚያገኙት የዘለዓለም ህይወት ስለ ኖሩ ተስፋቸዉን ሁሉ በዚህ ነገ ላይ ጥለዉት ነበር።

•ሳያል ባሳደደዉ ጊዜ ነብዩ ቅ.ዳዊት የኖረዉ ለነገዉ ነዉ።

•ነብዩ ቅ.ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ዉስጥ ሳለ የኖረዉም ለነገዉ ነዉ።

- •ቅ.ዮሴፍ በወኀኒ ሳለ አባቱ ቅ.ያዕቆብ ደግሞ በወንድሙ በዔሳዉ በተሰደደ ጊዜ የኖሩት ለነገአቸዉ ነበር፤ ያዕቆብም ከመሰደድ ዮሴፍም ከግዞት ህይወት እንደሚወጡ በእግዚአብሔር ታምነዋልና።
- ነገሮች ለአንተ አስቸጋሪ ከሆኑ ለራስህ ነገ መፍትሔ ይገኝላቸዋል ብለህ ንገረዉ።

ከዚህም በኋላ ለዚህ ነገህ በፈገግታና በደስታ ኑር!!

¢ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሸኖዳ ሳልሳዊ

ክፍል 2 ተፈፀመ